# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

የቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ግቢ ታምቧል ። የጎረቤትና የአካባቢው ሰዎች ካጥር ውጪ ፣ በምንዳዬ ጎጆና በአዳራሾቹ ሰበሰብ ዙሪያ ተቀምጠዋል ።

ልኬለሽ ወገቧን በነጠላዋ ጥርቅም አርጋ ታጥቃ ደረቷን እየመታች ልብ በሚነካ አሳዛኝ ድምፅ ታለቅሳለች ።

ቀኛዝማች ፣ ውጥንቅጡ በወጣ ስሜትና ፣ ምክንያት ፍለጋ በሚባዝን ሐሳብ ተወጥረው እየተቅበጠበጡ ፣ "እኔ በላይነህ አይደለሁም! እንኳን ምልክቱ ብቻ ተገኘ ፣ የዚህ የደሃ ደም በከንቱ ፈሰሶ አይቀርም" እያሉ በንዴት ከስለው እልፍኛቸው ውስጥ ይንቆራጠጣሉ ። ብስጭታቸው ናር ሲል ደግሞ ምንዳዬ ቤት ደርሰው ይመለሳሉ ።

ወይዘሮ እልፍ — ይከንዱ ፣ ካንጀት ጠብ በማይል አጉል ደስታ ውስጥ ውስጡን ይቦርቁና ፣ ምንዳዬ ቤት ሲገቡ ደግሞ ሐዘን እንዳንገበገበው ሰው ያባይ እንባ ያነባሉ ። መለስ ብለው ቆርቆሮው ቤት ውስጥ ይገቡና ዐይኖቻቸውን ወደ ላይ ሻጥ ፣ እጆቻቸውን በፊታቸው አኳያ ሽቅብ ዘርጋ ያደርጉና ፣ "አይ አንተ ጌታ ! ፈጥረኸኛላ ! አለሃ !" እያሉ ያመሰግናሉ ።

የምንዳዬ ልጆች እቤታቸው ደጃፍ ተቀምጠው ፣ ትልቁ እንባው ፣ ልሃጩና ንፍጡ እየተዝረበረበ ፣ ትንሹ የእናቱንና የወንድሙን ልቅሶ እያየ ሆዱ ባብቶ እየፈራ ያለቅሳሉ ። አካባቢውን የሐዘንና የብስጭት ጥላ ጥሎበታል ።

* * *

ቀኛዝማች ፣ ከቅምጣቸው ጋር ከተገናኙ ከሳምንት በላይ ሆኗቸዋል ። ምኞታቸው በእግረ — ሕሊና ማጀቴ ተሻግሮ የልቡን ሲያደርስ ፣ አካላቸው ግን በዛሬ — ነገ እንደጓጓ ቀረ ። በዚያ ላይ በሴትዮዋ መልከና ዳመጠ ገላ ከተማረኩ ጀምሮ ፣ ከገዛ ባለቤታቸው ጋር እያወሩ ወይም ጋደም ብለው በመደባበስ ላይ እያሉ እንኳ ፣ ሴሰኛ ነፍሳቸው ማጀቴ ትገባና ከቅምጣቸው ጋር ይላፋሉ ። በእንዲህ

ያለው ወቅት የላይ ገላቸው ይሞቅና መላ አካላቸው ይሰጠጣል ። ሰው በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ ላይ ሊገኝ የሚችል ቢሆን ምንኛ ደስ ባላቸውና ባንድ ጊዜ ማር — አምባና ማጀቴ በተገኙ ነበር ። ሚካኤል እንዲህ — እንዲህ ያለውን ነገር ለአምላክ እያቀረበ የሚያስፈጽም ቢሆን፤ለውለታው ምላሹ ሊቀ ሊቃውንት ቀጥረው አዲስ "ገድል ወይም —ተአምረ — ሚካኤል" ያጽፉለት ነበር ። ወይ ነዶ ! ሁለቱም ቀረባቸው! እሳቸው ግን ፤ አካላቸውን ሁለት ቦታ ላይ የሚከፍሉትና ምኞታቸውን የሚገልጹት በምንዳዬ ሰውነት እየሠረፁ ይመስላል ። እሱ በወይዘሮ ደጅ ይጥኑና በሳቸው መካከል አንድ እግሩ ማጀቴ ፤ ሌላው እግሩ ማር —አምባ የቆመ ቅርፀ ደጋን የሰው ተክል ነው ። የሁለቱ ሰዎች ሐሳብና ምስጢር ከወዲያ — ወዲህ የሚሸጋገረው በምንዳዬ እንደበት ነው ።

ቀኛዝማች ፤ ለመጨረሻ ጊዜ እነ — እርም — አይቀሬን አስከትለው ሚጨራና ሀገረ —ማርያም ያለውን ርስትና ይዞታውን ለመመልከት ሲሔዱ ፤ ምንዳዬ ግን ውጪኛውን አጥር የላላ — የላላውን እንዲያሳጥርና እንዲያጠባብቅ በመታዘዙ አብሮ አልሔደም ። የታዘዘውን ሠርቶና — ሕሠርቶ ዐረፍ ከማለቱ ቀኛዝማች አጃቢዎቻቸውን አስከትለው ፤ ገና ፀሐይ ሳታሽቆለቁል ስለገቡ ወደ እልፍኝ ተጠርቶ ሔደ ።

ሸዋርካብሽ ፤ የሰውዬውን እግር በገበቴ ውሃ ስታጥብ ከእርሱ ጋር የሚያወሩትን ሁሉ ጆሮዋን አቁማ ስትሰማ በማየቱ ፤ ከእግር— እስከ ራሱ ወረረው ።

"ደከምሃል እንዴ!" አሉት ፤ በመጨረሻ ቢደክመውም ደክመኝ እንደማይላቸው እያወቁ ።

"ምን ሠራሁና ፤ እየሁ ደይ — ለደይ እኮ ነው የዋልኩት" አለ ድካሙን ደብቆ ።

"እንግዲያውማ አንዳፍታ ማጀቴ ደረስ ብለህ ብትመጣ ፤ እንዳሳቤማ ትላንትና በጊዜ እገባለሁ ብዬ ነበር ። አንተን'ንኳ ያላስከተልኩህ ለውሎ — ገብ መንገድ ብዬ ነበር ። ሰዉ አላላውስ አለኝ ። ገብቼ አድሬ ቢሆን ኖሮ ረፋዱ ላይ ትመለስ ነበር ። አሁንም ቢሆን ገና ነው ፤ ባንተ አረማመድ ፤ አንዳፍታ ትንደረደራታለህ ። ከመሸብህም ጢት ትመለሳለህ" ብለው እንደ ጨረሱ ሸዋርካብሽ ገበቴዋን ይዛ ወጣች ።

"ያው እንግዲህ ነገ መሔዷ ነው ። ለምን አልሸኘኸኝም ብላ እንዳታኮርፍ ወረድ ብለህ እዚህ አለማደሬን ንገራት ። እኔማ ብቅ ብዬ



እሸኛታለሁ ብዬ ነበር ። ሰው አሰበበት አይውል ። ሒጂ — ሒጂ ብሎ አጉል አረገኝ እንዳትል" ብለው ተንጠራሩና ፤

"ያልኩህን ሁሉ ልብ ብለህ ይዘኸው የለ ?"

"እዎ!"

"ትስተዋለህ ብዬ ሳይሆን ፤ ነገር ያበዛሁብህ መሰሉኝ ነው ። እዎ ንገራት ፤ መቼም የቧ ነገር ፤ እዚህ ያለው ጣጣ ሁሉ ጣጣ አይመስላት ።"

"የከፋት ታይሆን ፤ ባያኡት ነው ። ምን ሴቶቹ — — —" ብሎ ሳይጨርስ ፤

"የከፋትስ አይደለም ፤ እንዲያው ብቻ የራስ የራሷን ስታይ —"

"ምን እሳቸው ብቻ ፤ ሁሉም የራስ የራሱን ነው እሚያየው" አለ አፍ አድጦት ።

"ነው ብለህ ነው? ኧረ ስንት አንገት ያለው ሰው አለ ፤ ብቻ እንደ የሰዉ ቆዳ ነው ።"

እዚያው እልፍኝ እንደ ቆመ ሸዋርካብሽ የእጅ ውሃ አምጥታ ከማስታጠቧ አረጋሽ ገበታ ይዛ ገባች ። ምንዳዬ ለመሔድ ቢያስብም ገበታ ሲቀርብ አይቶ ቢወጣ ደስ እንደማይላቸው ስለሚያውቅ ፤ ፈንጠር ብሎ እበሩ ጥግ ተቀመጠ ።

ቀኛዝማች ፤ ለወጉ ያህል ጐራርሰው መዓዱ እንደ ተነሣ ፤ አረጋሽ የነካ የነካውን በሌላ ገበታ ላይ አድርጋ አቀረበችለትና በቅራሪ እያወራረደ በልቶ ፤ እጅ ነሥቶ ወጣ ።

ወይዘሮ እልፍ — ይከንዱና ሸዋርካብሽ ካጥር ውጪ ሠዋራ ቦታ ላይ ቆመው ገልመጥመጥ እያሉ አፍ—ላፍ ገጥመው ይወያያሉ ። እንደ ተለመደው ስለ ባላቸው ጠባይ የምታውቀውን አንዳንድ ሁኔታ ከነገረቻቸው በኋላ ፤ ምንዳዬ ወደ ማጀቴ ሲሔዱ ለሴትዮዋ ይዞላቸው የሚሔደውን ነገር እንዲያዩና እንዲከታተሉ ነገረቻቸው ።

"መቼ ነው እንዲህ ያሉት ? አሁን ነው...?"

"ገና ገባ እንዳሉ ፤ እግራቸውን እያጠብኳቸው ..."

"ታዲያ እንዴት እንዴት አሉት ? ይኸነዬ በወጉ አልሰማሽም ይሆናል ?"

"ጣዩ በረድ ቲልልህ ፤ ሒድ ብለውታል ።"

"ከማ ጋ ሁነህ ሒድ አሉት ?"

"ከማም ጋ አላሉት ።"

"ብቻውንማ ከሆን ፣ እህልም ይዘህላት ሒድ አይሉት ፣ እንዲያው ነውዱ ጐተራው ያለው በየቦታው በያው ደይ — ደጁን ቢልኹላትማ ያያቸዋል ።"

የተበሳጩ ለመምሰል ጣታቸውን እያጮሁ ከንፈራቸውን ነከሱ ። በሐሳብ ሽፍታው አድፍጦ ወደሚጠብቅበት ቦታ ሔደው 'ያ ከውካዋ እየመጣልህ ነው ፣ ዛሬማ አንጀቴን ካላራስከው — —'አሉት ኮስተር ብለው ። "የሱንም የሳቸውንም ነገር የሣር — አምባው ጎርጊስ ካላ ሳየኝማ ፣ እንዲህ እንዳነፈሩኝማ ካላነፈርከልኝ — — —" ብለው ንግግሩ አልያያዝ ፣ ሐሳቡ አልመጣ ስላላቸው ዝም አሉና ቆሙ ።

ከአፈሳ ጋር የተሸረበውን ሴራ እንዳትጠረጥር በማለት ፣ "የሳቸው ነገር ምን ማለቂያ አለው ፣ ነጋ— ጠባ ቢያወሩትም አያልቅ ፣ ፈጣሪ እንዳለልኝ እሆናለሁ ። አሁን የሳቹውን እንተወውና አፈሳ አደራሽን ብሎኝ ሔዷል ። ያቺ ሚስቱም የለች መሰል ፣ በይ አሁን ቶሎ ቶሎ በይና ለሳቸው ካሰናዳነው እንጀራና ወጥ በደህናው አገልግል ቋጥሪልኝ ፤ ጐሽ ፈጠን በይ ታዲያ! ገና ቅድም ነበር የነገረኝ ፣ ስትጨርሺ ቀስ ብለሽ ጠቀስ አርጊኝ ። እስተዚያው እልፍኝ ነኝ" ብለው ወደ ቤት ተመለሱ ።

ሸዋርካብሽ የታዘዘችውን አገልግል ስታዘገጃጅ አረጋሽ ድንገት ከተፍ አለችባት ። ሁለቱም በየፊናቸው የሰሙና ያልሰሙትን ጨማምረው የሚናገሩት የተለየ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን ፣ የየራሳቸውን ዘመድ የጠቀሙና ያስደሰቱ እየመሰላቸው ነበር ።

"እ! ደሞ የምን አገልግል ትቋጥሪያለሽ ልጄ ? አለቻት አሽቆልቁላ እያየች ።

"እያየሽው ምኑን ትጠይኢኛለሽ! አገልግል ነዋ!"

"ለማን? ይኸነዬ እኮ በዚህኛው አገልግል አላሉሽ ይሆናል" አለቻት እንደ ዘበት ።

"እኔ ደሞ የት አባቱ ዐውቄ ! ለዘመድ ይሆናላ ! — — እቴዋ ናት" አለች ሳታስበው ።

"ደሞ ከመቼ ወዲህ ነው ፣ ከዚህ ከድስት አጥቅሺ የተባልሽው ? ይኸነዬ እኮ አላሉሽም" አለች ወዘ ፍልቅልቁን ድስት እየተመለከተች ።

"እኔ ምን አእልሻለሁ ፣ ምን አርጊ ነው እምትዪኝ ፣ ከየትኛው ድስት ነበር ያዘዝሻት ብለሽ ጠይቂያት ።"

"እንግዲህ ነገርሽን አትጐንጉኚ ፣ ደሞ ደህና ሰንብቼ ነበር ።"



"ታዲያ እንዲህ ያለውን ምን አጠያየቀሽ?"

"ኧረ ለቀቅ አርጊኝ እቴ! — —ሆ! እኔ ድስቱንስ አብረሽ ብትቋጥሪው ምን ቸገረኝ" ብላ አገልግሉን ትኩር ብላ አይታው ወጣች ።

"ኩቲ የሰው ኩቲ! ይኸነዬ እኮ ትንሽ የወሬ ጫፍ ብታገኝ ይዛ ለመሮጥ ነው" ብላ አገልግሏን ለጉማ ዘለንጋው ላይ አስቀመጠችው ።

* * *

ምንዳዬ ወደ ቤቱ ሊገባ ሲል ፣ ልኬለሽ ከቤት ውጪ ከበሩ በስተቀኝ እተተከለው ወፍጮ ላይ የአተር ክክ አቁታ ሽሮ ትሰልቃለች ። አንገቷ ላይ በጥቁርና ሰማያዊ ወፍራም ቋድ ማተቦች የተንጠለጠሉት መስቀልና ድንብሏ ፣ እጅዋ ከመጁ ጋር ወደ ፊትና ወደ ኋላ ሲመላለስ ፣ ደረቷን እየደቁ እንሹሉ ይላሉ ። ቹርባዋ ባንገትና ትከሻዋ ግራ — ቀኝ ተነስንሶ ከእንቅስቃሴዋ ጋር አብሮ ብትን ጥቅልል ይላል ። በሦስትዮሽ በመጉንጉኑም ቀጠን ያለ የጥቁር ሐር ትት ይመስላል ። የሽሮው ብናኝ አልበሉበሻና ከንዷ ላይ ረጧል ። ምንዳዬ አጠገቧ ቢደርስ ፣

የባቄላ አበባ በመሰለ ጥርስ ፣ ብስል እንኮይ በመሰለ ደም — ግባታም ፊት ሣቅ ብላ ተቀበለችው ። እሱም በበኩሉ ፈገግ ብሎ እያትና የንጋት ብርሃን መሳይ ፈገግታዋን ተቀብሎ ወደ መላ አካሉ ናኘው ። እንዲህ ነው ዘወትር ወደ መንፈሱ የምትሠርፀው ። በዚህ ጸዳለ — ገጽታዋ ነው ድካሙ ሁሉ ተገፍፎ ብስጭቱ ሁሉ የሚረገፈው ። የብርታቱ ምንጭና የነፍሱ ቀንዲል ነች ።

ጎጆዋቸው በመተሳሰብ ተዋቅራ ፣ በመተማመን ተማግራ ፣ በጽኑ ፍቅር ተመርጋ ተለብናለች ። የአንድነታቸውን ጥናት የመከራ ውጣ — ውረድ ቢወዘውዛትም ፣ ውሉንም ተቋቁማ ከሣን — እምባ — ሣር — እምባ — — —አልወደቀችም ።

"ልኬ !" አላት ፣ መጅዋን ለቃ ቀና እንዳለች ።

"አቤት" አለችው ፈገግታዋ እየደመቀ ።

"ልከውኝ መሔዴ ነው ።"

"ወዴት ልጄ ?" አለች ፣ ድንገት የፈገግታዋ ሙቀት እየቀዘቀዘ ።

"እዚያው ግጀቴ ነዋ!"

"እንዲህ መከራህን ስታይ ውለህ አሁን ደሞ ማጀቴ?" አለችው ልብን ጠቅ በሚያደርግ አሳዛኝ ድምፅ ። ላጭር አፍታ ያህል ቅዝዝ አለና ፤

"እሳቸው ታዲያ ስልል ቲያጡ ፣ እኔ ምን ላርግ ልኬ ፣ እስኪያልፍ ያለፋ የለ ? — —"

"አንተ እኮ ታዲያ እስኪያልፍ ያለፋል እያልክ መሞትህ ነው ። አንተ እንዲያው መስሎህ ይወዱኛል እያልክ ልብህን ታወልቃለህ የሚወድ ሰው እንዲህ ነው እንዴ? ከወደዱህና ታሰቡልህ እንዲህ ስትንገላታ መዋልክን እያወኡ ሌላ ሰው አይልሁም ኖሯል ? ሰባሂናቸውቬ — —የወደደ ሰው እንዲህም አደል!" ብላ ግድግዳውን ተደግፋ ዝም አለች ።

"እንዴት ብዬ ልንገርሽ? እማታኢው ነገር የለ ። ጌታ ሎሌውን ወደድኩህ እያለ ነው እሚገለው አሉ ። በየህ ላይ ደሞ መታመንን የመሰለ ጥሩና መጥፎ ነገር የለም ። ወይ ከነምስጢርሽ ትሞቻለሽ ፣ አለያም ለምስጢርሽ ሲሉ ይገሉሻል ። ያመነሽን ሰው የከዳሽና ሸተት ያልሽ ለት ደሞ በጥርሱም አይለቅሽ" ብሎ እሱም አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ ።

ልኬለሽ በሐሳብ ገሥግሣ ቀኛዝማች እልፍኝ ስትገባ ድንክ አልጋቸው ላይ ጋደም ብለዋል ። "ዋ ነዶ ሴት መሆኔ" ብላ ዙሪያውን መልከትከት ስትል ደኅና ጅናም ዱላ ከበሩ ሥር ታገኛለች ። ደስ ይላታል ። ጥርቅም አርጋ ይዛ መኻል አናታቸውን ስትላቸው ደማቸው ቲሊል ይላል ። ፎከረው ይነሡና ሊነጥቋት ሲሉ ሮጣ ስታመልጥ ከሐሳቧ ትባንናለች ። ከዚህ ቅፅበታዊ የሐሳብ ጉዞዋ በኋላ ፣ "ምነው የምር በሆነና የመጣው በመጣ" አለች ። ወኒያም ናት ። ምንዳዬ ሰውገድሎ የጠፋለት እንኳ ከልቅሶዋ በፊት ፣ "አበጀ! እንኳንም የነየተበትን አልተወ! ተንግዲህ የትም ሔዶ አውሬ ይብላው" ብላ ነበር ።

"አሁኑኑ ሒድ አሉህ እንዴ ?" አለችው ቀና ብላ ።

"ጣው በረድ ሲል እሔዳለሁ ።"

"ተሔድክ አሁኑኑ ነው መሔድ — አጉል ይመሽብህና . . ."

"አይ ልኬ ፣ ለሴላ መሰለሽ ፣ እዚያው አድረህ ሸኛት ብለውኛሊ — "

"እኛኑ ሴትዮአቸውን! አይ መታደል ፣ እሳቸው አዲሳባ ሊሔዱ..." አለች እየሣቀች ።



"እሳቸው ያልሔዱ ማ ይሔድ ! እንግዲህ ሁለቱንም ወስደው ያተራምሱ ።"

"ከነሱ ኑሮስ የኛና ያንተ ድህነት በስንት ጣሙ እቴ ! ዓለም አደል እንዴ ! አበስ ገበርኩ እቴ ! በተስኪያን መሳሙ ለምኑ ነው ? ሁለት — ሦስት ሚስት እያገቡ ? ቄሶቹም ዋና አድር ብዬ ናቸው ። ይኸነዬ እኛ — እኛ እደሆቹ ላይ ቢሆን ይበረቱ ነበር ። ያረበርባሉቬ ቁም — ነገርም የላቸው ። ጨከን ብለው ገሥጥ ቢያረጓቸው ከትት ይሉ ነበር" አለችና ዘወር ብላ እጅዋን በቀሚሷ ጠርዝ ጠራረገችው ። "እምኬደው አዳርከን ተሆነማ ጣዩ በረድ ይበልልህ ። እኔም ትንሽ ወጥ ቱክ — ላርግና በልተህ ትሔዳለህ" ብላው ሽሮውን ከመጅና ከወፍጮው ላይ በሙርዬ ጠራርጋ ፣ ከጳቱም አነስ ባለች ቁልቢጥ ሽሮ ይዛ ወደ ቤት ገቡ እሱ አልጋው ላይ ጋደም ሲል እሷ ወደ ምድጃዋ ሔደች ።

* * *

ምንዳዬ ፣ ቀኛዝማችን ተከትሎ አዲስ አበባ በመሔዱ ረገድ ከራሱ ጋር በሁለት ምክንያት መክሮ ጨርሷል ። ልኬለሽን እንደራሱ ቢወዳትም የመሔጃውን ምክንያት አንጠርጥሮ ያልነገራት ብስጭቷን ስለሚፈራው ነበር ። ቁጣዋም ሆነ ብስጭቷ ለሱ በማሰብ በመሆኑ ፣ ምንም ያህል ብትቆጣው ፣ ቁጣዋ ሁሉ እንደ ወለደው ልጁ ቁንጢጥ ደስ ይለዋል እንጂ አይከፋውም ። ከባላንጦቹ ጋር በመሐላ ፣ በወጀና በመቆረር ተስማምቶ ቢዋዋልም ፣ በላካቸው ሽማግሌዎች ጫናና ብርታት ማጀቱ ድረስ እንዲሔድና እንዲገበይ በመደረጉ 'ጃራንና የገሌ ወንዝን አለመሻገሩ ነውቬ ዞን — እምባ ሊገባ ምን ያክል ሲቀረው ነው' እያሉ መጸጸታቸውንና በተደረገው ውል ማዘናቸውን ሰምቷል ። ስለዚህም ጊዜ ጠብቀውና ሰበብ ፈልገው ሊበቀሉት እንደሚፈልጉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከርስቱና ከትውልድ መንደሩ ተነቅሎ ከነቤተሰቡ በሰው ቤት ሎሌነት የሚኖረው ኑሮ ከድህነት እንደማያላቅቀው በመገንዘቡ 'እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል' እንደሚባለው አብሮ ለመሔድ ልቡ ቆርጧል ።

የልኬለሽ ድስት ትንተከተካለች ። የእሳቱ ላንቃ ዙሪያውን ይገርፋታል ። እሷ ግን ፣ በጭራሮ ስንጥር ዐመዱ ላይ ምስቅልቅል መስመር እየሠራች ስታፈርስ ፣ ስሜቷን ለዐመዱ የምታዋይ ትመስል ነበር ። ወደ ፊት ስትጠጋ እሳትና ረመጥ ፣ ወደ ውስጧ ስትገባ ንዴትና ብስጭት ፣ ከውጭ ረመጥ ፣ ከውስጥ ረመጥ ፣ የልኬለሽ ሕይወት ።

* * *

ወይዘሮ እልፍ — ይከንዱ ፣ የምንጻፉን ወደ ማጀቱ መዓከ ፊጥ ነው ለመናገር ፣ የት እንደሚያዩና ምን እንደሚረግጡ ሳያስተውሉ ፣ ወደ አፈሣ ቤት ሲገሠግሡ ቤቱ ከቀድሞው የራቀ መሰላቸው ። የአጥሩን በር ገፋ አድርገው ሲገቡ ፣ እግሩን ዘርግቶ ድግር ይጠርብ ነበር ። ገና ብቅ እንዳሉ ምሣሩን አስቀምጦ ጥርብራቢውን ከቁም ጣው ላይ እያራገፈ ተነሥቶ ተቀበላቸው ።

"እኔስ ያላገኘሁህ እንደሁ ብዬ — —" አሉ ትንፋሻቸው እየተ ከታለበ ።

"እኔ ዛሬ እየቼ ነው የዋልኩት — —ቀደምሽኚ መምጣቴ ነበር ።"

"እንኳንም የዋልክ ፣ እኔው መጥቼልሃለሁ ፣ ይልቅዬ አሁን ቶሎ በል ፣ ሆነም ቀረም ዛሬ ነው" አሉ ዐይናቸው ከወዲያ — ወዲህ እየ ቃበዘ ።

"ምነው ? ደኅናም አይደለሽ እንዴ?" አለ በንቃት ቆሞ ።

"ያ መዘዘኛ ፣ ማጀቱ ሊሔድልህ ነው" አሉ ወደ ጆሮው ተጠ ግተው ።

"መቼ? አሁን?"

"አዎ አሁን ፣ አዳሩን ታይሆንም አይቀር ። ዛሬ ነው መበር ታት ። እንግዲህ ሱሪ ይኸነዬ ነው — ቶሎ በል! እሱ እንደሁ ግድየለ ውም ። ቢመሽም ቢጨልምም ቁብ የለው ። ዋናው ነገር ቀድሞ መገ ኘትና ቶሎ የልብን ሠርቶ ዘወር ነው ። የዘንድሮ ወሬ እንደሁ በዚህ ሲታፈን ፣ በዚያ ያፈተልካል ፣ እንዲች ብለህ ትንፍሽ እንዳትል ። እንጀራም ባገልግል አስቋጥሬልሃለሁ ፣ በል አሁኑኑ ተነሥ" አሉ ቸኩለው ።

"የምን አገልግል ?"

"አይ ያንተ ነገር ፣ አሁን ባታስጮኸኝ ምናሻህ ልጄ! ለግ ብሎ መሰለህ ጢሻ ለጢሻ ፣ ጊዜ ያለ ጊዜ መባዘኑ? ለኔው ብሎ እኮ ነው!"

"እሱስ እውነሽን ነው ፣ በዚሁ ይዘሽው አትመጪም ኖሯል —"

"ሸዋርካብሽ ወና ድረስ ሔዳ ትጠብቅሃለች ። ቶሎ ቀድመህ ጠብቃት ። ደሞ እፍህ ዘረጥ ብሎ ይኸን ወሬ እንዳታወራት ፣ ሚስቱ የለችም አገልግል ቋጥሪለት ብዬ አወነባብጃታለሁ ። ቃላችን አንድ



ይሁን ብዬ ነው ። በል እንግዲህ" ብለው የጉዳዩን አጣዳፊነት ለማሳ ወቅ ሁለቱን ድግር እንሥተው እቤቱ ደጃፍ አስቀመጡለት ። እሱ ወደ ቤት ሲገባ ፣ እሳቸው ቸኩለው ሲመለሱ ፣ ሚስቱ ሊጢን ሳትለ ቃለቅ ብቅ አለችና ፣

"እንዴ? እቴሜቴ!! ምነው አለመግባትሁ? ቡሃቃኮ ገብቼ ነው ።"

"ቸኩዬ ነው ግድየለሽም ፣ መግባቱን አጥቼው መሰለሽ ፣ ግቢ!" ብለዋት በጥድፊያ ወጥተው ሔዱ ።

"ምን ሰሙብኝ ጌታዬ ሆዬ ! ደሞ ተመቼ ወዲህ እንዲህ ያለ ጠባይ አመጡ!" ብላ ተመለሰች ።

አፈሣ ወዴትና ለምን እንደሚሔድ እንዳይታወቅበት ፣ ረጋ ባለ ሁኔታ አደፍደፍ ያለ ነጠላውን ለብሶና እንደ ዘበት ጠበንጃውን ይዞ ከቤት ሲወጣ ፣ ከባለቤቱ ጋር ዐይን—ለዐይን ግጥምጥም አሉ ።

"ወዴት ትሔድ ነው ልጄ?" አለችው ጠበንጃውን እያየች ።

"እቴዋ ና ሰው ሸኝተህልኝ ትመለሰላህ ብላኝ ነው ፣ እየሁ እቅ ርቡ ነው ፣ እርቄም አልሔድ" ብሏት ወጣ ። ሥጋትና ፍርሃት ስለ ተሰ ማው ዋናውን መንገድ ለቆ ባሳቻ — ባሳቻው ጉዞ ቀጠለ ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ውስጥ — ውስጡን ሥጋትና ተስፋ እያራረጣቸው ወደ ቤት ሲገቡ ፣ ሸዋርካብሽ ውሃ አርከፍክፋ ቤት ስትጠርግ ደረሱ ።

"አይ ጉደኛ ! ይኸነዬ ያን ያልኩሽን አላዘጋጀሽም ይሆናል ፣ ያንቺ ነገር እኮ" አሉ አካባቢውን ሳይመለከቱ ። የልባቸው ምት ጨምሮ ሰውነታቸው ተጣድፏል ።

"የመቼሽን ነው እቴዋ?" አለች ቅጠሉ ያልደረቀ መጥረጊያ ይዛ ።

"በያ ቶሎ በይ ! እንግዲህ ያንቺ ነገር — — እርሜን ዛሬ ብለ ምናት ታስብዬብኛለሽ ። እያ ሃች ወና ቀድሞ ይጠብቅሻል ፣ ይኸነዬ ደርሶ ይሆናል ። ደሞ በዚያው እልም በይ አሉ ። አሳብ የለሽ ! አቀብ ለሽው ቶሎ ነይ ። ነግሬሻለሁ ። ገና ስንትና ስንት ሥራ አለብን" ብለው ወደ እልፍኝ አመሩ ።

የጅዋን ላይ የአቧራ ብናኝ በጭብጨባና በእፍታ ቀንሳ ፣ የቀረውን በቀሚሷ አባበሰችው ። አገልግሏን አዝላና አሮጌ ነጠላዋን ለብሳ

በጓሮው የእጥር በር በኩል ስትወጣ ፥ አረጋሽ ደግሞ በዚያው በር ወደ ግቢ ስትገባ ፊት —ለፊት ተገናኙ ። ሽዋርካብሽ ዝም ብላ ስትሔድ አረጋሽ ቆም ብላ አየቻት ።

“ይች ደሞ ለማ ይሆን? እሚያቀብሉት አያጡ? መሔድ ሲሳናቸው ጊዜ ፥ እየፈተፈቱ ይልኩ ጀመር ። አበስኩ ገበርኩ እቴ ! ‘ቤት እንዳልጠላ እናቴ አለች’ አለ ያ ጋሼ መከታ ። ማባሽ ሐጂ አለሽ ብለው ያስፈጥጡኛል ፥ ተከትሎ ነበር ማየት ፤ እንዲያው ዛሬ ቀይ —” ብላ በሌላ በር ወጥታ ተከትላ ለማየት ወደ እዳራሹ ገባች ።

ሽዋርካብሽም ተናዳ ፥ “የት እባቷ ቆይታ ነው በዚህ ብቅ ያለችው ። ከውካዋ ጥላ ቢስ ። እንግዲህማ ቤቱን አዝላው ሔደች እያለች ስታወራ መክረሟ ነው ። ልፊ ብሏት ነውዴ እስተዛሬም ያደረሰችላቸው ወሬ በቂያቸው ነበር” ብላ ገሠገሠች ።

እፈሣ ከመንገድ ውጪ ጉብታ ላይ ተቀምጦ አሻግሮ አይቷታል ። እሷ ፈጥና ለማድረስ ፥ እሱ ቶሎ ተቀብሎ የሚድሔበትን ሳያሳውቅ ለመሔድ በየበኩላቸው ቸኩለዋል ።

ወደ መንገዱ ገባ ብሎ በርጋታ ተቀበላት ።

“የቴዋን ነገር ታኢዋለሽ ፥ እምንገድም የቆየሽ አይመስላት ፥ በያ ላዩን በብሳናው ጋ አቋርጠሽ ሒጂ” ብሎ ከካባቢው እስከትርቅ አይዞሽ እንደሚል ሰው ቆሞ ፥ ባይኑ ሸኛት ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፥ እልፍኝ ገብተው ነጭ አጉዛ እተነጠፈበት ድንክ አልጋ ላይ እንደ ተቀመጡ በውጥናቸው መሳካትና አለመሳካት እየተርበተበቱ መላ አካላቸው ይንዘረዘራል ። ተስፋና ሥጋታቸው ግብግብ ገጠሙ ። ሐሳባቸው ሁሉ ፥ ዐውሎ ነፋስ እንዳነሣው ትቢያ ይበተንባቸዋል ።

ቀኛዝማች እዚያው እልፍኝ ውስጥ በግድግዳ እተከለለው ክፍል እንቅልፋቸውን ይለጥጣሉ ።

ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፥ “ይኸ ጠንቀኛ እንዳመሉ መንገድ ቀይሮ በሌላ ጋ ይሔድና ያጡት ይሆን ? ወይ ደሞ እጉል ይስቱ ይጨርቆትና ጉዱ ይንተከተክ ይሆን? ቢሳትስ ማ ተኩሶ እንደ ሳተው ይታወቃል ?” በማለት በሐሳብ ይባዝኑና ፥ “የኔ ጎርጊስ የት ሔዶ ? የዛሬንማ የልቤን አድርሶ ካላወጣኝ — —” በማለት ይሳላሉ ። እንደገና ደግሞ ውስጣቸው የብትንትን ሐሳብ ሜዳ ይሆንና ፥ “እስቲ እማ ልሳሳተዋ ሴትዮ እንዲህ ልሳሳት ፥ ያንዳንድ ቀን ፍርጃኮ እቤት አይውልም” በማለት ከንፈራቸውን እየነከሱ በሥጋት ማዕበል እየታመሱ



ተከዙ ። ባለፈው ጊዜ አገልግሎቹን በድብቅ ያቀበሉት እሳቸው ራሳቸው ነበሩ ። ዛሬ ግን ፥ በሸዋርካብሽ በመላካቸው ተጨነቁ ። ጥርጣሬአቸውም ነፍስ ዘርቶና አካል ገንብቶ ከፊታቸው ተገተረ ። “እንዲያው እኮ ነው መሥጋቴ ፥ እንዲህ አለ ስርፋ ሔደህ አገልግሉን ስጥልኝ ብላ ሃለች በይ አላልኳት ። ይኸነዬ በሷ ቤት ቀላ መውረዱ ይመስላታል ። ምኑን ተምኑ እያይዛ ትጠረጥራለች ። ‘ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም’ የሚሉት ቢጤ ሆና ነውዴ” በማለት አንዱን ሥጋት በሌላ ምክንያት እየሻሩና ፥ አንዱን ጥርጣሬ በሌላ ሰበብ እያስወገዱ የሐሳብ ድሪቶ ሲደርቱ ነፍሳቸው ተንገላታች ።

*   *   *

ምንዳዬ የቀረበለትን እንጀራ ሲበላ ፥ ልኬለሽ ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ ዐልፎ ፥ ዐልፎ ወደ አፉ ትላለች ። መብላቷ ሳይሆን ማባሳቷ ነበር ።

“በወጉ ቀረስ እያደረግሽ አትበይም ወይ? የምን ለኮፍ —ለኮፍ ነው ።”

“እኔ ያለሁት እገዛ ቤቴ ፥ ይልቅዬ አንተ እሰው ቤት እምኬደው ደህና አርገህ ብላ ።”

“እኔ በቃኝ ታላልኳቸውስ ፥ ለሞተ እህል አይነፍጉኝም ፥ ለዚህስ — —”

“ቢሆንም ስንቅን ይዞ ነው መግደርደር — ብላ ብየሃለሁ” ብላ ወ/ሮ እልፍ — ይከንዱ በደህናው ቀን በሰጧት ውጪ — ሰማያዊ ፥ ውስጠ — ነጭ መጨበጫ የለሽ ጭልፋ ወጥ አወጣች ።

“እዚያም ቀኛማይ ጋ ትንሽ ወራውሬአለሁ ልኬ ።”

“የሳቸውን ተወው ። ያን ዐሥሬዬ እየተሰቀከ እምበላውን ነው ? ያን መብል አበለው ።”

“እሱንማ መች አጣሁት ! — —አሁን ግን ጠግቤአለሁ ልኬ” አላት ።

“እስኪ ሙች በለኝ ?” አለችው እየሣቀች ።

“እኔ ልሙት !”

ጠቀም ያለ ጉርሻ ጠቅልላ ብድግ አለችና ፥

"እንካ በል ይቺን!"

"ልኬ ሙች ጠግቤአለሁ ፣ ለማ ብዬ ነው በገዛ ቤቱ" አላት አሻቅቦ እያየ ።

ግላውን ለማፍረስ ከጉርሻው ላይ በጥቃ በልታ ፣ "በል ይኸው ለማላው ያክል ቀምሻለሁ" ብላ አፉ ላይ ደቀነችለት ። ጎረሰ ። ያን እላምጦ ከመዋጡ ደገመችው ። ገበታውን አንሥታ ካስታጠበችው በኋላ ዝናሩን ታጥቆና ጠበንጃውን ይዞ ተነሣ ።

እጅዋን ያዝ አድርጎ ፣ "በይ እንግዲህ ልሒድ ፣ ትፈራላችሁ እንዴ?" አላት ብዙ ጊዜ ተለይቷት ያልሔደ ይመስል ።

"ደሞ የምን ፍርሃት አመጣህ? እንኳንና ዛሬ ያንዬም አልፈራሁ" አለችው በልበ ሙሉነት ። በአድናቆት ትኩር ብሎ አይቷት ወጣ።

የበሯን መቃን ተደግፋ አየችው ። የፈገግታዋ ብርሃን ፣ የውሃ ፍንጣቂ እንዳረፈበት ጢፍ ተጭለመለመች ። እጁን ስታስታጥበው የያዘቻት ሽክና አፏ ቁልቁል ተደፍቶ ውሃዋ ተንጠፈጠፈ ። አንገቷ ሰበር ሲል እንባዋ ዱብ —ዱብ አለ ። ከመቼው ዐርፌ እያለ ሲጓጓ እንደ ገና መንገድ መግባቱ አበሳጫትና ፣ "ዋ! ኑሮ ሆዬ!" ብላ ቀና ስትል ፣ የአጥሩን በር ከፍቶ ሲወጣ በእንባዋ ግርዶሽ አየችው ።

* * *

አፈሣ ፣ ከሣር —እምባ በስተደቡብ አመሪት ግራርን ዐልፎ እግድም አሽቀልቁሎ ከወረደ በኋላ ሽፍታው ካደፈጠበት ቦታ ገንዳ—ውሃ ደረሰ ። ሁለቱ የሚተዋወቁባትን ሦስት ጠጠር ወደ ጢሻው ወርውሮ የመምጣቱን ምልክት አሳወቀው ። በተጨማሪም የሚያወዛውዛትን የአባሎ መለሎ ዛፍ ከነቀነቀ በኋላ ፣ ጉበጥ ጉበጥ እያለ ተጠጋ ። እንደ ደረሰም ጉዳዩ እንደ ተሳካለትና ሐሳቡ እንደ ሠመረለት ሰው ዐቅፎ ሳመው ።

"እህ ! ምን ነገር ተገኘ ?" አለ ሰውዬው ግራ ገብቶት ።

"እንደ ቦይ ውሃ ሰተት ብሎ መጣልሃ !" አለ በዝግታ እየሣቀ ።

"ከሆነ አይቀር እንዲህ ነው ። ከማን ጋ ነው ፣ ብቻውን ነው ?" አሉ ከወደ አንገቱ መዘዝ ከወደ ትከሻው ሰግደድ ብሎ በደስታ ።

"ብቻውን ነው ጥይት እንዳበረረው ድኩላ ! አገልግሉን ፍታና አንድ ሁለቱዬ ጉረስ—ጉረስ አርግ ፣ እስተዚያ እኔ እጠባበቃለሁ ።"



"አሁን የመብሉን ነገር ተወውና ፣ ፊትና ኋላ ነበራችሁ እንዴ?"

"እኔ ቀደም ብዬ ነው የተነሣሁት ፣ ከኔ በኋላ ብዙ ሳይቆይ አይቀርም ፣ አጉል ደሞ ያየኝና ይገነግናል ብዬ ነው ስሮጥ መምጣቴ" ብሎ ውሽቱንም ቀደደው ።

አገልግሉን ፈትቶ ለቅምሻ ያህል ሁለተዬ ጉርሶ አቀረበለት ። ሰውዬው በችኩታው የሚተግመንና ባነጣጣሪነቱ የሚመካ ስለነበር ሙሉ አካሉ በንቀት ተዝናንቷል ። "ያውም እንዲህ አድፍጬና የተመቻቸ ቦታ ይዤ — አይይ ! ሰው ያየህ እንደሁ ነገሩ ይበላሽብኛል ባይሉኝ ኖሮ ፣ እኔ እእ ነበር" ብሎት ነበር አፈሣን ።

የማድፈጫው ቦታ በሰውዬው ቁመት መጠን እንደ መደብ ተደልድሎ ፣ ቅጠላ ቅጠል ተጐዝጉዞበታል ። ዙሪያው ፣ በቀንጠፋ ፣ በአጣጥ ፣ በመዛዝኘና ቀጋ ተቸምችሟል ። ከወደ መንገዱ ሆኖ ለሚመለከት ፣ ጢሻው ውስጥ ምን እንዳለና ምን እንደሚደረግ ፈጽሞ አይታይም ። ማድፈጫው ከመንገድ በታች ስለነበር ፣ የልብን ሠርቶ ቁልቁል ለማምለጥና ሌላ ውድማ ውስጥ ለመሽንጥ አመቺነት አለው ። ሰውዬው በተረጋጋ ሁኔታ እየጐረሰ አሻግሮ ሲመለከት ፣ አፈሣ በሆዱ ተኝቶና እግሩን አንፈራጦ እያነጣጠረ ጥበቃውን ቀጠለ ። በአፈ—ሰፊ ቁምጣ ሱሪው ውስጥ ብቅ ያለው ጠምዛዛ ታፋው እተጋደመ ሙቀጫ አፍ ውስጥ የገባ ዘነዘና ይመስላል ። እንደ ትላልቅ እሎሎ ቁጭ — ቁጭ ያለው ባቱም በጉልህ በሚታይ የደም ሥርና ጅማት ተወጣጥሮ ተከቧል ። ሽቅብ ያንጋጠጠው የተረከዙ ንቃቃት የተበነጣጠቀ የእንጨት ቅርፊት መስሏል ።

"እስታሁን የት እሚደርስ ይመስልሃል ?" አለ ሰውዬው እያላመጠ ።

"እንዲህ አሳብ ያለው ሰው መስሎሃል! —ታልመሰለው ፣ ሲቆነን ባየኸው!"

"ለነገሩስ ባለ ዶቃ ኖራለች" አለ ንቀትን በሚገልጽ አኳኋን ።

"አሁን ነው የወደቀ ዛቢያ የመሰለውዬ ፣ ላመት ይሁን ለመንፈእ ያክል ያንተ ቢጤ እኮ ነበረ ።"

"ኧረ ወዲያ ! ወንድ አይመዘን ! ዋ ልብ ሆዬ ! ይኸን መግቢያ ቀዳዳ እያጣ ሙጥኝ እያለ የመጣውን ሁላ እኩል አርገዋ ! አለማወቅ እኮ ጣጣ ነው ።"

"እየህ ላይስ እውነት አለህ ። ስንቱ እንቶጭ እወንዶች መኻል እየገባ ወንድ መስሏል" አለ ምንዳዬን ለማናናቅ ።

"እንዲህም ብልህ ፣ ሜካ የቀመሰና ጨለማ ለብሶ ያደረ ሰው ፣
የዋዛ ሰው እንዳይመስልህ ። ምንም ቢሆን ልቡ ቶሎ አይበረግግም"
አለ በሰበቡም ራሱን ከፍ አድርጎ ለማሳየት ።

አፈሣ የሚመልሰው አጥቶ ጸጥ አለ ። ሰውዬው የቻለውን ያህል
በላና ፊቱን ወደ ምሥራቅ አዙሮ ተቀመጠ ።በትዕቢት ያበጠው ልቡ
ምንዳዬን ከመጤፍ አልቆጠረውም ። አፈሣ ከሆነለት ብቻውን አለ
በለዚያም ተደርቦ በመተኮስ 'የገደልኩት እኔ ነኝ' ለማለት ያውጠ
ነጠው ሐሳብ አብሮት አድፍጧል ። ቢሆንም ፣ ሰውዬው ፣ 'ሜካ የቀመ
ሰና ጨለማ ለብሶ ያደረ ሰው የዋዛ እንዳይመስልህ' ብሎ የተናገራት ነገር
ደግሞ ፣ በሐሳብ እየታየች ስላስፈራራችው ፣ ሐሞቱ በሥጋት ተበርዛ
ያቺው ወኔው በረገገች ። ምንዳዬ ከሰው ጋር ተጣልቶ ሲደባደብ ፣
የዱላ አሰነዛዘርና ድፍረቱን ፣ ከሱም ጋ አብረው ቆላ ወርደው ሳለ ፣
ድኩላውን ባንድ ጥይት ሲያስቀረው ተመልክቷል ። ይኸ ሁሉ ታየ
ውና ውስጡ በረዶ ሆነ ።

"ና በል እንግዲህ ቦታዬን ልአልኝ ፣ አንተ ገበሬ ነህ አዝመ
ራውን አሽቀልቁለህ እይ ። እኔ ደሞ ቃታዬን ጨብጬ ልጠባበቅ ።"

"ኧረ ተው አትናኤኝ ፣ እኔም የዋዛ ሰው አልምሰልህ ።"

"ደሞ ምኑን አመጣህብኝ ፣ እኔ የንኤትም አዶል! ሰው እንዳዋ
ዋሉ ነው ብዬ ነው ። አሁን ለማናቸውም ቅንጭላክን ደፈቅ አርግ"
አለ ሰውዬው በትዝብት ።

"አሁን አንኮንህ ለጠፍ ብልስ ? ይበአናል እኮ" ብሎ ቦታውን
ለቀቀለት ።

"እኔ እንዲህ ያለ ነገር አልወድም ። ደሞ ላንድ ልጉኒ ይህን
ያክል ክብርት" አለው ቆጣ ብሎ ።

ሰውዬው ተመቻችቶ ደፈጣውን ሲቀጥል ፣ አፈሣ እጅ እግሩን
ሰብስቦ ምንዳዬ ወደሚመጣበት አቅጣጫ መመልከት ጀመረ ። ዋናው
ሥጋታቸው ግን ፣ 'ምናልባት ከሌሎች መንገደኞች ጋር ይመጣ ይሆን?'
የሚል ነበር ።

* * *

ቀኛዝማች ከእንቅልፋቸው እንደነቁ ፣ እእምሯቸው በሐሳብ
ተዋከበ ። አንዱ ተግ ሲል ሌላው ይተካል ። አብዛኛው ሜካ እንደ
ሚያተራምስ ኃይለኛ ዱደን ስሜታቸውን ያናውጥና የሐሳብ ግርድ



እንኳ ሳይተው ለዘለዓለም ይጠፋል ። የመጨረሻዋ ሐሳብ ግን የዋዛ
አልነበረችም ። እያሯሯጠችና እያዳፋች በእግረ ሕሊና ግጀቴ ይዛ
ቸው ገባች ። ቀስ ብላ አስልታ አመጣጧም ያለ ነገር አልነበረም ።
ለካስ ከነባሮቹ አንዷ ኖራለች ። እንደሚዋደድ ባልንጀራ ተያይዘው
ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ግቢ ዘው አሉ ። ሐሳብና ቀኛዝማች አንድ
አካል ፣ አንድ አምሳል ሆኑ ። ሁለት ፣ አንድ ፣ ሁለት ። መላ አካላቸው
ተንቀሳቀሰ ። የሚላወሰው ተላውሶ ፣ የሚንጠራራው ተንጠራራ ።የስ
ስና ስሜታቸው ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ አመልግሎ ገላ ላይ አንዣበበ ።
ስተት ብለው ጓዳ ገቡ ። ሴትየዋ በውስጥ ልብስ ላይ ነጠላ ጣል አድ
ርገው ጣራ — ጣራውን እያዩ ተንጋለዋል ። ቀኛዝማች ቀስ ብለው
ነጠላውን ሲገፏቸው ፣ "ውይ! ምንድነው እቴ እንዲህ መሆን"
ብለው ግልብጥ ሲሉ ፣ ጠበብ ባለው ነጭ የውስጥ ልብስ ውስጥ ቂጣ
ቸው መንታ የግመል ሻኛ መስሎ ተከመረ ። እንደ ልማዳቸው እጃ
ቸውን ሰነዘሩ ። የተኙበት ያልጋ ዘንግ ሲመታቸው ባነኑ ። ሁለመና
ቸው ነደደ ። ላምሮታቸው ሲሉ አዲስ ውሳኔ ወሰኑ ። አያስችላቸውም ።

"አልሸኘሽኝም ከምትል ሒጂ ብሸኛትስ 'ዓመት ከመነዛነዝ
አንድ ቀን መደባበስ ።' ለምን ቀደም ብዬ ምንዳዬን እንደ ላኩባትም
እነግራታለሁ ። ካሥር መላከተኛ ፣ አንድ ዋና ይበልጣል" አሉና ተነሥ
ተው ሲንጠራሩ በውሳኔአቸው ተደሰቱ ። ፈገግ ብለው ተንጎራደዱ ።
ወጣ ብለው በቅሎ እንዲጫንላቸውም አዘዙ ።

ቸርነትና መታፈሪያ በቅሎ ጭነውና ከእልፍኝ ጠበንጃ አውጥ
ተው ካጥር ውጪ ሲጠባበቁ ፣ ሰውዬው የክት ገበርዲናቸውን ለብሰ
ውና ሽጉጣቸውን ታጥቀው ወጡ ። ወዲያው የሚመለሱ ለማስመሰል
የሚሔዱበትን ቦታ አልተናገሩም ። ሚስትየዋ ግን ጠርጥረዋል ። እን
ደዋዛ ብቅ ብለው የሚሔዱበትን አቅጣጫ ተመለከቱ ። ሁለመናቸው
በንዴት ጨሶ ልባቸው ነደደ ።"እንግዲህ የኔ ነገር ምን መላ አለው ?
ምነው ሞቼ ባረፍኩት "ብለው አቀረቀሩ ።

* * *

ምንዳዬ ፣ ነጠላውን አጣጥፎ ግራ ትከሻው ላይ ጣል አድርጓ
ታል ። ሰደፉን ወደኋላ አዙሮ የጠመንጃውን ማንገቻና አፈ ሙዝ
በግራ እጁ ጨብጦ በእርጋታ ይጓዛል ። በሰማዩ ላይ ደመና ፣ በአካባቢው
አየር ውስጥ ጭጋግ አልነበረም ። ሁሉም ነገር ወለል ብሎ ይታያል ።
ቀዝቀዝ ብሎ በመጠነኛ ፍጥነት የሚነፍሰው ነፋስ ቁጥቋጦውን ሲያም
ሰው ይቆይና ከወደ ተራራው አናት ቁልቁል የሚወዛገዘገው ተባራጅ
ነፋስ ደግሞ ጠንከር ካለ ኃይልና ፍጥነት ጋር እንደ ደራሽ ውሃ ሲከለበስ
በት ሜካውን አንኩሮት ይነጉዳል ።

አፈግ የቁም ሕልሙን ያያል ። በጉራ የተሞላው ሕሊናውና ለመዋሸት የተፈጠረው አንደበቱ ዛሬም እንዴት ተጋግዘው የሐሰት ካብ እንደሚከቡ ይዶልታሉ ። እንዲያውም ፣ እንዴት አድርጎ ምንዳዩን እንደ ገደላቸው ለሴትዮዋ በሐሳብ መሸርከት ጀምሯል ። አገላብጠው ስመው ፣ አመስግነው ሲሸልሙት ይታየዋል ። ከሐሳቡ ሲነቃ ግን ፣ ከውኑ ዓለምና ከፊት ለፊቱ ጢሻ ጋር ይፋጠጣል ። ሐሳብና ድርጊት እንደ ጨለማና ብርሃን ቢጻረሩበትም ምኞቱ እያየለበት ሲገድል እንጂ ሲሞት አይታየውም ።

አጠገቡ በደረቱ ተኝቶ የሚጠባበቀው ሰውዬ ግን ፣ ምንጊዜ ምንዳዩ ብቅ ብሎለት ፣ ወይ ጭንቅላቱን ፣ ወይ ደረቱን ብሎ ብረቱን ለመግፈፍ ፣ ትኩር ብሎ እያየ በጉጉት አነጣጥሯል ።

ጀምበር ከመጥለቋ በፊት የምንዳዩ ሕይወት መጥለቅ አለባት ። እስከ ዛሬም ውላ በማደሯ ተናዷል ። የወይዘሮ እልፍ ይከንዱ እምቢታና ሥጋት እንደ ግምብ አጥር ተደንቅሮ ባያስቸግረውማ ኖሮ እዚያው ሣር አምባ ከቤቱ በታች ደንገዝገዝ ሲልለት ፣ የልቡን ሠርቶ ዘወር ለማለት አስቦ ነበር ። "ኤዲያ ! ላንድ ለማይረባ ሰው ይህን ያክል ሽብ—ረብ ፣ እዚያው እገዛ አጥራቸው ሥር ጅብ የዘነጠለው አህያ አስመስዬው እምሒደውን አጉል አጉላሉኝ" ብሏል በተደጋጋሚ ።

ነፋሱ ቀስ — በቀስ ተግ ፣ አካባቢውም ጸጥ አለ ።ፀሐይ የተራራ አናት እየላሰ የሚያልፍ ጨረሯን ወደ ቅርፀ —ቆሬው ሚዳማ ቆላ አሻግራው ፣ የገንዳ ውሃ ሸለቆን የከላይ ተራራ ጥላ ጥሎበታል ።ሁሉም ነገር ይታያል ።

ሽፍታው ድንገት አካላቱን ነዘረው ። ንቃቱም የልብ ምቱም ጨመረ ። እንደ መሸበርም ፣ መርበትበትም ቃጣው ። ግንባሩን ከስክሶ ትኩር ብሎ ተመለከተና ፤

"እስኪ ና ! እስኪ ና !" ሲል አፈግ ከሐሳቡ ባነነ ።

"ምነው? መጣ እንዴ ?" አለ ፣ ራሱ ማየት ሲችል ወዲያው ሐሞቱ ፈስሶ ።

"እስቲ እሱ መሆን አለመሆኑን አረጋግጥልኝ"አለ እንዳነጣጠረ ።

አፈግ በጭላንጭሉ ውስጥ አሾልቆ ተመለከተና ፣

"ነው! እሱ ነው!" አለ እሱም ጠመንጃውን ይዞ እየተጠጋ ።

"በል ተፀው! አንተ ገለል በል!" አለውና አካላቱን ነቅንቆ ፣ ጠበንጃውን ተከልከለ ፣ አንድ ዐይኑን ገደል ፣ እግሩን ፈርከክ አድርጎ ተመቻቸ ።

ምንዳዩ ወደ ተነጣጠረበት አፈ ሙዝ አቅጣጫ ጉዞውን ቀጠለ ።



## ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ከገንዳ ውሃ ሸለቆ የሚመጣላቸውን መልስ በጉጉት እየጠበቁ ፣ ሳይታወቃቸው ከላይ ቤት ታች ቤት ያደዘድዛሉ ። አእምሯቸው በጭንቀት ተወጥሮ ሊተረተር ፣ ልባቸው በተለዋዋጭ ምት ልትፈነዳ የተቃረበች መሰለች። የምንዳዩና የባለቤታቸው በቅደም ተከተል ፣ ያውም ባንድ አቅጣጫ መሔድ ተምጦ የማይወለድ የብስጭትና የሥጋት ፅንስ ሆነባቸው ። የሚያማክሩት ሰውና የሚጽናኑበት ሐሳብ አጡ ። ወለሌ ሆነ ። የመቃብራቸው ጉድጓድ አፉን ከፍቶ ታያቸው ። ይደርሳል ብለው ያላሰቡት አሥጊ አጋጣሚ ዙሪያውን አጠራቸው ። አንዳች ድምፅ ከሰሙ ፣ ወይም ከሁለቱ የአጥር በሮች አንዱ ከተከፈተ ነፍሳቸው ተብረክርካ ጆሯቸው ይቆማል ። ገቢ ወጪውን እያሳቀሉ ይራገማሉ ። ሥጋታቸው እየጨመረ ፣ ተስፋቸው መነመነች ። ያችኑ ያዩዋታል ። በመኻሉ ደግሞ በሥውር የሸረቡት ትብትብ ተጋልጠ "አሄሄ! እኛ በሰው ነገር ምን ዶለን ብለን ነውዬ ፣ ሥራይቱንማ ማ እንዳሠራት መይ አጣናትና ? አሁንማ ምን መላ አለው ! እሱ ቀን የጎደለበት ፣ አገሩን ጥሎ ፣ ቁርበቱን ጠቅሎ የወጣለት" እያለ ሣር ቅጠሉ የሚያጋልጣቸው መሰላቸው ።

"ምነው በቀረብኝ እቴ ፣ እስቲ ሞልቶ ከተረፈ ትዳሬ ላይ ምን ጐደለብኝ? እቤት ያለው ፣ እጁር የበቀለው ሁሉ የኔ — — ለማንም ድብኝት ቂጥ ጋለሞታ እንዲህ መሆኔ ለማ ብዬ ነው ። ለምን እበእጇቸው ላይ አፈናጠዋት አገር — ላገር አይዞሩም ! የዋህነቴና ተይባይ አጥቼ ነው ። እሱም ቢሆን በሎሌነቱ ያው እሳቸው አርግ ያሉትን ያረጋሊ ፣ እምቢ አይላቸው" በማለት ይጸጸታሉ ። መውጫ ማምለጫ እንዳጣ የዱር ዐውሬ ባጥሩ ዙሪያ እየዞሩ "እህህ!" ይላሉ ። ቀደም ሲል ተወልዶ ለአካለ መጠን የደረሰው ሐሳባቸው ራሱን ችሎ ገንዳ ውሃ ከሰዎች ጋር አድፍጧል ። አሁን ያንን ውጥን ማሰናከልና ያንን ጥይት ማምከን አይቻልም ። የተሰማ ነጉድጓድ ፣ የተለቀቀ ናዳ ሆኗል ።

እልፍኝ ገብተው ዐረፍ ሲሉ ደግሞ ፍርሃትና ጸጸቱ ፣ የማሰላሰያ ዘዴውም ደብዛው ይጠፉና እንደ ቂል በዘፈቀደ ሲያስቡ ፣ "ኧረ ይታባቱ! እንዳተከነኝማ ካላተከንኩት ሙቻለሁ! እኔ ነበርኩ ስንቱን ቀባጥሬና ይሁን ይሁን ብዬ ለዚህ ሁሉ ወግ ያበቃሁት ። ካፍ —ካፉ

ከሳቸው ፥ ከሆድ ከሆዱ ከኔ ጋ ቢሆን አይቀዉኝም ነበር ። እየሁ በየሁ ሆነን ፥ ቲመቸው ቲመቸው ደበቅ እያለ ነገረ ሥራቸውን ቢነግ ረኝ ኖሮ ፥ ለዚህ ሁሉ አንዳረስም ነበር ። ኧረ ይታባቱ ይኸ መናጢ!" ይሉና ከንፈራቸውን ይነክሳሉ ።

ከምንዳዬ ጋር የጀመሩትን ግላዊ ግብግብ በራሳቸው አሸናፊ ነት ሲደመድሙ ደግሞ ፤ ቀጥ ያለ ዳገት ወጥቶ እንደሚያርፍ ሰው ብረጂሙ ይተነፍሳሉ ። ተለዋዋጩ ስሜታቸው ወስድ — መለስ እን ደሚያደርገው ሰው አቅበጠበጣቸውና ሳያስቡት ወደ ምንዳዬ ቤት አመሩ ። ከበሩ ትንሽ ራቅ ብለው ፥ "ልኬለሽ! አንቺ ልኬለሽ!"አሉ በነኮትኳታ ድምፅ ። መልስ አላገኙም ። እንደገና ሲጠሩ ልኬለሽ ብቅ አለች ።

"ውይ! አለሽ እንዴ? ምነው ይህን ያክል ስጣራ ዝም ማለትሽ ልጄ?" አሉ በኩራት ቢጤ ።

"አልሰማሁሁም ነበር ። ልጆቹ ናቸው እማማ ይጣራሉ ያሉኝ" አለች እበሯ ላይ ቆማ ።

"ምነው ዛሬ ወደኛ ቤት ብቅ አለማለትሽ ልጄ ? ለእንዴት ዋላችሁንኳ?" አሉ ጠጋ እያሉ ።

"መጥቼኮ ነበር ፥ አላየሁኝ እንደሁዬ — —" አለች አንገቷን ሰብራ ።

"ነው? ልብ ባልልሽ ነው ። የቴዴ ባልሽ ? ምነው አላየሁት?" አሉ ትኩር ብለው እያዩዋት ።

'እኝህ ሴትዮ እያደር መለተቱ ልበል ፥ እዚያው አጠገባቸው ቲመላለስ ውሎ ምነው አላየሁት እሚሉ ነገርን ምን አመጣው' አለችና በውስጧ ፥

"እሳቸው — — " ከማለቷ ።

"ላኩት እንዴ ?" አሏት ካፏ ልፈው ።

"አሁን መጣሁ ብሎኝ ነው ወጣ ያለው ፥ ቢልኩት ነውዬ ወዴት ይሔዳል?" አለች የባለቤቷ አጣብቂኝ መግባት ልቧን ከፉኛ እየጨመቀው ።

አእምሯቸው ምላሳቸውን መቆጣጠር ያተወ መሰለ ።

"ቆዬ እንዴ ተወጣ?"



ነገሩ ካልጣማት ልቧ የሳቸውን ያህል ክፋት ሊጠነስስ ቢች ልም ፥ አትተናኮልም ።

"ዋኢት ቆየት ብሏል" አለች ፥ 'ደሞ ተመቼ ወዲህ ነው ይኸ ሁሉ ጠጋ — ጠጋ' ብላ በልቧ ።

"እሰው ጋ እልከዋለሁ ብዬ ነበር — —አሁንማ መሸ — — ባይሆን ነገ" አሉና ዝም ብለው ቆሙ ። የቤትዬዋ ዝም ብሎ መቆም ልኬለሽን አስጨነቃት ።

ከሚያዋክባቸው ጥርጣሬና ሥጋት መካከል አንዱን እንኳ በዘዴ ለመገላገል ፈልገዋል። ረመጡን በገለባ እያዳፈኑ ፥ ሸንቁሩን ጋን በአሸዋ ቢመርጉት የሚሆን ይመስላቸዋል ። ነፍሰ — ሥጋቸው ተባዘተች ።

"አንቺ ልኬለሽ?" አሏት ቤተሰባዊ ስሜት ባለው ቃና ።

"እመት!" አለች ፥ 'የዛሬውስ የጉድ ነው' እያለች በሆዷ ።

"ከዛሬ — ነገ እነግርሻለሁ ስል ፥ እርስት አረገዋለሁ — — የዘንድሮ ልብ ልጂ . . ."

"ምኑን?" አለች ነቃ ብላ ።

"እንግዲህ እኮ እሰው አገር መሔዴ ነው ።"

"ወዴት?" አለች ዐውቃ ።

"አዲሳባ ነዋ! ባርላማ መሾማቸውን መቼም አቀሻል ፥ እሳቸው ቲሔዱ እኔ እንዴት ብዬ እቀራለሁ ። አልሔድም እንዳልል ነውር ነው ። ሰጪስ ምን ይለኛል ! ለኔማ እየሁ እሞቀ ቤቴ ይሻለኝ ነበር ። እና ይኸውልሽ ደህና ባለሙያ ጥፍፍ ያለች ሰው ባወጣ — ባወርድ ፥ ባወጣ — ባወርድ — —ስንቱን አስቤ ፥ ስንቱን ተመኘሁት መሰለሽ — — ቀልቤ ታዲያ ዞሮ ዞሮ ያረፈው አንቺ ላይ ነው ። ከማይረባ አጉል ዘመድ ደህና ባዳ ይሻላል ። እንዲያው ነው ፤ ዘመድ ፥ ዘመድ እምንለው ፥ ምኝነታችን" አሉና ትኩር ብለው አዩዋት ። ለይስሙላ የፈገጉት ፈገግታ ግን የቁም ሞቱን ሞተ ።

"አ — ይ! እኔ ታዲያ ወዴትና — ወዴት ፥ ምንና ምኑን ዐው ቄው ! እኔ ለራሴ ማጀቴ እንኳ ትሔድ መላ — ቅጡ ይጠፋብኛል ፥ እዚያማ ሔጄ መሣኢያ ለመሆን ነውዬ ምን አጠምኋለሁ ። ለዚያ ውስ ማቲዎቼስ ?" አለች የምትመልሰው ጠፍቷት ።

"እኔማ እዚህ ብቻሽን ከምትንገላቺ እዚያው ከባልሽ ጋ ይሻ ልሽ እንደሁ ብዬ ነዋ ! ሰውማ መች አጣሁ ፥ ጫማዬን ስመው ባይለ

ምኑኝ ነው ። እኔም ያለ ባልሽ ሌላ ሰው ይዘሁ አቴዱም ብዬ ማለቱ ላንቺ ብዬ ነበር” አሷት ገራገር ልቧን ለማግለል ። በልቧ ማቀችባቸው ፣ ‘የዚሁ አነሳቸውና ፣ ከነባሌ እሰው አገር ወስደው ሊያንገበግቡኝ ፣ የሱም ሆድ—ሆዴን እየበላኝ ነው ። መላው ጠፍቶኝ’ ነው እያለች።

ዝምታዋን አይተው ፣ “እንግዲህ ተሱ ጋ ተማኽሩበት ፣ በኔ በኩል የውዴታዬ ወጥቶልኛል” ብለዋት እንደዋዛ ተመለሱ ። እሷም አትነግረው ፣ እሳቸውም እንደማትነግረው ያውቃሉ ።

* * *

ምንዳዬ ረጋና ነቃ ባለ ስሜት በወጣ ገባው ጠመዝማዛ መንገድ ጐንበስ ቀና ፣ ዘንበል ጋደል እያለ ሲጓዝ ፣ ድንገት ያጋጠመውን ውሃ የሸረሸረው መሬት ለቆ ወደ ሌላ ወገን ለመሻገር እመር ሲል ግራ ክንዱ ላይ በጥይት ተመታ ። “ዘራፍ ምንዳ ገላግሌ !” ብሎ መለስ እላለሁ ሲል ተደገመ ። ምድርና ሰማይ ዞሮበት ወድቆ ተንከባለለ ። በቦታው ተፈጥሯዊ ዘቅዛቃነት ታግዞ የሞት — ሞቱን ተንሸራቶ ከመንገድ በታች ትንሽ ቦይ መሳይ ፈፋ ውስጥ እግሩን ቁልቁል ዘርግቶ ተወሸቀ ። ደንግጧል ። ፈርቷልም ። የሕይወት ጉዳይ ሆነና ከመሬቱ ጋር በደረቱ ልስቅ ብሎ አደፈጠ ። ከየት እንደ ተተኮሰና እምኑ ላይ እንደ ተመታ’ንኳ አላወቀም ። ደሙ ብብትና ግራ ጐኑን እያራሰ መንቆርቆር ጀምሯል ። እንደምንም ድንጋጤውን ውጦና ባወጣ—ያውጣኝ ብሎ ይሔድ ወደ ነበረበት አቅጣጫ አነጣጠረ።ሽፍታው ቃታውን ጨብጦ ጐንበስ ጐንበስ እያለ ከጐዘጐዘበት ጢሻ መሰስ ሲል ፣ “ወይ ነዶ! ጥኢት ጠጋ ቢልልኝ ጥሩ ነበር” አለ ዞሮ እስከሚሔድ የነበረው አንድ መቶ እርምጃ ያህል ርቆበት ። ሽፍታው ጠበንጃውን ለማፈፍ አካባቢውን እየተንቀዠቀዠ ሲመለከት ፣ ምንዳዬ ካደፈጠበት ሆኖ አንድ ጠበንጃውን ደግኖ እያሰላ የሚመጣ ሰው አየ ። ማንን እንደሚፈልግ ገብቶታል ። አቅሙ እየደከመ ጡንቻው ቢዝልም ፣ ወኔው በቁጣ ነደደ ። ዐይኑ ተጎለጎለ ። አነጣጥሮ በደረቱ ለቀቀበት ። “ዘራፍ አባመንጥር!” ብሎ ወደ ፊት ጐንበስ ሲል ምንዳዬ ሁለተኛዋን ጥይት በርግብግቢቱ ለቀቀበት ። ጠበንጃው ተሽቀንጥሮ ባፍጢሙ ተደፋ ። እዚህም እዚያም ጻዕር ሆነ ። የምንዳዬ አቅም ተጠነፈፈ ።

“ወይኔ ምንዳ! ጠላቴን ሳላውቀው መሞቴ ነው” ብሎ ጠበንጃውን ከሞት በኋላም ይገለገልበት ይመስል ከንፈሩን ነክሶ ብረቱ ላይ ተደፋ ።

አፈሣ በርከክ ብሎ በጭላንጭል አየ ። ነገሩ ተበላሽቷል ። ልቡ በፍርሃት ቀዘነ ። እንጀቱ ተንጫረረ ። “ምን ይብጀኝ ! ምን ልሁነው !



እንጃለቱ ይኸ ነገር” አለ መላ አካላቱ እየራደና ከፋኛ እየሠጋ ። ውስጥ—ውስጡን ሲሸረከት የዋለው አንደበቱ ፣ ደፍሮ ለመፈጸም ከራሱ ጋር የገባውን ቃል —ኪዳን የፍርሃት ውኃ በላው ። ዙሪያው ገደል ሆነበት ። ‘ብትጠየቅ እንኳ እኔም ተኩሼ ነበር ትላለህ’ብለው ሹክ ያሉት ይመስል እና ፣ በተጨማሪም በአካባቢው ‘ሌሎችም ሰዎች አሉ’ ብሎ ምንዳዬ ይፈራ ዘንድ ፣ አንድ ጥይት ወደ ሰማይ ተኩሶና ጠበንጃውን አንጠልጥሎ ቁልቁል ፈፋ — ለፈፋ ሽሽቱን ተያያዘው ።

አካባቢው ጸጥ አለ ። ሩብ ሰዓት ያህል እንዳለፈ ከወደ ማጀቱ የመጡ ሦስት ሰዎች ተኩስ ከተሰማበት ገንዳ ውሃ አካባቢ እንደ ደረሱ ፣ አንዱ ባለ ብረት ጥይቱን አቀባብሎ ፣ ሁለቱ ዱላቸውን በጥንቃቄ ጨብጠው ዙሪያ ገባውን እየቃኙ መንገድ ቀጠሉ ።

“ይኸ ደም የለመደ ቦታ’ኮ አይታመንም”አለ አንዱ ዙሪያውን እየተመለከተ ።

“ምናባቱ ቢለምድ! ሞት የሸተተው ከመጣም ያው ነው” አለ ሙክ ብሎ ሌላው ለማደፋፈር ። እንዲህ እንዲህ እያሉ ሲሔዱ ፣ አንድ ሰው እግሩ ተንጨፍሮ ፣ ባፍጢሙ ተደፍቶ ደሙ እባብኛ ሲፈስ ተመለከቱ። ፊታቸውን ከስክሰው ግራ ቀኛቸውን እየቃኙ ተከታትለው ተጠጉት ።

“እምኑ ላይ ጣለን ወንድሜ” አለ አንዱ ፣ ወደ ወደቀው ሰው እያየ ።

“ገዳዮቹ ሳይሸሹም አይቀሩ” አለ የመጀመሪያው ።

“በኋላ ላይ የሰማናት ጥይት የመሔጃ ሳትሆንም አቀር” አለ ሌላው ።

“ምን አገናኝቷቸው ይሆን ? መገን የኛ አገር ሰው —— በሚረባ በማይረባው ሁሉ . . .”

“እንዲያው ማ ይሆን? የኛ አገር ሰው ይሆን ይሆን?” አለ ሦስተኛው ።

“እንዴት እንወኸው ፣ ባፍጢሙ ነው የተደፋው?” አለ መላሹ።

ምንዳዬ እንደ ምንም ከራሱ ቀና ብሎ ሰዎቹን ሲመለከት ፣ የሚያውቀው የሣር — እምባ ሰው በማየቱ ፣ “አቶ ጀማነህ”ብሎ በተዳከመ ድምፅ ተጣራ ። አቶ ጀማነህ ደንገጥ አለና ፣ “ማን ነህ ?” ብሎ ጥሪውን ወደ ሰማበት አቅጣጫ ትኩር ብሎ በጥርጣሬ ተመለከተ ።

“ምንዳዬ ነኝ” አለ በታፈነ መሳይ ድምፅ ።

“የማ ምንዳዬ?” አለ አቶ ጀማነህ ግር ብሎት ።

ትንፋሽ አጥሮት ዝም አለና ፣ “የማር — እምባው ፣ የቀኛማይ በላይነህ ።”

“የኛ ምንዳዬ !?” ብሎ አቶ ጀማነህ ወደዚያው ተራመደ ።

“እዎድ” አለው ፣ አግድም አሻቅቦ እያየ ።

አቶ ጀማነህ ወደ ምንዳዬ ሲጠጋ ፣ ሌሎቹ ከልብ ሆነው ተከተሉ ።

“ወይኔ ወንድሜን! ወይኔ ወንድሜን! ለካ የገዛ መከራችን ኖሯል!” ብሎ የጠመንጃውን አፈሙዝ ተመርኩዞ ጐንበስ አለና፣ “ምን ተርፏል ! ተበላሽቶ! ወይ ጉድ !” ብሎ ተጠጋ ።

“ወደላይ አውጡኝ ፣ መውጣት አእቶኝ ነው ።”

ተረዳድተው አወጡና ከወገቡ ቀና አድርገው አስደግፈው አስቀመጡት ።

“ምንድነው ነገሩ ?” አለው አቶ ጀማነህ ከፊት ለፊቱ ቁጢጥ ብሎ ።

“ምናውቄ ብለኸኝ ፣ ውድማ ለብሶ እንዲህ ተጫወተብኚ ፣ እን ኳን አንዱን እንዲህ የሪቅ ድጋፍ አስመሰልኩቲ ብሞትም አይቆጨኝ” ብሎ ዐይኑ ተንገረበበ ።

“አንተ ማነህ ከተማ” አለ አቶ ጀማነህ አንጋጦ እያየ ። “በል አንተ እንግዲህ ገሥግሥ ፣ እኛ እየሁ እየጠበእን እንቆያለን ፣ ቶሎ ሔደህ—ለቀኛማይ ንገር” ። ከሦስቱ ልጅ እግሩ እሱ ነበር ። ‘እኔንም ይተናኮሉኝ ይሆን’ እያለ መንገድ ገባ ።

ሰዎቹ ከምንዳዬ ግራና ቀኝ ትንሽ ፈንጠር ብለው በንቃት ተቀመጡ ። ምንዳዬ “እ!” ብሎ አቃስቶ ዐይኑን በመጠኑ ገለጠና “አቶ ጀማነህ!” አለ በደከመ ድምፅ ። “አቤት” ብሎ በፍጥነት አጠገቡ ቆም እንዳለ ፣ “እስቲ እንዲያው ደስ ብሎኝ እንኳ ብሞት ፣ የዚያን የቡከን ጠመንጃ ወዲህ በልልኝ፣ ሌላው ቢኸር አይቼው ልሙት” አለ ዐይኑ እየቦዘ ። አቶ ጀማነህ ከወደቀው ሰውዬ ፊት አንሥቶ አጠገቡ አጋደመለት ። ፈገግ ባይልም በልቡ ደስ አለው ። ‘አይቆጨኝም ፣ እንዲህ አናቱን ነድዬ ሬሳውን ማየት በቂዬ ነው ። የቅንነት አምላኽ ነውዬ ፣ ይኸን ማንም አይፈጥመው’ አለ በሆዱ ።

*　　*　　*



ቀኛዝማች ፣ ከሩቁ የተተኮሰውን ጥይት እንደሰሙ ፣ “እንግዲህ ደሞ ጠገቡ! ልባቸው አበጠ! አዝመራው ሳይደርስ በቅጠሉ ይጠግባሉ ፣ ሲያጡ መከራ ሲያገኙ መከራ!” አሉ ሽጉጣቸውን እያመቻቹና የበቅሏቸውን ፍጥነት እየቀነሱ ።

ወደ ማር እምባ የሚገሠግሠው መልእክተኛ ከቀኛዝማች በቅሎ እፊት —እፊት ዘከ—ዘከ ከሚለው ከመታፈሪያ ጋር ፊት—ለፊት ተያየ ። መታፈሪያ በሰማው ተኩስ ምክንያት አካባቢውን በጥርጣሬ እየቃኘ ይጓዝ ስለነበር ፣ ከፊት ለፊት እየገሠገሠ ወደ’ሱ የሚሔደው ጐረምሳ አፈጣጠን ስላላማረው ፣ “ቁም ሰውዬ ! ምን ያሮጥሃል!” ብሎ ጮኸበት ።

ወጣቱ ረጋ አለና ፣ “ወይ ያገጣጠሚ ነገር!አትልፋ ቲለኝ እኮ ነው ፣ ምን እግር ጣላችሁና መጣችሁልኝ ፣ የኔም ሩጫ እሳቸው ጋ ነበር” አለ ሰውዬውም እንዲሰሙለት ጮክ ብሎ ። ከመንገዱ ገለል ብሎ እንደ ቆመ አጠገቡ ደረሱና ፣

“እማጋ?” አሉ ፣ ቀኛዝማች ይፈልገኛል ብለው በማይገምቱት ሰው በመፈለጋቸው ተገርመው ።

ወጣቱ ከመንገድ በታች ቆሞ አንጋጦ እያየ ፣ “ጋሼ ጀማነህ አንቱ ጋ ልኮኝ ነው አመጣጤ ፣ ምንገድ ሳይመታኝ እየሁ ተገናኘኒ —— እኔማ ምን ብዬ አስቤው ።”

“የማነው ጀማነህ ? ምንድነው ጉዳው ?”

“ሦስት ሆነን ተወደ ማጀቱ ትንመጣ ፣ እምንገድ ላይ ተኩስ ሰማንና ምንድነው ነገሩ እያልን ስንጠጋ እያሃች ገንዳ ውሃ ፣ ምንዳዬ በጥይት ተመቶ ጢሻ ውስጥ ቲያቃስት አገኘነውና ፣ ‘ቶሎ ብለህ ሔደህ ንገራቸው’ ብሎኝ ወዳንቱ ቤት ነበር አሯሯጤ” ብሎ አንገቱን ሰበር አደረገ ።

“ምንድነው እምትለው? አላወከኝም እንዴ?”አሉ የተሳሳተ መስሏቸው ።

“እንዴ? እኔ መች አጣሁሁ!—ሺ ብሳሳትስ አንቱን አጣኋለሁ እንዴ?”

“እኮ ታዲያ ምንድነው እምትለው? ነገርህ እኮ!”

“እያሃይ ገንዳ ውሃ ምንዳ በጥይት ተመቷል እኮ ነው እምልሁ ።”

“የኔ ምንዳ !!? ማ እባቱ ?!” አሉ ቱግ ብለው ።

“ማ አይቷቸው! ማ እንደሆነ አላወቅንም!”

“እናንተ የት ኖራችኋል?”

“ምነው ተወደ ማጀቴ ትንመጣ ነው ብየሁ!”

“እ—እ! ይቺማ ጥንስስ አላት —— ቆልት ነች! —— በጂ!” አሉ ቀጥል ለማለት ።

“አንዱ ሰውዬ ግን እዚያው ሙቷል!”

“አንተ ለመሆኑ የማ ልጅ መሆንህ ነው?” አሉት እየጠረጠሩ።

“ያስግድ ስቄሺ ?”

“እ—እ! ነህ እንዴ !”

ከቀኛዝማች በቅሎ ኋላ የቆመው ቸርነት በንዴት ብው ብሎ ይቅበጠበጣል ። ‘ንዝዣም የሆኑ ሰውዬ! ምን ያናዝዛቸዋል ፣ ምናለ ቶሎ ብንሔድበት!’ አለ በሆዱ ።

“አሄሄ! እኔ መች አጣኋት! ይቺ ለኔ የመጣች ፣ ለኔ የታሰበችነች! ‘እህያውን ፈርቶ ዳውላውን’ አሉ ። የምቀኝነት ናት ! ለኔ ያሰቧትን ታይሆን አይቀርም!” አሉ ፊታቸው ፍም መስሎ ።

ቀኛዝማች ገሥግሠው ገንዳ ውሃ እንደ ደረሱ ፣

“ምንድነው ነገሩ ጎበዝ?” አሉ ገና ከበቅሎ ሳይወርዱ ።

“ኧረ እኛም ገራ ገብቶናል —— የምን ጉድ ነው እያልን ተጸምጠናል! ቀኛግይ” አለ ጆግንህ በትሕትና አሻቅቦ እያየ ። ሰውየው ከበቅሏቸው ወርደው ምንዳዩን አሽቆልቁለው አዩት ። ሁለመናቸው በንዴት ተንቀጠቀጠ ።

“እናንተ ምንቱ ኖሯል የደረሳችሁት?”

“እኛ ገና እያሄድ ሆነን ነው ተኩስ የተሰማው ፣ ወዲያው ብን ደርስማ ኖሮ . . .”

“የሸፈም ታይኖር አይቀር” አለ ሌላው ።

“እንዴት ?” አሉ በምን ፀወቅህ በሚል አስተሳሰብ ።

“አንዱ ጥይት እንዲህ ተወደታይ የተሰማች መሰሉኛል” አለ ነገር ሳያዞር ።



ቸርነት እንደ ተለመደው ከሰውየው ኋላ ሳይሆን ከፊት ለፊታቸው ቆሞ በደም የራሰውን ጓደኛውን ባዘኔታ አየና ፣ ባፍጢሙ የተደፋውን ሰውዬ በንዴት ተመለከተው ።

“እስኪ ገልበጥ አርገው እንየው” አሉ ቀኛዝማች ። ሁለት ሰዎች ፈጠን ብለው የሞተውን ሰውዬ በጀርባው ገለበጡት ። “ኧኸኸ! ደህና ዋጋውን አግኝቷልና በል! ታዲያ ከምንዬው ፈቱ አበጠ ?”

ምንዳዬ ፣ እነ ቀኛዝማች ከደረሱ ጀምሮ ዐይኑን በመጠኑ ገለጥ አድርጎ ሁሉም ምን ያህል እንዳዘኑና እንደ ተናደዱ አይቷል ። ሟቹ በመዘቅዘቁና ፊቱም በረጋ ደም በመጨማለቁ ፣ ማንነቱን ለመለየት አልቻሉም ። ሁሉም አፍና አፍንጫቸውን በእጃቸው አፍነው ቆሙ ።

“አበጀህ!” አሉት ወደ ምንዳዬ መለስ ብለው ። “ሱሪ ማለት ይቺ ነች! ሌላ—ሌላውን ተዉት ። የዋዛ ሰው መስለኸው ነው አል ሰ ሜ! ወን ! ገድሎ ሊፎክር ነበር አመጣጡማ! ታቀዋለህ እንዴ ምንዳ?” አሉት ትኩር ብለው እያዩ ።

ትንፋሽ ለመሰብሰብ ዝም ብሎ ቆየና ፣ “ቀድሞ ነገር መች ልብ ብዬ አየሁትና !”

“ለመሆኑ ፊት — ለፊት ነው ፣ ሸምቆ ?” አሉ በደም የራሰ ልብሱን እያዩ ።

“ተደብቶ ነውዬ ! ለጥኢት ነው ሚኻል የዋለልኝ ! እንደሱማ አሳብ ቢሆን —”

“አንተ ታዲያ እንዴት አርገህ አገኘኸው ?”

“እኔማ አገር—አማን ነው ብዬ እንደ ልማዴ ተዝናንቼ ትሔድ ፣ እሱ እጢሻ ውስጥ አሾትሎ ሲጠባበኸኝ ነበር መሰል ፣ ሁለተዬ ተኩሶ እንደ መታኝ ነፍሴን ስቼ ተንከባለልኩና እንዳጋጣሚ እየች ውሃ አበ ረቦራት መሬት ውስጥ ተንሸራትቼ ውሽቅ አልኩ ። እንዲያው ፈጣሪ አምላኽ ትረፍ ቢለኝ ነውዬ ፣ በኔ ብርታትም አደል” ብሎ ዝም አለና ፣ “መሞቴን ሊያይ ይሁን ፣ ይቺኑ ጠበንጃዬን ለመውሰድ እንጃ ባቱ ፣ እኔኑ ፍለጋ ጐንበስ — ጐንበስ እያለ ቲመጣ አነጣጥሬ ጠበ ስኩታ ——”

“አጠናቅቃለሁ ሲል ተጠናቀቀና ዐረፈዋ !” አሉ በኩራትና በደስታ እየሣቁ ።

“ብቻውን አልመሰለኝም ፣ እሱ ተወደቀ ወዲያም ሲተኮስ ሰም ቻለሁ ። የዚህኛውን መውደእ ቲያዩ ሸሽተው ይሆናሊ” ብሎ ካንገቱ ዝልስ አለ ።

“ይኸ እዚህ ከወደቀ በኋላ ተኩስ ሰምተህ ከሆነማ ነገር አለ ። እስቲ አንደዬ ገባ በሉና አስሱ ጐበዝ ! አሁንስ አድብተው እንደሁማን ዐወቀ ?” ብለው አካባቢውን በጥርጣሬ እያዩ ሽጉጣቸውን መዘዙ ። ባያስታውቅባቸውም ውስጥ — ውስጡን ሠግተው ነበር ። እዚያው እመንገዱ ዳር ጠፍጠፍ ያለ ድንጋይ አየት አርገው አረፍ አሉ ። መታፈሪያ በቅሎውን እተንዘረፈፈ ቅርንጫፍ ላይ ሸብ አድርጎ በጥንቃቄ ቆመ ።

ሦስቱ ሰዎችና ቸርነት በተለያየ አቅጣጫ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ ጫካው ገቡ ። የሁሉም ልብ ተሰቀለ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አቶ ጀማነህና አብሮት የነበረው ሰውዬ አፈሣና ሚቼ አድፍጠውበት የነበረውን ቦታ አገኙት ።

“እጅሬ ስንቁንም ይዞ ኖሯል በል!” አለ አቶ ጀማነህ ተደስቶም ተገርሞም ። በሚገባ ያልታሰረውን አገልግል ከፍቶ ተመለከቶና ሌላ ተጨማሪ ነገር ያለመኖሩን እንዳረጋገጠ አገልግሉን ይዞ ከጢሻው ሲወጣ ከነቸርነት ጋር ተገናኙና ወደእነቀኛዝማች ዘንድ አመሩ ።

የቀኛዝማችና የሎሌዎቻቸው ዐይን አገልግሉ ላይ ተተክሎ ፣ ‘አንተን ደሞ እዚህ ምን አመጣህ’ እያሉ የሚጠይቁ መሰሉ ። ግራ ገባቸው ። በሦስቱም አእምሮ ውስጥ አንዳች ጥርጣሬ ተላወሰ ።

ከጐራ ጐራ ያስተጋባው የአምስቱ ጥይቶች ድምፅ ዘወትር ከሚሰማው ተኩስ የተለየ ስሜት ፈጥሮ ከያቅጣጫው ወደየቤቱ ያዘግም የነበረውን ያመሪት — ግራር ፣ የሣሊማኖና ኮበኮብ እረኛና ገበሬ ወደ ገንዳ ውሃ አላስኬደውም ። የተኩስ ድምፅ መስማትና እነእከሌ ተጋደሉ ማለት ተራ የዘወትር ነገር ነው ። በዕለቱም ገንዳ ውሃ ተኩስ ተሰምቷል ብሎ ከማጀቴ ሽቅብ የወጣ ፣ ወይም ከአካባቢው መንደሮችና ቤቶች አደጋው ወደ ደረሰበት ቦታ ቸኩሎ የሔደ አልነበረም ። ይልቅስ ከዕለቱ ሥራና ጉዳያቸው በዚያው በኩል ወደየቤታቸው የሚያዘግሙ ገበሬና መንገደኞች አንዳንድ እያሉ በመድረሳቸው ቁጥራቸው በረከተ ። አብዛኞቹ ግን ፣ ማጀቴ የዋሉ የሣር አምባና ያካባቢው ሰዎች ነበሩ ። ሁሉም ደንገጥ እያሉ ተቀላቀሉ ።

“በሉ እንጂ ጎበዝ!” አሉ ቀኛዝማች ፣ በብስጭት የነደደ ዐይናቸው እየተንቀዠቀዠ ። “አንዳፍታ ወረድ በሉና ለቃሬዛ እሚሆን እንጨት ቁረጡ” አሉ ትዕዛዝም ፣ እርዳንም በተቀላቀለበት ሁናቴ ።

ሦስት አራት ሰዎች አብሯቸው የዋለውን ምሳር እንደያዙ ወደ ጫካው ገቡ ።



“ከነዚያ ከባላጋሮቹ መኻል ይሆን ይሆን እንዴ ይኸ ሰውዬ?” አለ ጀማነህ ቀኛዝማች ተቀምጠው እሱ ቆሞ ሬሣውን እያዩ ።

“እኔ ምን ዐውቄ አቶ ጀማነህ ፣ ባይሞትማ ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር —— ትንሽ ፍንጭ ይሰጥ ነበር ።”

“ያገር ልማድ አፍርሰውና ውል ጥሰውማ እንዲህ ታደረጉ የጉድ ነው” አለ በማጋነን ።

“አያረጉትም! አያረጉትም! ካረጉትም ጠባቸው ከማ መሰለህ? ‘ባለቤቱን ታልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ’ ይባላል ። እነሱ ተሆኑ አንናናራትም? ባለጌና ፈሪ ውል አያውቅም ። ይኼ ሰው የዞን — አምባ ሰው መሆኑ ተታወቀ ጉድ ይፈላል” አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

ተጨማሪ መንገደኞች እየደረሱና እጅ እየነሡ ተቀላቀሉ ። ወደ ጫካው የገቡት ሰዎች ወፈር ፣ መለል — መለል ያለ እንጨት ቆርጠው ተመለሱ ። ወዲያው ከየገበሬው በተገኘው ገመድና የመጫኛ ቁራጭ ፣ እንዲሁም መዘው ባመጡት ሐረግ ፣ ቀኛዝማች ፣ ሁለት ቃሬዛ ሲሠራ አይተው ፤

“ሁለት ቃሬዛ ለምናችሁ ነው?”አሉ ።

“ሁለትኮ ናቸው ቀኛማይ” አለ ከቃሬዛ ሠሪዎቹ አንዱ ።

“የማንንም ሽፍታ! ነፍስ ገዳይ ሬሣ ተሸክመን ልንሔድ!! አይ ደረግም! የማንም ጥንብ አንሺ ነን እንዴ ? እሱ እኮ አልቀናውሚ ፣ ቢቀናውኮ ለጅብ ነበር ጥሎት እሚሔደው ።”

“እሱስ እውነትኩን ነው ። እኛ ግን ዐይናችን እያዩ እንዴት ለጅብ ጥለነው እንሒድ? — ነግ በኔኮ ነው ቀኛማይ — ለሱ ብለን ታይሆን ላምላክ ነው” አለ ሌላው ።

“ቢሆንስ! ቢሆንስ! እናንተ ያሁኑን ነው እምታዩት ፣ እሱ እኮ እመጣጡ ፣ ገሎ ለመወርወሪ ለሌላም አልነበር —— ያው ባዝነን እጅ—እግሩን ነበር እምናገኘው ። ኸረ ይታአባቱ !” አሉ ደማቸው ፈልቶ ።

“አዩ ቀኛማች! አሁን ለሱ በጅብ መበላትና አለመበላት አስበንለት መሰለሁ? እዝጊሐርን አንድ አምላክን እንዳናስቀይም ነውዩ! በፆ ላይ ደሞ ማ መሆኑን እንወእ ብለን ነው ። ወይ ምንዳዬ ወይ ሌላ ሰው ያኸውና እንገላገላለን ። ባንድ ወገንምኮ የግዳይ ያክል ነው ። ምንዳዬም ቢሆን ደስ ይለዋል ። የጠላትን ሬሣ አስከትሎ

መግባትም እኮ ጀግንነት ነው" አለ ፣ አቶ ጀግነህ ስሜታቸውን በሚነካ አነጋገር ።

ምንዳዬን ቅጠላ—ቅጠል እተጐዘጐዘበት ቃሬዛ ላይ በጥንቃቄ አጋድመው ሁሉም በጸጥታ ቆሙ ። የሰዎቹ ጥያቄና ሐሳብ የቀኛዝማችን ልብ አሳላው ። በነገሩ ባይደሰቱም ፣ "በሉ እስኪ እንዳላችሁ ይሁን ፣ ሆን ብለው ለዱር ዐውሬ ጥለውት ገቡ ከምንባልና አንጉል ስማችን ከሚጎድፍ ይዘነው እንሒድ" አሉ ። የሰውዬውንም ሬሣ ቃሬዛ ላይ አጋድመው ፣ ያገኙትን ቅጠላ —ቅጠል ዘንጣጥፈው ጣሉበት ። ምንዳዬ የቸርነትና የመታፈሪያ አደፍደፍ ያሉ ነጠላዎች ተደርበውለት ፣ ቀኛዝማች በቅሏቸው ላይ ወጥተው ከፊት እየመሩ ፣ ቃሬዛ ተሸካሚዎቹ እየተጋገዙ ወደ ሣር —አምባ መልስ ሆነ ።

የቀኛዝማች ልብ የወይዘሮ ደጅ ይጥኑን ገላና መውደድ እንደቋመጠ ፣ ቤትዮዋ ካሁን አሁን ይመጡና አብረን ስንጫወት አድረን ነገ ጧት ይሸኙኛል እንዳሉ ፣ ምንዳዬ ያሰበው ሁሉ ቀርቶ ፣ ፈጽሞ ያልጠበቀው አደጋ ገጥሞት ፣ ፀሐይ ጠለቀች ። ሰዎቹ እየተጋገዙና እያረፉ ፣ ተጨማሪ ሰውም እየተገኘ ፣ ከቤቱ የራቀውም ወደ ኋላ እየተመለሰ ፣ ዳገት ቁልቁለቱን ዘልቀው ከቀኛዝማች ግቢ ግርጌ እንደ ደረሱ ፣ ወሬው በየት በኩል እንደ ቀደመ ሳይታወቅ ኡኡታው ቀለጠ።

ልኬለሽ ደረቷን እየጠፈጠፈች ፣ ደም እንዳሰከረው ሰው ሮጣ ካጥር ውጪ ካሳረፉት ከምንዳዬ ቃሬዛ ላይ ዘፍ አለች ። ተሯሩጠው አነሷት ። ዳግመኛ ወደ ቃሬዛው እንዳትጠጋ ስለ ከለከሏት ሽቅብ ሽቅብ እየዘለለችና ደረቷን እየጠፈረች እዬዬዋን ለቀቀችው ፤ የአካባቢው ሰው ከየቤቱ መጥቶ ፣ ያዘን እያለቀሰ ፣ ሌላው እየተከዘ ተሰባሰበ ።

ቀኛዝማች ፣ በምንዳዬ መቁሰል ክብርና ዝናቸው የተቀነሰና የተነካ ስለ መሰላቸው አንጀታቸው አሯል ። 'ጉዞዬን ለማደናቀፍ ሆን ተብሎ የተደረገ ተንኮል ነው' አሉ በልባቸው ። በአንድ ጉዳይ ግን መንፈሳቸው ረክቷል ። ምንዳዬ ገድሎ በመዳኑ ፣ እንደ ልብ ጓደኛው በጣም ደስ ብሏቸዋል ። ከልኬለሽ ሌላ ፣ ከቀኛዝማች ይበልጥ እጅግ ደስ ያለው ግን ቸርነት ብቻ ነበር ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፣ ወገባቸውን በነጠላ ጠፍንገው ደረታቸውን እየመቱ ከምንዳዬ ቃሬዛ አጠገብ ቆመው እንባቸውን አንዶለዶሉት ። ቀኛዝማች ከጥቂት ሰዎች ጋር ቆመው በትካዜ ያስተውላሉ ። ነገሩ ከጠበቁት በላይ ተጋንኖ የልኬለሽም ኡኡታ ከቀኛዝማች ግምትና ፍላጐት ውጪ ሰዉን ሁሉ በማንጋጋቱ በጣም ተናደዱ ። እፏን ቢያፍኑት ደስታቸው ነበር ።



"ምን መሆኗ ነው ይቺ ሰው! ለምን ተረፈልኝ ፣ ለምን ዳነልኝ ብለሽ ነው" አላት ጀግነህ ።

"ሃይ በሷት ደግም አደል! እሱንስ ቢሆን ለምን ታስጨንቀዋለች ፣ ነውር እማደል እንዴ ! ምንድነው እንዲህ ያለ ነገር" አለ ሌላው ቀበል ብሎ ።

"የሞት መስሏት ይሆን እንዴ? አላወቀች እንደሁ" አለ ከተሰበሰቡት መኻል ።

"ጤናም የለው እንዴ ሰዉ?! ለምን ብለን ነው ሞተ የምንላት?" ብሎ መለሰ ሌላው ።

"ያለሱ ማን አላት? ለሷኮ የሞተ ያክል ነው — — እንዲያው ብቻ አያድርስ ነው!"

"አሁን እሷ ሙሾችና ምን ትጠእመዋለች ። ቆሰለዬ አልሞተ ፣ ይህን ያክል አገር ማመስ ምንድነው?" አለ አንድ ባለ ወፍራም ድምፅ ።

"ድንጋጤ ክፉ ነው ። ቲደርስብን ብቻ ነው እምናኸው ፣ ልጇ መስስ እስቲልላት ነውዴ ፣ ዝም ግለቷግ መች ይኾራል ፣ እንዲያው ለጊዜው ከፉል ያለልን እየመሰለን ነው ። እሱማ እንኳን ለቆሰለና ለሞተስ ምን ይኮናል — —ተሆነ ወዲያ" አሉ አንድ ሽማግሌ ።

ቀኛዝማች ፣ ቅዝዝ ብለው ሰዉን ሁሉ ተመለከቱና ፣ "በሉ እንግዲህ ጎበዝ! ይኸን የኔን ወደ ቤቱ ውሰዱልኝ ። አገር ይየው ብየ ነው እንዳፍታ አሳርፉት ያልኳችሁ ። ያንን ግን ሰው ሁሉ ይየውና ፣ የሚያቀው ሰው ከተገኘ የየት አገር ሰው እንደሆነ እንስማማ እንደሆን ይሆናል" ብለው ሰዉን ለመቀነስና እሳቸውም ገለል ለማለት ወደ ቤት ሲገቡ ቸርነትን ጠርተው ለብቻው ሹክ አሉት ።

እሳቸውን እምናና ተጠግቶ በሚኖር ሰው ላይ ፣ የዚህ ዓይነቱ አደጋ በመድረሱ ፣ እገሬው ፣ 'ለካ እሳቸውም ይደፈራሉና' እያለ የጠላ መጠጫ ፣ የቅራሪ መጨለጫ አድርጓቸው እንዳይጠሉበት እያሰላሰሉ ወደ እልፍኛቸው ገቡ ።

ምንዳዬን ወደ ቤት ካስገቡት ሰዎች መካከል ፣ "ልቅሶ ቲሰማ ደግሞ አደል ፣ እሱም ቢሆን ይጨነቀዋል ፤ ድምጻችሁን ቲሰማ ይባባል" ብለው ልኬለሽንና ልጆቿን ዝም እንዲሉ ስለአስደፈሯቸው ልቅሷቸውን በስቅስቅታ ቀጠሉ ። ከቤት ውጪ ደግሞ ጠያቂዎችና አጽናኞች ስለ ዕለቱ አደጋ የተለያየ ወሬ ያወራሉ ። ከፊሉ ቀኛዝማች

ወጣ ገባ ሲሉ መምጣቱን እንዲያዩለት ከንብንቡን አውርዶ በቀላሉ ከሚታይበት ቦታ ላይ ተቀምጧል ።

ልኬለሽ ንዴትና ብስጭት ሲገፋፋና ሲያዳፋት ፣ "ጉድ አረጉኝ! ጉድ አረጉኝ! ተው ስልህ! — ተው ስልህ! ተው ይቅርብን! — ተው እንሒድ ስልህ! አንት ውለታ ገዳዩ !—— እንዴት ልሁንልህ! እንዴት እባቴ ላርግህ!" እያለች ትንሰቀሰቃለች ። "ጤናም አደለች እንዴ ይቺ ሴት?! ምነው ዝም ብትል" ሲሏት ደግሞ ጸጥ ትላለች ።

ወይዘሮ እልፍ — ይከንዱ ፣ በተራቸው ወደ ምንዳዩ ጐጆ ገባ ይሉና "ወይ ልጄን! — ወይ ልጄን! እስቲ ምን ባረከና ምን በበደ ልክ ነው ይኸ ሁሉ!" ይሉና የገዛ ድርጊታቸው ሕሊናቸውን እንደ ጋሬጣ እየወጋና እንደ አለብላቢት እየለበለበ ስላሠቃያቸው ፣ ፊታቸው ግዕረ — ሞት የሚተናነቀው በሽተኛ መሰለ ።

የምንዳዩ መዳን የተናካሽ አውሬ ያህል እያስፈራራ የሰውቁው መሞት ፣ የሥጋት ጉጠቱን ይዞ አፈጠጠባቸው ።

ምናልባት ምስጢሩ ካፈተለከ ደግሞ ፣ የሚያስከትለው አደገኛ ፍጻሜ እየታያቸው በቁማቸው ተብረከረኩ ። በውስጣቸው የሚፈራገ ጠውን ፍርሃት አድበስብሰው ፣ ስሜታቸውን የሚደብቁበት ጥንካሬ ስላጡ ዙሪያው ገደል ሆነባቸው ። የሚያዩት ሁሉ ሊለሚያስደነግጣ ቸው ነፍሳቸው ከፉኛ ተሠቃየች ።

* * *

አፈሣ ፣ አሞቱ ፈስሶና ይይዘው ይልቀው ጠፍቶት ፣ ጢኽ — ለጢኽ ፣ ፈፉ ለፈፉ እየወደቀ — እየተነሣ ከሸሸ በኋላ የማታ — ማታ ላይን ያዝ እንዳደረገ ወደ ቤቱ ገብቶ ልብሱን ቀየረ ።ቀላ ውሉ የገባ በመምሰል ራሱን እየነቀነቀና እያዘነ ከሰው ጋር ተቀላቀለ ። ወ/ሮ እልፍ — ይከንዱን ማግኘትም ሆነ ማየት አልፈለገም ። ሁለመናው ተብ ረከርኮ በቁሙ ቀዝኗል ። እጁድቅ ባይ እርጌ ሽማ ያለበሰውን እስከ ሬን እንኳ ትኩር ብሎ ማየት አልቻለም ። የሕሊናው ሸብር አዳዲስ ተከታታይ ሥጋትና ጥርጣሬ እየፈጠረ ውስጥ—ውስጡን ያስበረግ ገዋል ። ሐሳቡ ይበታተንና ብዙ ነገር ይታየዋል ። የማይሆነው ሁሉ ። "በል ተነሥ! አንተም አብረህ ነበርክ አሉ" የሚሉት እየመሰለው ገልመጥመጥ አበዛ ። በመኻሉ ደግሞ የዕለቱ ውሎው መነሻና መድረ ሻው ይጠፋውና ነገሩ ሁሉ ቅዠት ይመስለዋል ። የገንዳ — ውኃ ነገር በጣልቃ ብቅ ሲልበት ደግሞ ፣ ነፍስ — ሥጋው ኩምሽሽ ይላል ። "እስኪ ሰው መስሎኝ ከማይረባ ሰው ጋር ወኖ እንዲህ ልዋረድ —



ወይ —ነዶ! እንዲህ ሞቱ ሳይቀርለት — እኔው ተኩሼ ልበለው ስለው እምቢ ብሎ ጉድ — ሆነ! የማያኤውን ሁሉ እያወራ እኔንም ፈርቶ አስፈራኝ" ይላል ። በመኻሉ ሬሣውን አየት ያደርግና ዘወር ይላል። እውስጡ የሚራወጠው ሥጋት — ፈጠር ፍርሃቱ ግን ፣ አንገቱን ጠምዞና የፈረጠጠ ቀልቡን ጨምድዶ ከሬሣው ጋር በሐሳብ ያስወ ራዋል ።

"አንተ እኮ ነህ ለዚህ ያበቃኸኝ ፣ የመከርናትን ሁሉ ዝርክርኳን ባላወጣት እኔ አይደለሁም— እውነትም ሙቻታለኋ!" የሚል ይመ ስለውና ፣ "አይ አሁን ሰው ባይኖርና ብቻውን ባገኘሁት ፣ የልቤን እሠራ ነበር" ይላል ፣ በንክ ቢጤ አስተሳሰብ ። ሰው ሁሉ የጠረጠረውና እሱን—እሱን ብቻ የሚመለከት መሰለው ።

ምናልባት ደባው ቢጋለጥ ፣ የሚያውቀውን ሁሉ ተናዞ ከጣጣው ለመገላገልና ነገሩን ሁሉ በወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ላይ ለመለደፍ ወሰነ ። ሴትዮዋንም ጭንቀት እያዳፋ ካጥር—ውጪ ያስወጣቻውና ወደ ሬሳ ጠባቂዎቹ ብቅ ሲሉ አከላቱ ይረግዳል ።

* * *

ምንዳዬ ቤት ውስጥ ከነበሩት ጥቂት ጠያቂዎች መካከል ፣ አን ዲት ባልቴት ልኬለሽን ከበሩ ሥር ጎትተው ባለቤቷ ወደ ተኛበት አልጋ ወሰዱና ፣ "እስኪ በይ እይው ፣ ለምን ተረፈ ነው? ለምን ከነነ ብሱ መጣልኝ ነው? እንኳንና በጥይት ያክል ነገርና ፣ በዱላ እንኳ የተመታ እንዴት—እንዴት ነው እሚሆነው ፣ ኤጅ—ኤዲያ! አሁን ይህን አጣሽውና ነው ፣ ደግም አደል የጌታን ዐይን አታውጪ ፣ ተፍቶ ልሻል ። በይ ጠጋ ብለሽ አነጋግሪው ፣ ቀስ ብሎ ጥሩልኝ ብሎኝ ነው፣ ደሞ አልቅሽበት አሉ! ነፈረቅ! የሰው ነፈረቅ!" ብለው ወደ አል ጋው ግርጌ ገለል አሉ ።

ደካማዋ ኩራዝ የክር ጥላሸቷን ተሸክማ ለወጉ ያህል በምሰሶው ዙሪያ እያበራች ጥንፋፊ ላምባዋን ሽቅብ ታልባለች ። ምድጃው ላይ የሚነደው የእንጨት እሳትም ፣ ቦግ እልም እያለ ይጭለመለማል ። የቤተሰቡ ኑሮ ምስክር ነው ። በወጉ አይበራ—በወጉ አይጠፋ—የብር ሃንና የጨለማ ቅይጥ— ድንግዝግዝ ።

ልኬለሽ የአልጋውን ወራጅ ዘንግ በሁለት እጇቿተደግፋ ፣ "ምን ዳዩ ? ምንዳዩ? ነብስህ አለ?" ብላ ልታየው ጐንበስ ስትል እንባዋ ተንጠባጠበ ። አቅም አንሶትና ትንፋሽ አጥሮት ዝም አለ እንጂ ወኔው አልተሸነፈም ። ዐይኑን እንደ ምንም ገልጦ "አይዞሽ ደህና ነኝ ፣

አታልቅሺ ፣ ተርፌያለሁ” ብሎ ፈዘዝ ባለ ዐይን አያት ። ድምፁን እንደ ሰማች ነፍሷ ገባች ።

“እሺ” አለችው ከንፈሯ ላይ የደረሰውን እንባዋን ከምራቋ ጋር አብራ ውጣ ። “እንኳን ደህና ሆንክልኚ ፣ እኔስ አላለእበም ። ልጆቹም ዝም ይላሉ ፣ አናለእስም ። አንተ ብቻ አለሁ በለን ፣ ድምጥህን አሰማን” ብላ እንባ በከተረ ዐይን አየችው ። በንግግሩና በዐይኖቹ ተስፋ ተጽናናች ። በድንጋጤ ውርጅብኝ ተናውጾ የቆየው አእምሮዋ ፣ ጸጥ—ረጋ ማለት ሲጀምርም የፈገግታዋ ጎሕ ከትካዜዋ ጀርባ ብቅ ማለት ጀመረች ።



## ምዕራፍ ዐሥራ አራት

ቀኛዝማች ፣ ባስቸኳይ እንዲመጡ የላኩባቸው ወጌሻ ከተለያዩ ፅፅዋትና ሥራ—ሥር ያዘጋጁትን ድቁስ መድኃኒት በትናንሽ ቅሎች ይዘውና ፣ የሰባራ መጠገኛ መቃቸውን አንጠልጥለው ሲገቡ ሁሉም ከልጋው አካባቢ ገለል አለ ።

“ይኸ ሁሉ የሰው መንጋ አንድ ላይ ታጉሮ ምን ያረጋል? እንባ ምን ሲፈይድ አይታችኋል? ደም ሲያቆም ነው ፣ ቁስል ሲያጠግግ” ብለው ከነተከታያቸው መደብ ላይ ዐረፍ አሉ ። የሣር—አምባና የአካባቢው ሕዝብ ‘እሳቸው እጃቸው መዳኒት ነው ፣ እንትፍ— እንትፍ ብለው ዳበስ ዳበስ ታደረጉ ፣ በኢ ነው’ በማለት ያምንባቸዋል ።

አንድ እፍኝ ጨው የተጨመረበት ውሃ እንዲሞቅ ስላዘዙ ወዲያው ተጥዶ ማገዶ ተለቀቀበት ። ኩራዚቱም ከቀኛዝማች ቤት የመጣ ላምባ ተጨመረባት ።

“ይኸ ቤት—ቤቱ ምንም አያረግልኝ —— እስቲ ደህና ደህና ጉበዝ ከደይ ጥሩ” ብለው እንዳዘዙ ፣ አራት ሰዎች ተከታትለው ገቡ ። ሌሎቹን ሰዎች ከቤት አስወጥተው ወደ ምንዳዩ አልጋ ከተመለሱ በኋላ ፣ እጃቸውን በዝግታ ካንገቱ ሥር በማሳለፍ ከትካሻው ቀና ሲያደርጉት ቸርነትና መታፈሪያ ፈጥነው ረዷቸው ። ከራሱም ከትከሻውም ከወገቡም ደጋግፈው ሲያስቀምጡት ፣ ልኬለሽ እበሩ ጋ ቆማ የሚያደርጉትን ታስተውላለች ። ልጆቹም አጠገቧ ቆመው ይመለከታሉ ። ደረታቸው ቅትት—ቅትት እያለ ይናኻሉ ። ምንዳዩን ደጋግፈው ሰፊ ግርንቡድ ላይ ካስቀመጡት በኋላ ፣ የሚያኽ ደሙን ለማቆም የታሰረውን ጨርቅ በዝግታ ፈቱት ።

ወጌሻው ለብ አለው ውሃ ውስጥ ጥጥና ላባ እየነከሩ ግራ ክንዱን በዝግታ ካጸዳዱ በኋላ ፣ “ይኸውላችሁ ፣ ጥይቷ በየህ በኩል ገብታ በዚህ በኩል ነው የሾለከችው” ብለው የግራ እጅ ጣቶቹን አንድ ባንድ ደጋግመው ሳቧቸው ። ሦስቱ ብቻ ቋ—ጧ— አሉላቸው ። የክንዱን አጥንት ቀስ ብለው በዘዴ ሲደባብሱ ፣ ከብብቱ ይጀምሩና እስከ ክርኑ መታጠፊያ ይወርዳሉ ።

“ኧረ እንደ ተወራውም አደል ፣ ሥጋ—ሥጋውን ነው ፣ አጥንቱን ላመል ታህል ነው አከክ ያደረገቻት ። ጌታ ውሎለታል ፣ ቁስሉ እን

ደሁ ነገ ጧት ይሽራል” ብለው የምንዳዬን እጅ በጥንቃቄ በቸርነት ካስያዙ በኋላ ፣ ከትናንሽ ጡሊዎቻቸው አረንጓዴና ግራጫ መሳይ ዱቄት እያወጡ ፣ ጥይት በገባበትና በወጣበት በኩል በጣታቸው ገፉ—እያ ደረጉ ገና ደም በሚያዝው ትኩስ ቁስል ላይ መድኃኒት ደመደ ሙበት ። ባመጡት አሮጌ የነጠላ ትልታይ ጨርቅ በክንዱና ባንገቱ ዙሪያ እየጠለፉ አሰሩለት ። ከትከሻና ከሽንጡ ወደ ቀኝ ዘንበል አድርገው የግራ ብብቱን የኋላ አካባቢ ደባበሱት ። የፈሰሰው ደም ረግቶና ደርቆ ትናንሽ ቅርፊት ፈጥሯል ። ያንንም ለብ ባለው ውሃ ውስጥ ጥጥ እየነከሩ የማጠብ ያክል ጠራረጉና አፏን ከፍታ ደም የምታመነጨውን ሁለተኛዋን ቁስል አገኟት ። ረጋና ትኩር ብለው የደሙን መፍለቂያ ካስተዋሉ በኋላ ፣ ዙሪያዋን ነካ—ነካ ፣ ጫን ጫን እያደረጉ ቀጠን ብሎ የረጋውን ደም ሲያስወጡ ምንዳዬ ፣ “እስስስ! አ!” ብሎ የሥቃይ ድምፅ አሰማ ። የልኬለሽ ልብ ሥቃዩን በሰቀቀን ትጋራ ። ፊቷ ቅጭም ብሎ ዐይኖቿ ፈጠጡ ።

“አይዞህ! አይዞህ በርታ! እንኳን የኔን የሽማግሌውን እጅ ጥይ ቱን ችለኸዋል ። አንተ ደሞ አይቆጭህም ፣ አንጅትህን አርሰሃል” ብለው እንደገና ዙሪያውን እየጠራረጉ ካጸዱና የረጋውን ደም ካስ ወገዱ በኋላ ፣ ፈገግ ብለው ቀና አሉ ።

“እንዴት ያለ ልበ ንጡሕ ነው! በየህ በኩል የገባችውማ ምና ምኒት አጥንት እሚሉ ነገር ሳትነካ ሥጋ—ለሥጋ ሾልካለች ። አዬ ዕድል እናንተ ሆዬ! ጌታ ከወደደኮ ከፈላ—ውሃ ያወጣል! አሁን ያነዬ የዛሬ ስንት ዓመት መሆኑ ነው ፣ የንቅጥቅጡ ጊዜ እንዷ ዘመዴ የድንጋይ ቤት ግንብ ተደርብቶባት ኡሑ ተባብለው ቲያወጧት ፣ ለማላ ያክል እንኳ ጫር አላረጋትም ። እስቲሽርልህ ድረስ እጅህን ማንቀሳኧሱ ነው የሚቸግርሂ ፣ ጡንቻህ መወጠሪያ ላይ ባለመሆኗ ደህና ነህ ፣ የዛሬውን ቀን ባል—እንዳለው ባሉን ጠይኧህ ጠብለው ፣ መሰንበቻ ውን ደህና — ደህናይቱን ጉርስ — ጥጥት ካረከ ብድግ ትላለህ” ብለው ወደ በሩ እያዩ ፣ “ሌላ አሮጌ ነጠላ የለሽ ይሆን? ማ ሒዶ ያመ ጣሊ እኔም ጋ ነበረ” አሉ ።

ልኬለሽ ፣ ወደ ድብኝቷ ተንደርድራ ማጀቱ ገበያ ስትወጣና ቤተ ክርስቲያን ስትሔድ የምትለብሳትን ነጠላዋን ሰጠቻቸው ።

“እንዴ ፣ ይኸማ አይሆንም ፣ ሌላ ነትብትብ ያለ እላኢ አልኩሺ ይኸ—”

“ግዴለሁም—ሆን ብዬ ነው ። ለማባቱ ሊሆነኝ ፣ እንዳፈቀደሁ አርጉት ።”



“ተይ አይሆንም ኋላ ኧን” አሉ እንዳትጸጸቺ በሚል ስሜት ።

“በሉ ወዲህ በሉት እኔው ልጀምርልሁና” ብላ እጅዋን ስትዘረጋ ወጌሻው የነጠላውን ጥለት በጥርሳቸው ነክሰው ቁልቁል ተለተሉት ።

“ና በል እንደ እድምህ ደህና አርገህ አብራልኝ” አሉት ባለ ኩራዙን ። ከዚያም እንደ መጀመሪያው ሁሉ ከየቅሎቹ መድኃኒት እያወጡ በመነስነስና ባውራ—ጣታቸው እየሰጎዱ ከሁለት አቅጣጫ ደመደሙለት ። በነጠላውም ትልታይ በትከሻው አሻግረው ካንገቱ በስተቀኝ በኩል ጠልፈው ፣ በደረቱ በኩል በማሳለፍና በግራ ትከሻ ውም በማዞር ካሰሩለት በኋላ በጥንቃቄ አስተኙት ።

“እንግዲህ እንደ ካካቴ አትንጫጩ ። ጥላ እንዳይሆንበት ሽማ ቢጤ ጋርዱለት ። ሰው ቲንጋጋ ጥሩ አደለም ። ዛጎልም የብር ቀለ በትም አበት አርጊለት ። መበርታት ተንግዲህ ነው ። የምትነጨዋንም የምትጠጣዋንም መረአ የሰጠሽው እንደሆነ መሰንበቻውን ይጠግለ ታል ። ሰውዬው ግን በለስ ባይሰጠውና ፣ የዚህም ቀኑ ባይደርስ ነውዬ አተኳኮሱስ የዋዛ አልነበረም” ብለው እጃቸውን ከታጠቡ በኋላ ፣ ቅላ ቅልና መቃቸውን አንጠልጥለው ወደ ቀኛዝማች እልፍኝ ሔዱ ።

* * *

“እኔ ቅድሙንም ተናግሬያለሁ ፣ ለዚህ ኖሯል እንዴ ስታንዘፋዝፉ የመጣችሁት ? እንዲች ብላችሁ እዚች እግቢዬ እንዳታገቡ ። ለሱ ብቻ የመጣ መሰሏችኋል ፣ የተደገሰው ለኔ ነበር ። ባይገድለውም እኮ ገሎታል ፣ የምንዳን ደም አፍሶ ነው የሱ ሬሣ እዚች እግቢ እሚገባው ? ለካጥር ውጪም ሰው ምን ይላል ብዬ እያንገበገበኝ ነው ። እኔ የሽፍታ ሬሳ ማጎሪያ ነኝ እንዴ? ለኔ ብላችሁ እንደሁ ኮለሌ ጣሉት” ብለው ካስጠነቀቁ በኋላ ቀኛዝማች ወደ ቤት ገቡ ።

አንዳንዶቹ እየተሾካሾኩ ሲያሙና ሲያወሩ ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ እጅግም ጮክ ሳይሉ ፣ “የኖረ አህያ እንኳ ለጅብ ቲጣል ያሳዝናል፣ ዐይናችን እያየ አውሬ ይብላው ማለት ጡር ነው ፣ ደግም አደል ። ነገና ተነገ ወዲያን ነውዬ ማየት ፣ ለክፉም ለደጉም ሰው የጁን አያ ጣም ። ባይሆን እንደ ፈረደብን እዚቹ እብርድ ላይ ስንጠብእ እናድ ራታለኒ ፣ ሰው ሆነን ከሰው ተፈጥረን ላውሬ አንሰጠውም” እያሉ አንድ ሽማግሌ ጅምራቸውን ሳይጨርሱ “አገር ማስደቡስ ቀላል ነወይ ፣ እንዲህ ያለው ሰባራ—ስም እስተ ልጅ—ልጅ ይሻገራል ። ሣር—አም ቦች ሰው ገለው ለጅብ ጣሉ መባልስ ውርደት እማደል ወይ?” ብሎ አቋረጣቸው አንዱ ።

“ገበርኩ ነው ጌታዬ ! ምንም ይሁን ምን እገዛ አገሩ የሞተ ሰው በምን ጠደኸው ።”

“ሙት ወቃሽ መሆን ነውዪ ፡ ይኸነዩ የሰንት ሰው እንባ ይኖርበት ይሆናል” አለ ሌላው ።

“ኧረ ተዉ እናንተ ሰዎች ጡር አትናገሩ ፡ እሱ እውነቱ አገር ሔዷል ፡ እኛ እዚህ በፈጣሪ ሥራ ገብተን ስንቱን እንዘላብዳለን ፡— —ያዝ ያረገን እንደሁ ሙስስ ልንል ።”

“ነግ በኔ ነው ጕበዝ ! ከቤቱ አይወጣ —መከራ አያገኘው የለም፥ ስለ ሥራው እንደሁ ጌታ አምላኽ ይጠይኸው ። እኛ እንደ ጀመርን የዛሬን እንደር” አለ የመጀመሪያው ።

ሁሉም በየበኩሉ ነገሩን አሰላሰለው ። ማንም ከመካከላቸው በግላዊ ርኅራኄው ይሁን በድፍረት ‘በገዛ ቤቴ ማንም አያገባውም’ ብሎ ሬሳውን ወስዶ ሊያሳድር የሚችል አልነበረም ። ሁሉም ጥርስ መግባት አይፈልግም ። ከምንዳዬ ይልቅ የቀኛዝማችን ቂምና ጥላቻ ይፈራሉ ። ስለዚህም እዚያው ከቦ በማደር ተስማሙ ።

ወይዘሮ አልፍ—ይከንዱ ፡ በምንዳዬ መጎዳት ተቆርቋሪ መስለው ወጣ ገባ ቢሉም ፡ ሊገልጹት የማይቻላቸው ምስቅልቅል ስሜት ናጣቸው ። እያዳፉ የወሰዷቸው ይመስል ወደ ሰውዬው ሬሳ ሲሔዱ ደግሞ ከውጪኛው አጥራቸው በር ፊት ለፊት ይቆሙና ፡ “መገን እኔ ዘንድሮ! አይ ቀን ሲጎድል! ምነው በኸረብኝ” በማለት ሰዎቹንና ሬሳውን በእሳቱ ውጋገን በትካዜ ያዩዋቸዋል ። ቀኑ የድንጋጤና የግርግር ዕለት በመሆኑ ሁሉም በያለበት የየራሱን ወሬ ስለሚያወራ ፡ ማን ወዴት እንደ ሔደና ከየት እንደ መጣ የሚያይና የሚያጤን አልነበረም ። ቤትዮዋም ልኩ ያልታወቀ ጊዜያዊ ብስጭት ወለድ እብደት ዳበስ ያደረጋቸው መሰሉ ። ‘ይኽ ዘላባጅ አፈሣ ያጋልጠኝ ይሆን ?’በማለት የሚሠጉት ሥጋትም ልባቸውን እየሰረሰረ ሁለመናቸውን ጋጠው ። ስለዚህም ውስጣቸውም ፡ ውጪአቸውም ነሆለለ ።

ቀኛዝማች ፡ በበኩላቸው የምንዳዬ በጥይት መመታት በጣም አሳስቧቸዋል ። ከሣር—አምባ— እስከ ዞን—አምባ አያሌ ሰዎችን ጠረጠሩ ። አውጥተውና አውርደው ብዙዎቹን ከነገሩ ነጻ አደረጓቸው ። በጣም የከነከናቸውና በተለያዩ ጥያቄዎች ቀስፎ የያዛቸው ግን ገንዳ ውሃ ጢሻ ውስጥ የተገኘው አገልግል ነበር ። ያገልግሉ ጉዳይ በሐሳባቸው ውስጥ አንገዋብ—አንገዋብ እገዛ ቤታቸው ያኮበኩባል ። ይህን ሐሳብ ወዲያ ቢሉት ወዲህ አልላቀቅ አላቸው ።



ቸርነትም አገልግሉን አገላብጦ ካየ ወዲህ ፡ ከራሱ ግምትና ጥርጣሬ ጋር ሙግት ገጥሟል ። በግርግሩ መኻል ጠበንጃ እንደሚያስቀምጥ ሰው ፡ ወደ እልፍኝ ገብቶ አገልግሉን ደብቆ ሲያስቀምጥ ነገሬ ብሎ ያየው ሰው አልነበረም ።

ቀኛዝማች በላይነህ ፡ ቤቱ ጭር ማለቱንና ባለቤታቸውም ምንዳዬ ቤት መሆናቸውን ወጣ ብለው ካረጋገጡ በኋላ ቸርነትን አስጠርተው እልፍኝ ገቡ ።

“ያን አገልግል የት አረከው? ደህና ስፍራ ደብቀህ አስቀምጥ ብየህ ነበር — —”

“አስቀምጪዋለሁ ፡ ላምጣው እንዴ?” አለ ወዳስቀመጠበት አቅጣጫ እያየ ።

“እስኪ አምጣው ፡ ሰው አንሥቶት ከሆነም ካንተ ነው ጠቤ —”

“ቀድሞ ማ አየውና! — — ማንም አላየ ። እኔ ምኔ ሞኝ ነው” ብሎ ወዳስቀመጠበት ሔደ ።

ባይናቸው ተከተሉት ። ከሳቸው ባሻገር ከነበረው ድንክ አልጋ ሥር ጨለማው ውስጥ የደበቀውን አገልግል አውጥቶ እፊታቸው አስቀመጠላቸው ። ከፊታቸው ገለል ብሎ እንደ ቆመ ፡ እሳቸው እንደተቀመጡ ፡ ማንገቻውን ፡ ልጉሙን ፡ መቆለፊያውንና መጠኑን ጭምር አገላብጠው አዩት ። አገልግሉ የተለጐመበት ማህራረብና ዐልፎ—ዐልፎ እፊያው ላይ በጌጥ ማውጫ የመተከቫ ብረት የተሠራው ሽልም ጌጥና አጫጭር ሐረግ ፡ እንዲሁም ያመጡበትን ቦታ አስታወሱት ። ግራ—ተጋቡ ።

‘የኛ ከሆነ በየት በኩል ሔዶ እዚያ ወድቆ ይገኛል ። ምንዳዬ ይዞት ሔዶ ነው እንዳይባል ደግሞ ፡ ከመቼ ወዲህ የዚህን ቤት አገልግል ይወስዳል ። ለዚያውም ይኸ ትልቅ ነው ። ቢወስድስ እዚያው አጠገቡ ወድቆ ይገኝ ነበረ ፡ እዚያ ጢሻና ፈፋ ውስጥ ምን ወስዶ ይጥለዋል?’በማለት ሲያወጡና ሲያወርዱ ከቆዩ በኋላ ፡ ወደ በሩ ጠጋ ብሎ የቆመውን ቸርነትን “እስኪ ሒድና ያቺን አረጋሽን ጥራት ፡ አንተ በዚያው ምንዳዬ ጋ ሒድ ፡ ይቺ ነገር ብልጭ ብትል ዋልህ ! እኔ እንዲያው ለምናልባቱ ላጣራ ብዬ ነውዪ ፡ ይሆናል ብዬስ አይደለም ፡ ባምሳያም ሊሆን ይችላል ። አንተ ግን አፍህ ሸርተፍ እንዳይል ሳያጣሩ ወሬ ደግም አደል” እንዳሉት ውልቅ አለ ።

‘አወጫባሪ የሆኑ ሰውዬ! ስንበትበት ብለውማ የገዛ ቁምጣ ሱሪዬንም በወጉ ታቀዋለሆይ ታይሉኝም አይቀሩ ። ስንትና—ስንትኽን

እንዳህያ የተደበለልኩትን አገልግል አጣሁትና ፣ አምሳያው ይሆናል ሲሉኝ ቃጢ” እያለ አረጋሽን ጠራላቸው ።

ቀኛዝማች ፣ በአገልግሉ ሰበብ ክፉና ደጉን ሲያሰላስሉ አረጋሽ ገብታ ቆመች ። “እ! መጣሽ? እስኪ ነይ ወዲህ ጠጋ በይ” አሉ እሷንም አገልግሉንም እያዩ ። እጅዋን የኋሊት አጣፍታ ጠጋ ብላ ቆመች ። እልፍኝ ውስጥ ብቻዋን ተጠርታ ከገባች በምስጢር የምትላከውና የሚነገራት ፣ ወይም የሚጠይቋት ነገር እንዳለ ታውቃለች ። የታላቅ ወንድም ልጅ በመሆኗና ፣ ያለሷም ታማኝ ምስጢረኛ ያለ ስለማይመስላት ፣ በዚህ ሁኔታ ተጠርታ በገባች ቁጥር ኩራት እየተሰማት ትደሰታለች ።

“እስኪ ይኸን አገልግል ደህና አርገሽ እይው” አሏት ። ወደ ፊኖሱ ብርሃን ተጠግታ አገላብጣ አየችው ። “ምን ይሆን ነገሩ ፣ ደግሞ ምን ሊያመጣብኝ ይሆን ?”ብላ ዝም አለች ። ፋታ አልሰጧትም ።

“ምነው ዝም አልሽ? አየሽው አደል? የማን ነው?” አሏት ።

“አገልግሉማ የኛ ነው ። ዛሬ ምን መጣና የኖረ አገልግል አስመጥተህ ጠየከኝ ብዬ ነውዪ — —” ብላ ፣ ውስጥ ውስጡን ግን ፣ “አዬ ፈጣሪ አምላኬ! የዚህ ቤት ጉድ አያልቅ” አለች ።

“የኛ መሆኑን አረጋግጠሻል ?”

“እንዴ! እንኳን ይኸና ፣ የቤታችን ሰባራ ገልቦ ይጠፋኛል እንዴ?’

“ማለፊያ! ታዲያ ይኸን ሰሞን እቤት ኖሯል?”

“አዎድ! — — ኋላ ማ ይወስደዋል?”

“እኔማ የት ዐቃለሁ ፣ ይኸ ይኸ የናንተ ሥራ ነው፣ ግን — —” ብለው ሳይጨርሱ ፣

“ዛሬ እንኳ አይቸዋለሁ ”።

“እንዴ? ተይ ከልብ ሆነሽ ተናገሪ ፣ ያላየሽውን አየሁ አትበይ ፣ እንደ ቀላማጅ ”።

“እኔ ያላየሁትን አየሁ አልልም ፣ ለማ ቢዬ ነው መዋሸቴ ፣ — — አይቸዋለሁ ”።

“ካልሽም ይሁንልሽ ። ያዋሳችሁት ሰው ኖሯል —ወይስ” — — — ብለው እንደ ጀመሩ ፣

“እቴዋ አውሰው እንደሁዪ — — እኔማ ምን ዶሎኝ — —”



“እንዴት ነው ምን ዶሎኝ ብሎ ነገር — — ወጪና ገቢውንም አታቂም ማለት ነው? እኔም ሞኝ ነኝ አንቺን አደራ ማለቴ ፣ የት እንደ ተገኘ ስትሰሚ ፣ ገና ጉድሽ ይፈላል ።”

“ኧረ እኔ ሙያየን ከቤትም አልወጣሁ ።”

“መልቲ! የሰው መልቲ ! ከቤት አልወጣሁም ካልሽማ ፣ ይኸ አገልግል በየት በኩል ወጥቶ ሔዶ እዱር ተገኘ? ሲወስዱም አላየሽ ማለት ነው ። ዋናው ነገር የኛ መሆኑን ማረጋገጥሽ ነው ። ነገር ቢመጣ ወለም—ዘለም እንዳትይ ።”

“ደሞ የምን ነገር ነው?” አለች ፍርሃት—ፍርሃት እያላት ።

“እየፈታፈታችሁ የምትልኩለት ሰው እንዳለ ብዬ ነዋ!”

“ውይ! አበስ ገበርኩ! አሁን እኔ ነኝ እንዲህ ያለውን ነገር እማደርገው ? የነሱን አላእም — — በዚህ ተሆነስ ፣ ያሻህን አርገኝ — — ለምን ዐርባ አልገረፍም — — — ”

“ሌላም ሰው አጠቃቅሶ ሲወጣ ዝም ብለሽ ካየሽ እኮ ያው ነው። ወይ እንደዋዛ ከተል ብሎ መሔጃውን ማየት — — ወይ ለማን እንደሚያቀብል — — ”

“እሳቸው እንደሁ አያረጉትም ። በዚህ እንዳትኮነን ። ባይሆን ያቺ ጉደኛ ዘመዳቸው ‘አዩኝ— አላዩኝ’ እያለች እግራችንን ጠብአ ታረገው ይሆናሊ” አለች የምትገላገል መስሏት ። ቀን ያየችውን መናገር ፈርታ እንጂ አስታውሳለች ።

“ማ?” አሏት ቶሎ ካፏ ቀልበው ።

“ሌላማ ማን አለ ፣ ያቺው ሸዋርካብሽ — እሷ ናት እነካኪ — — አታርፍ!”

“ዛሬ አገልግል ስትቋጥር አይተሻት ኖሯል?”

“ለማን ነው ብዬ አላልኳትሚ — — እሱማ !”

“ታዲያ ይህን ያክል ምን ወዲያ — ወዲህ አሰኘሽ ? — ዛሬ አይተሻል ?”

“አዎድ ፣ ዛሬም አይቻታለሁ” አለች ድምፅዋ በፍርሃት እየደቀቀ ።

“በይ ሒጂ ፣ ይቺ አሁን ያወራናት ወሬ ብልጭ ብላ እሰው ጆሮ ትገባና ነግሬሻለሁ ። ዘልዝዬ ነው እምሰእልሽ ! ታቂኛለሽ ! በይ ደሞ ያቺን ሸዋርካብሽን ጥሪያት” ብለው ገላመጧት ።

ሟቹንና አገልግሉን እንዴትና በምን እንደሚያገናኙ ግራ ገባቸው ። ግልጽ የመጠራጠሪያ ምክንያት አጡ ።

"አንድ ያልታወቀ ነገር አለ ማለት ነው ። አለበለዚያ አገልግል አሞራ አይደል ። ምን አስቸኮለኝ ፣ ከቶ ሥራን ተራራ አይሸሽገው" አሉ ። ሐሳባቸው በያቅጣጫው ኳተነ ። ከእያንዳንዱ ተከታታይ ሐሳብ በኋላ ፣ "የሚገርም ነገር ነው ፣ መጨረሻውን ብቻ አይቼ" በማለት የግምትና የጥርጣሬአቸውን ጦር ወደ ተለያዩ ሰዎች ሰበቁት ።

ሸዋርካብሽ አዳራሹ ውስጥ ተቀምጣ ስታወራ ፣ አረጋሽ ጠጋ ብላ ቀኛዝማች እንደሚፈልጓት ስትነግራት ፣

"ምነው ፣ ለምን ፈለጉኝ ? ራት ይቅረብ ተባለ እንዴ!" አለች ብድግ ብላ ።

"እኔ ለምን እንደ ተፈለግሽ አላእም — — — ለራትም አልመሰለኝ — — " አለቻት በሚያሥጋ ሁናቴ ።

"ማን አለ! እቱሜቱ አለች እንዴ!" አለች ለምን እንደ ጠየቀች ሳይታወቃት ።

"እሳቸው ጋሼ ምንዳ ቤት ናቸው ። ይልእ ቶሎ በይ!"

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ በሉሉበት ተጠርታ ከገባች ላንድ ከበድ ያለ ጉዳይ ወይ ጥያቄ እንደሚሆን ታውቃለች ። "ምን አረግሽ ሊሉኝ ይሆን ጌታዬ ፣ ምነው ዕድሜዬ ባጠረ ዘንድሮ ሹን" እያለች ገብታ ገለል ብላ ቆመች ።

"የት ኖረሻል!" አሏት ከእግር እስከ ራሷ እያዩ ።

"እዚሁ እትልሉ ቤት ነበርኩ ።"

ሁኔታቸው ሁሉ አላማራትም ። ልቧ ተርበተበተ ። ሰረቅ አርጋ ሰውየውን ስታይ ዐይኗ አገልግሉም ላይ ሰላረፈ ፣ አካላቷ ተንዘፈዘፈ ። ዐይኗ እዚያው ተሰካ ።

"ይኸ አገልግል የማነው ?" አሏት እሷንም ፣ ዕቃውንም ተራበተራ እያዩ ።

"የቱ ?" አለች አገልግሉን እያየችው ነፍሷ ተጨንቃ ።

"ስንት አገልግል ይታይሻል ? ይኸን ነዋ !" አሏት ባገሚቸው እያሳዩ ።

"ዛሬ አንድ ጉድ አለ ፣ ቤቁም ደጁም አላማረኝ" አለችና ጉንበስ



ብላ አየችው ። የምታስበውም ፣ የምትናገረውም ጠፍቷት ዝም ብላ ቆመች ።

"ምነው ዝም አልሽ! አንቺን እማደልንዴ እምጠይቀው!" አሉ በስጨት ብለው ።

"እ !" አለች በስመመን ።

"በይ እሱን በር መለስ አርጊውና ነይ !"

መሬት ቁና ሆነችባት ። በሩን ዘግታ መለስ ስትል ፊቷ የፍርሃት ደም ተከለበሰበት ። "በይ ይኸን አገልግል እንሥተሽ እዪው !" አሏት በግራቸው እየገፉ ። እጅዋ እየተንቀጠቀጠ አገላብጣ አየችው ። ድንጋጤ ተናነቃት ።

"እህ! ———በያ ተናገሪ! የማን ይመስልሻል ?"

"እ!"

"አትናገሪም ወይ ? ምነው ምን ዘጋሽ ?!" አሉ በቁጣ ።

"የኛ ነው" አለች የሞት ሞቷን ።

"ልብ ብለሽ —እዪ!——እንዳትሳሳቺ" አሏት በሚያፋጥጥ ሁኔታ

"አዎ" አለች በሰላላ ድምፅ ።

"በምን ዐወቅሽው ?"

"የገዛ አገልግላችንን እንዴት አጣዋለሁ !"

"በምን ዐወቅሽው ነው ያልኩሽ ?" አሉ በቁጣ ።

"በማንጠልጠያው ነዋ ! ማንጠልጠያው ድፍን ነው ። በያ ላይ ደሞ የዚህ ዓይነት ሌላ አገልግል የለንም ። ይኸ የተለጐመው መግህር አረም ነው"

"እንዲህ እያፍታታሽ ተናገሪ ! ትላንትም ዛሬም እቤት ኖሯል!?"

"እዎ!"

"ዋ ! አይ ቀላማጅ ! ይኸ አጉል መቀላመድ ! ከዚህ ከቤትም አልወጣ ?" ተጨንቃ ዝም አለች ። አገልግሉ ነፍስ ቢኖረው ሲዋ ፣ ዐመድ ቢሆን ብን ባረገችው ነበር ።

"እውነት —እውነቷን ብትናገሪ ይሻልሻል ! ያቺ እንደሁ የቀራት ነገር የለም ፣ ልቅም አርጋ አንድ ባንድ ነግራኛለች! ያልሰማሁ መስሎሽ" አሉ በሚያፋጥጥ ቃና ።

ነገሩ ሁሉ ተማታባት ። "ያቺ ሙጢ—አፍ አገልግል ይዛ ስትወጣ አይቻታለሁ ካለቻቸውማ ጉዴ ፈጠጠ ። እኔ እነሱ ሊተዋወሱና ዞረው ሊላላሱ ምን አስዋሸኝ ፣ በምን አበሳዬ ልጠመድ ። እኔ የትም—የትም ዞሬ ቁራሽ እንጀራ አላጣ" ብላ ቀልቧን አረጋጋች ።

"እኔ ምን አስዋሸኝ— —እቴሜቴ ዛሬ አገልግል ቋጥሪ ብላኝ— —"

"ከዚያስ ፣ ?" አሏት በችኮላ ።

"ከዚያማ ፣ ላብዬ አፈሣ ወስጂ ሰጠሁት — —"

"የቱ አፈሣ?" አሉ ቅጭም ብለው ።

"እየሀ ስሬ ያለው የኛ አፈሣ!"

"እሱ ሚስቱ የት ሔዳ ነው ፣ አገልግል ተዚህ መወሰዱ?"

"እኔ ምን አአለሁ!" ብላ የፎይታ ያህል ተነፈሰች ።

"አሁንማ እኔ ምን ዐቃለሁ ማለት የለም ። ብላችሁ — ብላችሁ እየፈተፈታችሁ ታቀብሉ ጀመር ። ገና ብዙ ጉድ አለ ስትዝረኽረሁ ጉዳችሁ መውጣቱ ነው ፣ እዚህ ድረስ መጥቶ ነው የወሰደው? እንዴት ነው ነገሩ ? " አሏት በግልምጫ ።

"እኔ ነኝ እያ ሃይ ወና ድረስ ወስጂ የሰጠሁት" አለች እየተን ቀጠቀጠች ።

"ከዚያስ?" አሉ ተጣድፈው ።

"ተመልሼ መጣሁ ።"

"አንቺማ ተመልሰሻል ፣ እሱ ወዴት ሔደ?—በሥራቱ ተናገሪ ፣ ልቤን አታቃጥሉት! ልብ አርጊ! ዛሬ ነው ማለትሽን! ይቺ ቃልሽ እንዳትለወጥ ።"

"አዎድ! ዛሬ ነው"

"አገልግሉንም አረጋግጠሻል!"

"አዎድ" ብላ አገልግሉን እንደ ተናካሽ አውሬ ፈራችውና እግሯ ሥር አስቀመጠችው ።

"ለመሆኑ ዛሬ ብቻ — — — ሌላ ጊዜም?" አሉ ጥርጣሬያቸው እየበዛ ።

"በዚህኛው ዛሬ ብቻ — —" ብላ ግራ—ተጋብታ ዝም አለች ።



"እህ!ደህና ሙያ ተይዞልኛላ ! ገና ብዙ መዘዝ አለ! እንኳን ብቻ ፍንጩ ተገኘ!"

በድን ሆና ቆማ ፣ አፈሣን እያሰላሰለች ሠጋች ።

ቀኛዝማች መጨረሻውን ለማወቅ ተጣደፉ ። ብዙ ነገር ታያቸው ። "ነገሩ ያበቃ እንዳይመስልሽ ። ገና ምኑ ተይዞ! ገና ብዙ ምስጢር አለ ማለት ነው ፣ ዋ አባሽ! ይቺ ወሬ ትሰማና ! ነግሬሻለሁ! አንቺ ቀልማዳ ቅልምድምድ! በይ ሒጂ!" ብለው ባይናቸው ገረፏት ። ቅስሟ ነክቶና ልቧ ተርበትብቶ ሹክክ ብላ ስትወጣ ፣ "እኚህን ሰውዬ አላይበት እምን ጉድጓድ ልግባ" አለች በልቧ ።

አረጋሽን አዳራሽ ውስጥ እንዳገኘቻት እልህ ተናነቃት ። ጉሮሮ ዋን ሲል አድርጋ አናቷን ብትላት ደስታዋ ነበር ። ዳሩ ምን ያረጋል ጉኗን አይታ ፈራች ።

"አይሰእሉኝ! አይዘለዝሉኝ! ሒጂና ጨማምረሽ ንገሪያቸው ደሞ" አለቻት ።

"እረ ንሺ አረጋሽ! ነገር ማወናወን እምችዪው አንቺ ! ወስፌ አፍ! " አለቻት አፍጣ ።

"ማ? እኔ ልጂት?! አይይይ! ምን ያረጋል — — እምነግርሽንስ ዐቀው ነበር!" አለችና ራሷን ነቀነቀች ።

"በያ—ንገሪኝ! ምን አስፈራሽ! ተናገሪና ይውጣልሽ! ምን አለ ባት ልትዪ ይሆን?"

"ያለብሽንማ አንቺው ታኢ.ዋለሽ! ምን ይሆናል ፣ ጉንሽን አይ ተሽ ነው! እኔ ለራሴ ማን አለኝ?"

"ይኸን ታወእሽማ ፣ እጅ—እግርን ሰብስብ ፣ አፍን ክርክም ነው!" አለቻት በኩራት ።

"አይይይዋ ! አለማወእ! ያስመካ መስሎሻል ፣ አያስመካም! አንድ ድዬ እማይገባበት የለም!"

"እከከከከ! ለዚህም በትተሻል ለካ! በያ ግደይው! ይኸው ነው የቀራችሁ!?"

"እሞፈር—እቀምበር አትርገጪ ! አንካኪ! አላኳሽ! እኔ ማንዛ ረጥ አላእበትም!"

"ድንቄም! ያብዬን ለምዬ! በማ መስለሽ እንዲህ እምትዘናበ

ጨው?———እገዛ ቤቱ ተኽምጠሽ ነገርሽን ትፈተፍቻለሽ! ሙሬ—አፍ! !የሰው ሙሬ አፍ!” ብላ ቱግ አለች ።

“ኤጭ ኤዲያ! ለማያእሽ ታጠኝ!” ብላ ስትወጣ “ይቺ የበረት ውልድ ተዘባነነች እኮ” አለች በቀስታ ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ምንዳዬ ቤት ቡና አስፈልተው ፣ እዚያው ከተቀመጡትና ወጣ—ገባ እያሉ ከሚያወሩት ጐረቤቶች ጋር እያወሩ ለይስሙላ ቡና ሲያከትሙ ፣ ሐሳባቸው የማይደርስበት ፣ ሥጋታቸው የማይገባበት ቦታ አልነበረም ።

ምንዳዬ እየቆየ—እየቆየ ሲያቃስት ፣ የልኬለሽ እንባ ሰልፉን ይዞ ያሽቆለቁላል ።

“እስቲ እንዲያው የዝጌሐርን ነገር እዩት” አሉ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ በአዘኔታ ስሜት ።

“የቱን?” አሉ አንዲት እርጅና የተጫናቸው ባልቴት ። “ይኸን የሱን ነገር ነዋ! አየሁ ሲንከላፈት ውሎ ፣ የማታ ማታ——” ከማለታቸው ፣

“ፍርጃ ነው እመየቴ! ፍርጃ! ሩህያችን በሱ እጅ ሆና ስንቱን እንመኝዋለን ፣ ዘወር ቷልብን ፣ የንሳቻ ጭብጦ ልናህል ። ይቺ የዛሬዋ ጀምበር በሱ እጅ ሆና ፣ እኛ የከርሞውን እናስባለን” አሉ ከወደ ጥግ የተቀመጡ ኮስማና ሽማግሌ ።

“ኋላስ! የኛ ነገር ይኸው አደል ። አንዲት ስኒ ቡና እስክንጠጣኳ ስንት አለ ። እኛ ደሞ እንዲህ ያለውን ውርጂብኝ በየት አስብነው—አይፍረድ ነው!” አሉ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ከምንዳዬ ቤት ጣራ ጥቀርሻ ግርጌ በገመድ የተንጠለጠለችውን የብቅል እንጀራ አሻቅበው እያዩ ። “አሁን በያ ሰሞን እንዲህ ወዳንጦኪያ ነው አሉ ፣ አባትና ልጅ እሰበሰብ ተቀምጠው ጣያቸውን እያሟሟኡ ፣ ልጅዬው ጠመንጃውን ፈትቶ ሲወለውል ይቆይና ግጥምጥም አርጎ አንድ ሁለት ሦስትዩ ጥይት እየዶለ እያወጣ ቲፈታትሽ ፣ በመኻሉ አባትና ልጅ ወሬአቸውን እያወራሩ ቲጫወቱ የጠመንጃው እፊ—ሙዝ ወዳባትዮው ዞሮ ኖሮ ፣ ልጅዬው ወሬ—ወሬውን እያሰላሰለ ታይታወኸው ምላጩን ሳብ ማድረግ ፣ ለካስ ጥይት ዶሎበት ኖሮ ፣ የገዛ አባቱን ግድል አርጎት እርፍ! የገዛ አባቱን ነው ተብሎ ዝም አይባል ነገር ፣ ዳኞቹ በጄ አይሉ ፣ ልጅን እፍስፍስ አርጎ ወህኒ——” አሉ በወቅቱ የሚያወሩና ልባቸውን የሚያታልሉበት ሌላ ሐሳብ ስላጡ ።

“አባትዮው ሞቶ ልጅዬው ደሞ ወህኒ?” አሉ ሽማግሌው ተገርመው።



“እንዲያው የፍርጃን ነገር ማየት ነውዩ” አሉ ከገዛ ሐሳባቸው ጋር ሳይገናኙ ።

ቀደም ሲል ያሰላሰሉት ሐሳብ የምንዳዬን አደጋ በፍርጃ ገልጸው እንደዚያ ዐይነቱ አደጋ አጋጣሚ እንጂ ፣ ታስቦ የሚደረግ ያለመሆኑን ለማስረዳትና ‘እውነኩን ነው እውነኩን’ እንዲባሉ ነበር ። ነገር ግን ወሬውን ሰምቶ ያጋነነና የቀጠለበት አልነበረም ። በወሬ ፋታ ለማግኘት ተነሣሥታ የነበረችው ነፍሳቸው በስንጥር እንደ ነኳት የጥንቅሽትል ተኮማተረች ። እሳቸውም ዝም አሉ ።

ላይ—ላዩን ጸጥታ የለፈነባቸው ቢመስሉም ፣ ውስጥ—ውስጡን ግን የሥጋትና የጭንቀት መንሽ እያገላበጠ በረበራቸው ። አዳዲስና እጅግ አስፈሪ ሐሳብ ያምጣሉ ። የሚወለደው ሐሳብ ግን እንደ ተናካሽ አውሬ ያስፈራራቸውና ፣ “እይ! ይኸስ የኔም አደል ፣ አበስ ገበርኩ!” ብለው ሐሳባቸውን ጥለውት ይሸሻሉ ። ይከተላቸዋል ። በመጨረሻ ግን ፣ ጭንቀታቸውን ሁሉ ለጊዮርጊስ እየነገሩ የሚሳሉትን ተስለው ሳይጨርሱ ቀታቸውን ሁሉ ለጊዮርጊስ እየነገሩ የሚሳሉትን ተስለው ሳይጨርሱ ሽዋርካብሽ ደጅ—ለደጅ ተንቆራጣ—ተንቆራጣ ፣ ፍርሃትና ሥጋት ሲያናውዛት ቀይቶ ቀስ ብላ ምንዳዬ ቤት ገባች ።

በጭንቅላቷ ስትጠቅሳቸው ፣ በዝግታ ተነሥተው ተከተሏት ። እሷ እየመራች ፣ እሳቸው እንደ ለማዳ በግ እየተከተሉ ፣ በስተግራ በኩል ካለው እዳራሽ ግራ ጥግ ጨለማ ውስጥ ገለል ብለው ቆሙ ።

“ምነው? ደህናም አደለሽ እንዴ?” አሏት ኩራት በሸፈነው ሥጋት።

“እዬ እቴሜቴ” አለች ፣ ራሷን እየነቀነቀችና ዐይኗን እያባበለች ።

“ምናባሽ ሆነሻል?—እስጢቲ! የሰው እስጢቲ! ማ ተናገረሽ ” አሏት በእኔ እያለሁ ቃና ።

“እይ እቴሜቴ! ይብላኝልሽ! እኔስ እንደ ዶሮ የትም ጭሬ አድራለሁ ።”

“ጤናም አደለሽ እንዴ? ምን ሆነሻል? ምንድነው ነገሩ?”

“የዛሬውንስ እታንሺው እቴሜቴ!”

“እኮ ምንድነው ነገሩ?——ዐፈር ብይ እቴ! ምን ግራ ታገባኛለች!”

“ሳብዩ እፈሣ የበጠሁት——”

“ሳብዩ እፈሣ የበጠሽው ምን?”አሉ በከውታ ።

“የበጠሁት እገልግል ነዋ—ምነው እፈር በበላሁት ዛሬ ኸን!”

"የቱ አገልግል?" አሉ ሰማይ—መሬቱ እየዞረባቸው ።

"ያንን ዛሬ ወስደሽ ስጪው ያልሽኝን ነዋ!"

"ታዲያ ምን አረገው? የሱ ነገር እኮ — — " አሉ ካንገታቸው ጠጋ ብለው ።

"እኔ ይት—አባቴ ዐውቄለት ፣ አገልግሉን ይዘው ቲያስቀዝኑኝ አመሹ ።"

"ማ?" አሉ ቢያውቁም በድንጋጤ ።

"ምኑን ማ ትይኛለሽ እቴሜቴ? እሳቸው ናቸዋ" አለች ፣ በሚያረጋግጥ ሁኔታ ።

"ጤናም አይደለሽ እንዴ?—ምን መሆንዋ ነው?"አሉ እየተንቀጠቀጡ ።

"አይ እቴሜቴ! ኧረ ሲሰሙትስ የምርም አይመስል ።"

"ታዲያ አንቺ ላፈሣ የሰጠሽውን አገልግል እሳቸው ከየት አገኙት?—ቅዠታም!"

"አይ ቅዠት እቴ! ቅዠትማ ቢሆንልኝ በየትኛው ዕድሌ!"

"ለሱ እማደል ወይ ወስደሽ የሰጠሽው? ለማባሽ ኖሯል የሰጠሽው?"

"ቲያመጣው ይኸው ነው እቴሜቴ!—ምንስ ብሆን አብዬ አፈሣን አጣዋለሁ?"

"ታዲያ ምን ልበል ? ለሱ ሰጠሁት ታልሽ— እሳቸው ከምን ምድር አገኙት?"

"እኔ የታባቴ ዐውቄ!—ምነው ዛሬስ ድራሼ በጠፋ!" ብላ አለቀሰች ።

"እንዴት ነው ምን ዐውቄ ብሎ ነገር?! ኧረ ንሽ እልፍ ይከንዱ! ተይ ተልብሽ ሁኚ!?"

"ኧረ ተይ እቴሜቴ ቂል አታርጊኝ!—እኔ እንዲያው ቲፈጥረኝ አዛ አያጣኝም — — — "

"ይኸን ቀልድሽን ተዪኝ ብያለሁ! ጥላ ቢስ! የሰው ጥላ ቢስ!"

"ኧረ ተይ እቴሜቴ! ተመቹ ወዲህ ነው እምቃለድሽ !?"



"ይኸነዬኮ ላልተባልሽው አቀብለሽልኝ መጥተሽ ነው ፣ እኔ መች አጣሁት!!"

"ኧረ ተይ ጡር አትናገሪ—ደግም አደል!—እቴሜቴ!"

"እት ይንሳሽ በመንሻው! እኔ ያንቺን ሥራ አጣሁትና ነው? አ ሄ ሄ ሄ ሄ !"

"ኧረ ዐፈር ያርገኝ እቴሜቴ ፣ ለምን አሁን ጠርተሽ አጠይኢውም?"

"ሊ.ኧር!? አይኧርም! ይኧር መስሎሻል እንዴ ? ለመሆኑ የት አገኘሁት አሉ?"

"ደሞ ይህን ያክል ክብርት ። ጠርተውኝ ገባ ተማለቴ በጥያኤ ቲያፋጥጡኝ ጊዜ — —"

"ምን ምን እያሉ?" አሉ ልባቸው ያለመጠን እየመታና ጀርባቸው እየጋለ ።

"ይኸ አገልግል የማነው እያሉ ነዋ!"

"አንቺ ታዲያ ምን አልሻቸው?"

"እኔማ ምን እላለሁ — — — "

"እኮ ምን አልሻቸው? ዐቀዋለሁ አልሻቸው?"

"ሌላማ ምን አፍ አለኝ?!"

"ዐፈር ብይ! ዐፈር ያስበላሽ! አይ የኔ ዘመዶች! ሰላ—ገደደ የትታቃላችሁ! ገና ዛሬ ምሰሽ ቀብረሽኝ !! እኔ ደሞ ሰው አገኘሁ ብዬ! መቸ እንዲህ እጄን ይዘሽ ትሰጪኛለሽ ብዬ — — — "

"ምን አርጊ ትይኛለሽ እቴሜቴ? ያቺ ፍየል ምላስ ዘመዳቸው አምባር — ተቀለበት አርጋ ነግራቸዋለች! ምን እንዳለቻቸው የት ዐቃለሁ ፣ እኔ ለራሴ እገባበት ጠፍቶኝ — — — "

"ምነው ዛሬስ ሞቼ ባረፍኩት! ምነው ዐፈር በበላሁት! ምነው የናቴን ቀን በሰጠኝ!" ብለው ቁጭ አሉ ።

"ኧረ እማይበጅሽ ዐፈር ይብላ!—ለምኑ ብለሽ!?"

"እስኪ ተይኝ ልጄ! እስኪ ተይኝ! አሁን ለመሆኑ አገልግሉ እማጋ ነው ያለው?"

"እያው እሳቸው ጋ ።"

"ወይኔ ልጂት! እስቲ ስንትና—ስንት አገልግል አለ? አላኸውም አትዪም?"

"እኔ አላኸውም ብል እሳቸውስ ያኡት የለም እንዴ ?"

"በምኑ ያኡታል? ደሞ ተመቼ ወዲህ ነው ፣ አገልግል አዋኢ የሆኑት ?"

"ምንስ ቢጠፋቸው በማህር አረም የተለጐመው አገልግል ይጠፋ ቸዋል እንዴ?"

"ውይ!ውይ!ውይ! በሱ ኖሯል እንዴ የወሰድሽለት ?"

"እዎድ!"

"ተመቼ ወዲህ እሱ አገልግል ተቤት ወጥቶ ያቃል! ማ አዘዘሽ?!"

"ቶሎ በይ ስትይኝ ጊዜ ወረድ አርጌ — — —"

"እንግዲህ የኔ ነገር ምን መላ አለው! —ምንም መላ የለው!" ብለው መሬቱን መቱ ።

"ኧረ ተይ እቴሜቴ! ኧረ ተይ! — — ያንቺን ስም አላነሡ !"

"ቀድሞውንም ፈርቻለሁ! 'ሃይ—ሃይ! ሃይ—ሃይ! 'ብሎ እዚህ ማጀ የዶለኝ እሱ ነው ። ያለሱ ምን ጥላት አለኝ ። 'ተው ታስገኘኛለህ ፣ ተው አይሆንም' ስለው ናኒጋ ከተተኝና ዐረፈ ። —የኔ ነገር ሞቷል! እውር በዳበሳ የሚያኸውን አገልግል ይዘው — — —"

"ይቺን ከውካዋ መኻል አናቷን ብያት ልሒድ!"

"አይይይ! ኧረ ወዴትና ወዴት፣ እኔ በምን ኃጢያቷ ።"

ሸዋርካብሽ ግራ ገባት ። ምኑን ከምንና ፣ ማንን ከማን ጋር እንደ ምታያይዘው ጠፋት ። ጨለማው ውስጥ እንደ ቆመች ውስጧም ጨለ መባት ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ጉልበታቸውን ተመርኩዘው በዝግታ ተነሡና ፣ "በይ ግቢ — መጣሁ" ብለዋት በጓሮ በር በኩል ወጥ ተው ሔዱ ። ካዳራሾቹ በስተደቡብ ምዕራብ ሲል የሚገኙት ሁለት የእጥር በሮች ጥሩ ጥሩ መዝጊያዎች ያላቸው ሲሆን ፣ ሁለቱም የሚዘ ጉት በጉቶ ድጋፍና በወፍራም እንጨት ተዋጋ ነው ። በጣም ቤተኛ ከሆኑ ሰዎችና እንደ እነ ምንዳዬ ካሉ ታማኝ ሎሌ በቀር ሌላ ማንም ሰው በነዚያ በሮች በኩል አይወጣም—አይገባም ።



ሸዋርካብሽ የቤትዮዋ አካሔድና አፈጣጠን ስላላማራት ፣ መለስ ያደረጉትን በር ቀስ ብላ ከፍታ በርቀት ተከተለቻቸው ። ሐሳባቸው በመበታተኑና ትከተለኝ ይሆናል ብለው ስላልገመቱ መለስ ብለ ውም አላዩ ። በጨለማው ውስጥ በየአጥሩና በየዛፉ ጥላ ብቅ ጥልቅ ሲሉ ፣ ከአቸኳኮላቸው ጋር በሕልሟ የምታያቸው መሰላት ። ወደ አፈሣ ቤት መሆኑ ግን ገብቷታል ።

" 'ለማን ሰጥተሽው መጣሽ ?' እያለች ከምትነዘንዘኝ ፣ እንዲህ እሷው ራሷ ሔዳ ስታጣራ እርፍ ትለዋለች—ምን በወጣኝ እቴ በማላ ኸው ነገር መንገብገቤ" አለችና ፣ "ይኽ ቀዳዳ ሰውዬ አልሰጠችኝም ብሎ ይሸመጥጥ ይሆን እንዴ ?" በማለትም ሠጋች ።

* * *

ቀኛዝማች ፣ ስለ አገልግሉ መገኘትና ካጥር ውጪ ስላለው ሬሣ በተደጋጋሚ እያሰቡ ባልታወቀው ሰውዬ ሞት ምክንያት ሥር—ሥሩን ተደስተዋል ። አንዳንድ ጊዜ የምንዳዬን የጀብድ ሥራ በሐሳባቸው ይነጥቁና 'አሽከርዬው ቢገልም ፣ ጌትዬው ያደረገው ያክል ነው ፣ ሳተና ጎበዝ መርጦ ማስቀደምና ቀልጣፋውን አይቶ ማስከተልም እኮ የባለ ሙያ ሥራ ነው ። እሱ በለስ ቀንቶት ቢገልም ፣ ገዳሉ መባል ያለባ ቸው ቀኛማይ ናቸው' በማለት ዝናውን ነጥቀው ክብሩን ይጐናጸፉሉ ። ይህን የሳቸውን ሐሳብ ሰው ሁሉ የሚያስበው እየመሰላቸው ፣ ከውስጥ ልባቸው ሲንደቀደቅ ፣ ከላይ ፊታቸው ፈገግ ይላል ።

ምንዳዬን 'እንኳን አተረፈህ ፣ የነዚህ የጣናት ልጆችህ አምላክ ነው የጋረደልህ' እንዲባልና ፣ እሳቸውን ግን ፣ 'እንኳን ደስ አለዎ! እንደ ቀትር እባብ የሚናደፍ ትንታግ ጎበዝ የሚመርጥ እኮ ጀግና ሰው ነው' እንዲባሉ ይፈልጋሉ ።

እንደገና ደግሞ ፣ ከተንጠራራ ስሜትና ልጓሙን ከበጠሰ ምኞት ተላቀው የገዛ ራስን ለመመልከት ወደሚያስችል የሕሊና ክልል ሲመ ለሱ ፣ "የዚህ የሰውዬ አመጣጥ እኮ ለኔም ሊሆን ይችላል ። ካሁን አሁን ደረሰ እያለ ሲጠባበቅ ውሎ ፣ የሱን ብቻ መምጣት ሲመለከት ንድድ ብሎት ተኩሶበት ነው ። እኔ ግን ስንቱን ስመኝ ሳልም ፣ አጉል ሊያበለሻሽኝ ኖሯል? በዚቹ በመመረጤ ቀንተው ነው ። ሌላማ ለምኑ? ምንዳዬ አንዳንድ ቀን እንደሚያደርገው መንገድ አሳብሮ በሌላ በኩል ቢሔድና ፣ እኔ አገር አማን ነው ብዬ ከች—ከች—ከች ስል ቢያገኘኝ ኖሮ ታላሰበው ጠብ ነበር እሚያረገኝ ። ተተቀደሙ ወዲያ ምን መላ አለው? አሁን ማይሙት እኔ እንደሱ ተንከባልዬና

ተቀላጥፌ ልድን! የማይመስል ነገር" በማለት አቅማቸውን ተረድተው ያንኑ ሚካኤላቸውን ደጋግመው ያመሰግናሉ ።

ከዚህ ሁሉ የሐሳብ ትንቅንቅ በኋላ ስሜታቸው ሲሰክንና ያ በውስጣቸው የሚጎማለለው የሐሳብ ጀግና ውሻ እንዳየች የበግ ግልገል ጥፏቸው ሲፈረጥጥ የጉራቸው ወናፍ ባዶ ይሆናል ። ከዚያ በኋላ ስሜታቸው ኩም ፥ ልባቸው ቅዝቅዝ ይላል ።

* * *

ከመንደሩ በገዛ ፈቃዳቸው የተሰባሰቡት ራሣ ጠባቂዎች ፥ እንጨታቸውን እየማገዱ ፥ በየዕድሜያቸው መጠን ያዩትን ፥ ካባቶቻቸው የሰሙትን ተራ በተራ ያወራሉ ። አቶ አከሌ ተብሎ ላልታወቀው ሰውዬም አንዳንድ ሴቶች ደረት መተውለታል ። አንዳንዶቹም ፥ "ዐፈር ይብላኝ! የየት አገር ሰው ይሆን ይሆን? ዋ! ያቺ እናቱ ይኸን ጉዱን አላየች ፥ ይኸን ጉዱን አልሰማች" በማለት በነግ—በኔ ርኅራኄ ትንፋሽ ሳያሰሙ አልቅሰው ፥ አንድ ሁለቴዬ ተናፍጠውለታል ።

ቀኛዝማች ፥ እንዳይሰሙና ምንዳዬም እንዳይቀየም ተጠንቅቀዋል። ሰው ሕይወቱ እንዳለፈ እንደኛው የሕልውና ምዕራፍ ይዘጋና ፥ አዲሱ የሙት ሥያሜው, ራሣ ይሆናል ። ሞት የሕይወት ደለል ነው ። ያም ሽፍታ የሙታን የጋራ ስም ከተሰጠው ቆየ ። ወይራ ሳይነድ ወይራ ። ከነደደ በኋላ ዐመድ ነው ። ባመዱ ለመኩራራትና ፥ ወይራነቱን ለማሳወቅ ፥ ላንድ አፍታ ብቻ የወይራ ዐመድ ቢባልም—ዐመድ ! —ያው ዐመድ — — ዐመድ! — — ዐመድ !

በሕይወት ማክተሚያና በራሣ መባል ጅማሬ መካከል ያለችው የጊዜ ቅጽበት ያዲሱ ሥያሜ መብረቃዊ የጊዜ ድልድይ ናት ። ደሃ ሞቶ ከቤቱ ፥ ባሕታዊ ከበዐቱ ፥ ነጋሲ ከቤተ መንግሥቱ አስከሬናቸው ሲወጣ ማንኛውም ልዑልና — ትሑት ስማቸው ቀርቶ ራሣ ይባላሉ ። ይስተካከላሉ ።

ራሣ ጠባቂዎች ፥ "አትንጫጩና— አትጩሁ ፥ ቀስ እያላችሁ አውሩ" የተባሉ ይመስል ፥ የሚያወሩት ረጋና—ቀስ ብለው ነበር። አንዳንዱ ወደ ራሣው ማየት ሲፈራ ፥ አንዳንዱ ደግሞ ራሣውን ሲያይ "ምነው እኔ ብቻ መሞቴ? በል አንተም ና" ይለው ይመስል ቶሎ ፊቱን ዘወር ያደርጋል ። የእሳቱ ብርሃንና የጨለማው ግብግብ በሚፈጥሩት ግፊትና ሽሽት በቃሬዛው ዙሪያ ሞት ያደፈጠ ይመስላል ።

አብዛኛዎቹ ስለሟቹ የነበራቸውን ሐሳብ የሚረሱት ከመካከላቸው በለዘኛ ወግና ተረታቸው የታወቁት ሽማግሌ አጠር—ወይም



ረዘም ያለ ወግና ጨዋታ ሲጀምሩ ነበር ። እኩለ—ሌሊት ገደማ እንደ ሆን ሁሉም በተንደረከከው ፍም ዙሪያ ተኮልኩሎ እሳት ሲሞቅ ፤

"አሁን ደሞ እንዴት ያለች አንድ ሸጋ ወግ አለችኝ ልንገራችሁ ፥ እሳትኮ ደግም አደል ፥ እንቀላፋችሁ እንዴ ?" አሉ ሁሉንም ባይናቸው እያዳረሱ ።

"ኧረ ተየቱ! አልያዘንም" አሉ በሁሉም ስም ሦስት አራቱ ።

"ሰውዬው አሉ ፥ ያንድ ቀን ውሎ ያስኬዳል አሉ ፥ ዘመዶቹ ሠርግ ይጠሩትና ሚስቱን ይዞ ይሔዳል ። ተዚያ ላይን ያዝ እንደማረግ ሲል፥ ሰው ሁሉ ዳስ ውስጥ መደዳውን ሆጭ ብሎ ተኽምጦ ጠላውን ቲጠጣ ይደርሳል ። እሱም ሚስቱን እጐኑ ቁጭ አርጎ ፥ አንደዬ ተቧ ፥ አንዳንዴዬም እጐኑ ተነበረው ሰውዬ ጋ እያወጋጋ ጠላውን ቲጠጣ አዳዩ አሁንም አሁንም መለስ —ቀለስ እያለ'ምነው ጨብጣችሁት ቀራችሁሳ? እምን ገድ የዋለ ሰው እንዲህ ነውንዴ አጠጣጡ?' እያለ ይሞላላቸዋል ። ያም ምንገድ ቲያንገላታው ውሎ የለ ፥ እሱም እየጠጣ ፥ ሚስቱንም ጠጪ ይላል ። ጠላ አዳዉ ገና ደረስኩ—ደረስኩ እሚል ሶታ ጉረምሳ ኖሮ ፥ ጠላ ሲሞላ በመጣ ቁጥር ፥ የሰውየውን ሚስት እግር በ'ግሩ አውራ—ጣት ረገጥ ወጋ ፥ ዳሱ ደሞ ጨለምለም ያለ ኖሯል ፥ እንደ ሚኸዳ ሰው ጉንበስ ይልና ፥ ቀስ ብሎ አስልቶ ፥ ቆንጠጥ ፥ ረገጥ—ምልዝግ እያደረጋት ይሔዳል ።

"ቆንገዦ ኖራለች?" አለ አንዱ ።

"ቆንገዦ! ጀምበር ፍንጥቅ አስክትል እምትሳም" አሉ ብልዛቸውን በውጋጋኑ እያሳዩ ።

ሁሉም ሣቁ ። ሽማግሌውም አብረው ወፍራም ነኪታ ሣቅ ሣቁ ።

"ችላ—ችላ ቁንጢጡ ቲበዛባት ጊዜ ፥ የባሏን እግር ቀስ ብላ ታነሣና እግሯ ላይ ውድር!"

"እ! ይተማመኑ ኖሯል?" አለ አንዱ አቋርጦ ።

"ኋላስ! ቢተማመኑማ ነው ፥ የባሏን እግር እላዋ ላይ መዘርጋቷ ።"

"በጄ!" አለ ሌላው ችኩል በረጂሙ ።

"ከዚያማ አዳይ ሆዬ እንደ ለመደ ጠላውን ሊሞላ ይመጣና ፥ በሰው ሚስት ቁንጅና ነሁሎ የለ? የሴትዮዋን እግር ያገኘ መስሎት የባልየውን እግር በቁንጢጥ ብድግ ያደርግለታል ።"

"የቅዱስ ሚሃል ያለህ ! ጉድ ፈላ!" አለ አንዱ ተመሳጭ ።

"ባል ሆዬ ቁንጢጡን ቀምሶ ዝም" ብለው ሲቀጥሉ ፣

"ሙትቻ! የሰው ሙትቻ!" አለ አንዱ ።

"ዐፈር ይብላ! ዐፈር ያስበላው! አይመርግበትም ኖሯል! አይ ዘረጥራጪ!" ሌላው ።

"እያቸው እንግዲህ — —ማቲ ይመስል አያሰሙ!" አለ ሌላ ቁጡ።

"አሁንም እንደገና አዳይ ሆዬ ቆየትየት ይልና ፣ ጠጡዬ!" እያለ ከባልየው ፈንጠር ብሎ ይጀምርና ፣ እየሞላ እየሞላ ይሔድና ፣ እዛቹ እል ማዱ ጋ ቲደርስ ፣ አሁንም ያው የሷ እግር ይመስለውና በቁንጢጥ ብድግ ያረግለታል ፣ ይኸነዬ ባል ሆየ አዳዉን ይጠራና — —"ብለው እንደቀጠሉ ፣

"እንዴት ያለው ፣ በክት—የበከተ ኖሯል! ወይ ነዶ!"አለ አንዱ ጣቱን እያፎኸ ።

"ውይ!———ምነው ዝም ብትሉና ብንሰማበት!"

"ወንድሜ!!" ይለዋል በማለት ቀጠሉ ።

'አቤት'

" 'አሁንም ይኸው አጠገቤ ቁጭ ብላለች ፣ ኋላም አቅፌያት እተኛለሁ ፣ ነገም ዐይንህ እያየ አገሬ ይዣት እገባለሁ ፣ ኧረ ለመሆኑ የት አገኛት ብለህ ትለፋለህ' አለው" አሉ ።

"እንዲሁ ብሎ?" አለ አንዱ በመደነቅ ።

"ከዚያስ "አለ ሌላው ፣ ሌላ ፍጻሜ በመፈለግ ።

"ከዚያማ ምን ይበል ፣ ቅንጡን እንደ ተመታ ሌባ ፣ ጀሮውን ወትፎ እልም አላ!"

"ደህናውን ሰው አጋጥሞታሊ ፣ እኔ ብሆን አለቀውም ነበር ።"

"የምን መልቀቅ! እኔን ያየህ ተኸጣ እስቲል ማበራየት ነበሪ" አለ አንዱ ተናዶ ።

"ዱላ ምንድነው? የባልየው ብልሃት ይበልጣሊ! ለዱላውማ ሁናቴውን አይቶ ይደርስበት የለ? መለስ ብሎ ናገር ቢለው ኖሮ—ያነዪ ነበር ወንድነቱን እሚያሳየው ፣ ያ እንደሁ ጥፋቱን አውቆ ሙሰስ ብሎ ሸሸ ። ባልየው ነዊ ብልጡ" አለ ሌላ ጐልማሳ ።

ከዚያም እንደየስሜትና ግንዛቤአቸው ተመሳሳይና ተፃራሪ አስተያየታቸውን ሰጡ ። ረመጡ ከሥር — አድፍጦ ፣ ፍሙ ስንጥቅጥቅ ቀያይ መስመር ሠርቶና ቀሪው የዐመድ ሻሹን እንደ ለበሰ ዶሮ ጮኸ።



በእሳቱ ዙሪያ የተቀመጡት ሰዎች እንደ ልብ ሲጫወቱና ሲሣሣቁ፣ አንድ ሰው ብቻ አእምሮው በሥጋት ተሰልቦና ፊቱ በሐሳብ ጠውልጎ ተቀምጧል ። ዐልፎ ዐልፎ ከሐሳቡ ሲባንን ከሚሉቅ አንቀቢት ላይ ደብቆ የወሰዳትን ኩብሬት ከእጀ—ጠባቡ ደረት ኪስ ዳበስ ያረግና ከሐሳቡ ጋር ይወዛገባል ። በየወሬው መኻል ፣ በየተረቱ ጣልቃ፣ እንቅልፋን ለማብረር ፣ ወይም ለሽንት የሔደ በማስመሰል የምንዳዬን ጎጆ በየት በኩል እሳት እንደሚለቅባት ከሩቅ እያየ ይመለሳል ። የእምሮው መሽበርና የወኔ ቢስነቱ ጉዳይ እንጂ ፣ የምንዳዬን ቤት ዙሪያና መላ አቀማመጧንስ የገዛ ቤቱን ያህል ያውቃታል ። ተንኮሉ ቢኖርም እሞትና ብልሃት ታጣ ።

ያን ለት ማታ ምንዳዬን በሚጠይቁ ሰዎች ወጣ—ገባ ማለትና ካጥር—ውጭ በነበሩት ሬሣ ጠባቂዎች ምክንያት የቀኛዝማች ግቢ በር አልተዘጋም ።

የምንዳዬ ጎጆ የባለቤቷን ወኔና ድፍረት ተጐናጽፋ ፣ የምትገላም ጠው መሰለው ። ቤት ሳይሆን ነፍስ ያለው አውሬ መስላ አስፈራራችው። አፈሣ ነፍሱን ቋጥሮ ከጎጆይቱ ጋር እንደ ተፋጠጠ ዶሮ ድጋሚ ጮኸ። እንደገና እሳቱ አጠገብ ይሔድና ፣ እሱን ከሚያህለው ፍርሃቱ ጋር ተፋርፍጦ ፣ ከሐሳቡ ጋር ይራኮታል ።

"አሁን ደሞ እንዴት ያለች ሸጋ ተረት አለችኝ ፣ ማንጊያ ትሆናለች" አሉ ሽማግሌው ።

"እጥቢያም ወጣች ፣ ሳይታወኸን እኮ ነጋ" አለ አንዱ እየተንጠራራ ።

"በየት እንወኸው ብለህ ነው ፣ ይኸው እስታሁን ጥርሳችን ታይ ከደን ፣ ይልቅዬ ይኸ ሬሣ ቀረበት——" አለ ሌላው ፈዘኛ እየሣቀ ።

"እሱንማ ምንዳዬ ደህና አርጎ አጫውቶታል! አሁን ምን ያረግለታል?" አለው የሱ ቢጤ ።

"አይ ወሬ ማቀርፈድ ስቶዱ ፣ አሁን ቢያጫውቱን ምናሻችሁ ፣ ምን እሚሉ ፈሊጥ ነው ደሞ በሙት መኸለድ!!" አለ ሌላ ልዘዝ ባይ ። ሁሉም ነቃ ብሎ ሲያዳምጥ አፈሣ ብቻ እኳሉ ተቀምጦ መንፈሱ ኮብልሏል ። ሁሉም ተንከትክቶ ሲሥቅ ከሐሳቡ ደንግጦ ባነነ ።

አእምሮው እንደ ተነካ ሰው ፣ የሚያደርገውን ትክክለኛ ነገር ማሰብና መወሰን ያቃተው መሰለ ። እንዳመሉ ቀስ ብሎ ተነሣና ክብሪቱን ይዞ እየተርበተበተ ትልቁን የግቢ በር ፀልፎ ገባ ። ከዚያም ጥግ—ጥጉን ያጥሩን ጥላ እየተከተለ በዝግታ ሲራመድ ፤

"እይ አፈሣ ፣ እንዲህ ያለውን ጉድህንስ ሰው አይስማው" አለ አንድ አሽሟጣጭ ተከልሎ ።

"እኔ ታዲያ እቧ መሆኗን የት አየሁላችሁ ? በያ ላይ ደሞ ባዶ እጇን" ።

"እባብ ነውዬ ዘንዶስ አልሸሽም ያለው ሰውዬ ቢጤ መጣ" አለው በድጋሚ ።

ልኬለሽ እየሣቀች ወደ ቤቷ ስትሔድ ሰዎቹም ወደ ነበሩበት ተመለሱ ። አፈሣ ግን ፣ ሲያውጠነጥነው የሰነበተው ደባ ከሽፎና ምስ ጢሩ የማፈትለክ ያሀል ካልጠበቀው ቦታ ደርሶ ፣ የእሱንና የወይዘሮ እልፍ ይከንዱን ሕይወት በማሥጋቱ ፣ ያደረበት ፍርሃትና ሥጋት የሚ ያጅርገውን ስላሳጣውና ስላንቀዠቀዠው ፣ የሚያስበው ሐሳብና የሚ ወስነው ውሳኔ ሁሉ ወደ ጊዜያዊ ንክነት አደላ ። የደህናው ጊዜ አፈሣ መሆኑ ቀርቶ የውጪ—ነፍስ ግቢ ነፍስ መዋከቢያ ሆነ ። አመሻሽቶ ከቤቱ የወጣበት ፋይዳ ቢስ ዓላማው ምክንያት መከናና ልቡ በኃፍ ረተ—ቅሌት ነክቶ እሱም እንደ ሰዎቹ እዚያው ተቀመጠ ።



## ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፣ የአፈሣን አጥር ጭራሮ በር ወደ ውስጥ ገፍተዋት ገቡ ። ሸዋርካብሽ ካጥር ውጪ ፣ አጥሩ ጥግ ተለጥፋ ቆመች ።

"ወይዘሮ አስካደች !" እያሉ ሁለት ሦስተዬ የአፈሣን ባለቤት ጠሩዋት ። የወቅቱ የድንጋጤ ስሜት በፈጠረባቸው ሁኔታ እንጂ ወይዘሮ የሚለውን የአክብሮት ቃል ከዚያ ቀደም እሷን ለመጥሪያ ተጠ ቅመውበት አያውቁም ። "ሴቱ ሁሉ ወይዘሮ እየተባለ ከተጠራማ ጉድ ፈላ ። የደህና—ደህናው ሰው ሚስት በምን ሊለይ ?" ይላሉ ራሳ ቸውን ከፍ ሲያደርጉ ።

"እመት !" ብላ በሯን ከፍታ ከወጣች በኋላ ፣ "ማነሽ ?" አለች በድምፃቸው ስላላወቀቻቸው ።

"እኔ ነኝ" አሉ በቀስታ ። በጨለማው ውስጥ ሙቀሟ መስለው ቆመዋል ። ዐወቀቻቸው ።

"ደህናም አደለሁ እንዴ ? ምነው በጭለማ ?" ብላ ወደ ሴትዮዋ ተራመደች ።

"ደህና ነኝ ፣ የለም እንዴ ?" አሏት እሳቸውም ወደቧ እየሔዱ ።

"ገና አሁን ገባ ማለቱ ነው ፣ ራሴን አሞኛል ብሎ ጋደም ብሏል" ከማለቷ አልፈዋት ገቡ ።

እዚህም ምሰሶው ወገብ ላይ ላምባዋ ሊጠነፈፍ የተቃረበ ኩራዝ የጨለማ አፍ እስኪጉርሳት ታጣጥራለች ። አፈሣ ጋደም ብሎ በሐሳብ ይናውዛል ።

"ደህና አመሸህ ወይ?" አሉት እንደገቡ ።

የዋለበት ድንጋጤና ውስጥ—ውስጡን የሚበተብተው ሥጋት አቅም አሳጥቶት እንጂ ፣ መምጣታቸውንስ ያወቀው ገና ሚስቱን ሲጣሩ ነበር ። በዝግታ ቀና ብሎ ፣ "እንዴት አመሸሽ እቴዋ ? ደህናም አላመ ሸሽ ?" አለ ራሱን በግራ እጁ ደግፎ ።

አስካደች ምድጃው አጠገብ ቆማ የመጡበትን ጉዳይ በንቃት ታዳምጥ ጀመር ። "ታሁን አሁን ትመጣለህ ስል ቅርት እልክ ።

ምነው ደህናም አደለህ እንዴ ?" አሉ ራሱን አሞታል እንዳልተባሉና ፣ ጭንቀታቸውን ውጠው ምንም ያልሆኑ በመምሰል ።

"አይ እቴዋ ፣ የዛሬውንስ አታንሽው ፣ ያንዳንዱ ቀን ጀምበር ነገር አላት ። አያድርስ ነው ። ባንዱ ስታመልጭው ባንዱ ያሳድድሻል። ንዴቱ ነው መሰል ራስ ምታት በቅቶ ይዞኛል" ብሎ ካልጋው ላይ ወረደ ።

"እኮ ተው በቃህ እንግዲህ እኮ ያንተ ነገር ፣ ካልጐለጐልከው አይሆንልህ ፣ እስቲና አንደዬ ብቅ በል !" ብለው ወደ ደጅ ሲወጡ ወዲያው ተከትሏቸው ወጣ ።

እስካደች የበሩን መቃን ተደግፋ ቆመች ። አፈሣና ሴትዮዋ አጥ ሩን ተጠግተው ሲቆሙ ፣ ሽዋርካብሽ ባጋጣሚ ልክ በዚያው በሁለቱ አቅጣጫ ካጥር ውጪ ቆማ ነበር ። የሚያወሩትን ሁሉ ልቅም አድ ርጋ መስማት ትችላለች ።

"ይኽን ውርጂብኝ አየህ ?" አሉት አፋቸው እየተርበተበተ ።

"ምን ማየት ብቻ — — እያው ነበርኩ እቴዋ" አለ በደቃቃ ድምፅ ።

"ተምርህ ነው እንዴ?" አሉት ደንግጠው ።

"እስቲ ዝም በይኝ እቴዋ ፣ የጦሰኛ ፈስ ዐይን ያፈስ" አለ በሲቃ።

"አንተ ምንዬ መጣህ?"

"የመቼሽን? ያመጣጤንማ ነገር አታንሽው ።"

"ምነው ታዲያ ብቅ አለማለትህ ልጄ? ታስባለችም አትል? የኔንማ ድንጋጤ አታንሳው — — — ሞቴን ባቀረበው — —"ብለው ተከዙ ።

"ለማ ብለሽ? ማባቱ እንዳይነካሽ——እረ—ንሱ!"

"የኔ ነገር ምን መላ አለው ፣ ጉዴ ተንተክትኮ!—ሞትማ በማን ዕድሌ?"

"ጤናም አደለሽ እንዴ እቴዋ ፣ ለምኑ ነው መጨነእሽ ?!" አለ በይስሙላ ኩራት ።

"ተዚህ የባሰ ነገር ምን ይመጣ ብለህ ? ቤቱን ያምሱት ይዘዋል ።"

"ማን?" አለ ግር ብሎት ።



"ሌላማ ማ ፣ ያለሳቸው?"

"ቀኛማይ? ደሞ ምን ልሁን አሉ?"

"ከኔጋማ ገና አልተገናኘንም ፣ ያቺን ሽዋርካብሽን ሲያትረከርኳት አመሹዪ!"

"እሷን ደሞ ምን አርጊ ብለው? "

"ቲጠይኡዋት ነዋ— ያልሰሙት መከራ አያስጨንቅ ።"

"ምን አረግሽ ብለው?"

"ያገኙትን አግኝተው ነዋ—የያዙትን ይዘው..."

"ምን ተገኘባት?"

"እሷማ ምን ይገኝባታል ፣ የተገኘብንስ እኛ ።"

"እ!እኛ ደሞ ምን ይገኝብናል—ምን ተገኘ እቴዋ?"አለ ደንገጥ እያለ ።

"ሌላማ ምን ይገኝብናል!— ያ መዘዘኛ አገልግል— አነስ ብለህ ነው?"

"የምን አገልግል እቴዋ?" አለ ልቡ እየደወለ ።

"ሽዋርካብሽ ያቀበለችህ አገልግል ነዋ! አልሰጠችህም እንዴ?"

አገልግሉም ቦታውም ትዝ ስላለው ድንጋጤው በመላ—አካ ሉ ተሰራጨ ።

"እሷማ ሰጥታኛለች እሳቸው ታዲያ ተየት አገኙት?" አለ ሁለ መናው እየራደ ።

"አይ አንተ ፣ እኔማ የት አባቴ ዐውቄ! እኔስ ገና በተራዩ ሳልጠየእ እቀራለሁ ?"

አፈሣ በድንጋጤ አፉ ከበተ ። ውስጡም እንደ ደጁ ጨለመበት ። የሱም ነፍስ እንዳገልግሉ ቀኛዝማች እጅ የገባች መሰለው ። አሞቱ ፈሰሰ ። ልቡ ቀዘነ ። ሽዋርካብሽ ካጥር ውጪ ቆማ አገልግሉን እንደ ተቀበላት ሲያምን በመስማቷ ጎንበስ ብላ መሬቱን ሳመች ። ዳግመኛ የተፈጠረች መሰላት ።

"እንኳን ከኔ ላይ የወረዱልኝ ፣ አልሰጠችኝም ቢል ምን ይውጠኝ ነበር ። አይ የናት አባቴ ውቃቢ ! ከጉድ አወጣኝ !! ይቺን አፉን

እሳቸውም ፊት ባይለውጥብኝ” ብላ በደስታ ተፍነከነከች ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱና አፈሣ ግን ፣ መሬት ጠባቻው ተፋጠጡ ።

“አንተ አገልግሉን ተሸብለህ ለማ ሰጠኸው ?”

“ለማ እሰጠዋለሁ እቴዋ ፣ ባደራ እሚሳከም እኮ አደል!”

“ወስደህ የት አረከለት ?”

“እንዴ!? ደህናም አደለሽ እንዴ እቴዋ ፣ እያው ገንዳ ውሃ ሔጀ ሰጠሁታ!”

“እዚያው አብረህ አልቆየህማ?” አሉት በትዝብት ።

“ምን አረግ እቆያለሁ?—አንድ ሁለቴዬ እንደ ጐራረሰ ተመለስኩ ።

“ይኸ ሁሉ ጉድ ቲፈጠም አልነበርከማ?—አላየህም ?”

“እያልኩሽ እቴዋ?—ሒድ ግድ የለም ሲለኝ ተመለስኩ ፣—እዚያማ ብኖር ኖሮ — —”

“ኧረ እንኳንም አልቆየህ ፣ ይኸ ጉደኛ ቢያይህ ኖሮ — — አበስ ገበርኩ! ቢያገኝህም አይምርህ ነበር ፣ ሮጠህ ብታመልጥም ጣጣ ነበር። የኔ ጊዮርጊስ የት ኬዶ — —”

አፈሣ አገልግሉን ትቶ መሸኙን ልቡ ካወቀ ጀምሮ የክህደት ብልሃት ማውጠንጠን ጀምሯል ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ እስከ ነገሩት ድረስ ግን ፣ ባለማወቁና መርሳቱም ትዝ ስላላለው ከደረሰው አደጋ ሌላ ፣ ጭንቀት ሳይፈጥርበት ቆይቷል ።

“አገልግሉን ያገኙት እዚያ መሆኑ ነዋ?” አሉ በመገረምና በማዘን ።

“ማ ይሰጣቸዋል እቴዋ? በየት በኩል ያገኙታል ?”

“የዋዛ ሰው መስለውሃል ፣ እሳቸውም ያልታወኡ ሽፍታ ናቸው ። እኔ መች አጣኋቸውና ያደባበትን ሲፈልጉ ይሆናል! ኋላማ አገልግሉን እንግቶ አይታኮስ?——”

“ጠርተው ከጠየኡሽ የኛ አደለም በያቸው!”

“ኡኡቴ! አይ ያንተ ነገር ፣ አገር ማገር ያየውን ነው የኛ አደለም እምላቸው? አሁን ወዲያ ቢሉት ወዲህ ቢሉት ምን መላ አለው ብለህ ነው? በየህ ላይ ያቺ አላኳሽ ዘመዳቸው ትክልክል አርጋ ነግራቸዋለይ ፣ አሁን ምን ይብጀኝ ነው እምልህ” አሉ ።

ሸዋርካብሽ ካጥር ውጪ ወደ ሰማይ አንጋጣ ፣



“አሁን እንደግዜር ማ ደግ አለ!?” ብላ ከንፈሯን መጠጠች ።

“ስንት ገቢና ወጪ አለ? ሰው ሲገፋ ነው እሚውለው ፣ ለምን እኔ ስንቱን የቤት ኩተት ዐቃለሁ ብለሽ አትክጂም! — አላየሁም አትያቸውም ! — — ”

“አንተ ደሞ ቲነግሩህም አይገባህ ልጄ! ምንስ ጠፋኝ ብውል የገዛ አገልግሌን አላኸውም ልበል? ምን ትሠሪያለሽ ቢሉኝስ ፣ አገልግሉን ሳንተ ማኸበሏን ዐውቀዋል እኮ ነው እምልህ ። አሁንማ አረረም መረረ ካንተና ከኔ ጀርባ አይወርዱም ። የኔ ጊዮርጊስ ብቻ በመያዣው ይያዝልኝ” ብለው ራሳቸውን ነቀነቁ ። ተስፋቸው ሁሉ በነነ ።

“ሸዋርካብሽን ጥፊ በያት!”

“አይይይ! ኤዲያልኝ ኤዲያ! ‘ቂል አይሙት እንዲያጫውት’ አሉ ወይዘሮ ይመናሹ ። እንኳንና ጠፋች ሞተች ቢባሉስ ምን ያረጋል። ተጠይአና ተናግራ በእቷታል” አሉ በልባቸው ከፉኛ እየጠሉት ። “ምነው አንተንም አጪሶህ በነበር!” አሉ በሆዳቸው ።

“አቤት እኔ! ብላ—ብላ ሞቴን ተመኘችልኝ?! ምነው የዚችን አገልግል ጉድ ባወኳትና ልቅም አርጌ በነገርኳቸው ። አዳሜ ሥር— ሥሩን ነገር አላት” አለች ሸዋርካብሽ በለሆሳስ ። በጣም ተናደደች ። አገልግሉን ወስዶ ለማን እንደ ሰጠው ለማወቅ ባለመቻሏ ቆጫት ።

“እንግዲያው እንዲህ እናድርግ” አለ የሸሸው ሽሽት እየታየውና የሚለው እየጠፋው ።

“እንዴት?” አሉ ዘዴ የተገኘ መስሏቸው ።

“አገልግሉ የማነው ቢሉሽ የኛ ነው በይና ፣ ለኔ ታይናገሩ ስንትና ስንት ዕቃ ለመንደርተኛው ሁሉ ያውሳሉ ብለሽ የተገላቢጦሽ ቱግ በይባቸው ። የሰሙትን ሁላ ቲናገሩ ዝም ብለሽ እህ በዪና አስጨርሻቸው ። እንኳንም ቀድመሽ የሰማሽ ። ለካ የገዛ ዘመዶቼም አይተኙልኝና ፣ እየሁ እቤቴ ተኸምጣ ትዳሬን ልትበትንብኝ አፏን አጣፍጣ ፣ እቴሜቴ እቴሜቴ ትለኛለይ ፣ ደሞ ከኔ ዐልፋ —ተርፋ እድሃው ዘመዴ ላይ መንጠልጠሏ ብለሽ ዱር በይ ። አለቅጥ በቅተው ታስቸገሩሽ ደሞ ሀብቴን በቁር ጤታ አካፍሉኝ ፣ በሆነ ባልሆነው አትነዝንዙኝ በያቸው ። ምንድነው ይህን ያክል ! ‘እንክንክ ያሏት ሙጀሌ የቆላ ቁስል ትሆናለች’ አሉ” ብሎ መልካም ሐሳብ ያቀረበ ይመስል ተኩራራ ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ግን እንኳንስ ምክሩ ፣ አነጋገሩ ተናነቃቸው ። ስንኳንና አሁን እንዲህ የነገር ውስ ተጐልጉሎባቸውና

ቅስማቸው ደቆ ፡ የሚያስቡት ምክንያት ሁሉ እንደ ጢስ እየበነነ ባስቸ
ገራቸው ጊዜ ቀርቶ ፡ በደህናውም ሰዓት ቢሆን ከቀኛዝማች ጋር የነገር
እንካ ስላንቲያ መግጠም አይወዱም ።

"ኧረ ወዲያልኝ ! ደም ሰው ነህ ብዬ መምጣቴዬ ! የሰው ወንድ
ነት ይዘህ ባታምኘኝ ፡ እማይባለውን ሁላ በዬ እምትለኝ — ዐውራ—
ጣታቸውን አይጠቡ — —"

ሸዋርካብሽ ካጥር ውጪ "ሙቻታለኋ ! አሂሂሂ ! እናንተ ጉዳች
ሁን ልደባብሉ ድሃዋ የኡም ስእሴን ላይላችሁ ! ደም ዕቃ ታውላለች
ተባለልኝ ! ወንድ ተሆነ ነይ በይ እንሒድ ብሎ አይነግራቸውም ? ሴት
እውል የሰው ሴት እውል ! አጥር ሥር ተወትፎ ዐሥሩን ተመኽባጠር ይኸ
ነዬ አይበረታላትም ? ይኸነዬ እንዲህ የተትረኸረኸው የሠራት ሥራ
ብትኖር ነው ! ተደብአ አትቀር" አለች አፏ ሳይላወስ ።

"አሁን አጅሬን በዚህ ለማወጫበር ነው? እማይመስልነገር! ነገር
ነው ሲያገላብጡ እሚውሉት ፡ እንዲያው ለምናልባቹ ጠርተው ተጠ
የቁህ ፡ እንዳላወክና እንዳልሰማህ ሁንና ፡ አስካደይ የቤቶቿን ልጠይእ
ሒዳ ፡ ቅርት ስትልብኝ ጊዜ አዳሬን ቆላ እወርዳለሁና ትንሽ እን
ጀራ ባገልግል ቋጥሪልኝ ብዬ እቴዋን ነግሬያት በሌላ አገልግል ልካ
ል ኛለቺ በዚህ አንቱ በምትሉት አገልግልም አደል በላቸው ። የታል
አገልግሉ እንዳይሉህ ፡ አንድ ባዶ አገልግል እልክልሃለሁ ። ምንም
ቢሉህ ቃልህ ይቺው ትሁን ። ተዚህ የበለጠ ሌላ ብላት እናገኝም—
በል ግባ ያቺ ጊንጥ ዘመዳቸው ደግሞ ይኸነዬ አበጃጅታኛለች" ብለው
ወደ አጥሩ በር ሲሔዱ ፡ ሸዋርካብሽ ሴትዮዋ የሔዱበትን ጉዳይ ጨር
ሰው መመለሳቸው እንደሆነ ገባት ። ከመከተል ይልቅ ራቅ ብላ መቅ
ደምን ስለ መረጠች ፡ ተረከዟን ወደ ላይ ከፍ አድርጋ በእግሯ ጣቶች
እየረገጠች በጨለማው ውስጥ ገሠገሠች ።

ሴትዮዋ የተስፋ ከረጢታቸውን አራግፈውና የተሸበረ ልባቸውን
አባብሰው ከአፈሣ ግቢ ሲወጡ ፡ ባዶ እጁን ተከተላቸው ።

ሸዋርካብሽ ዘወር ብላ እያየች ስትገሠግሥ ፡ የአካሉ አብዛኛው ክፍል
መሬት ውስጥ ተቀብሮ ሰያፍ ጫፉ ያገጠጠ ድንጋይ ፡ አውራ ጣቷን
መነገለው ። ነፍሷ ሱር አለች ። እንቅፋት ያነሳዳትን ጣቷን ጥርቅም
አርጋ ይዛ ላፍታ ያህል እፍ አለቻት ። ካውራ ጣቷ ሕመም ይልቅ
የልቧ ሽብር በማየሉ 'በል አፍክን ያዝ'ተብሎ እንደ ተቀጣ ልጅ ሕመ
ሟን አፍና ገሠገሠች ። በራቀች ቁጥር በመካከላቸው የነበረው
የጨለማ ጥልቀት ደነደነ ።

አፈሣ ጥቂት እንደ ሸኛቸው "እቴዋ !" አለ ከበስተኋላቸው እንደ
ጅራት ተለጥፎ ።



"ምነው ?" አሉት ፡ በልባቸው ግን ፡ "አንተንስ ያንሳህ ! አልጫ !
የሰው አልጫ ! ሙትቻ ! አሁን አንተም እንደ ወንዶቹ... አንጠልጥለህ
ይሆናል ?! ወይኔ ልጂት!" እያሉ ።

"አገልግሉን ያ ጉደኛ አይቶት ይሆን እንዴ ?"

"ማን?"

"ሌላማ ማን ያ የሳቸው አቶክቷኪ ነዋ!" አለ አሁንም ምንዳዬን
አልጋው ላይ ለመግደል በልቡ እየተመኘ ።

"ምንስ ቢያመው ፡ አገልግል ተገኘ ሲባል መስማቱ ይኸራል ብለህ
ነው? ባይሰማስ የገዛ ባልንጀሮቹ ይነግሩት የለ?! አጀብ—እቴ! እኔ
ያላንተ የበደለኝ የለ ። እቂጥ—እቂጡ ብትል ፡ ተሰውዬው ጋ ተለጥ
ፈህ ጀሮ ጥላውን ብትለው ኖሮ ይኸነዬ እርፍ ግልግል ብዬ ነበር ።
አንተ ታዲያ በየት ። እንደ ድውር አድራሽ ፡ አድርሰህ ከተፍ አልክ
ልኛ!"

"አሁንስ ለምን ምናምን ፈትፈት አርገሽ አታጉርሺውም — —"
ብሎ ሊቀጥል ሲል ፡

"በል ይኸን አፍክን ያዝልኝ! ነገርህ ሁሉ እሬት—እሬት አለ!
እዱር አልሆንልህ ቲልህ እምድጃ ሥር ደሞ መጣህ!? አበስ ገበርኩ
እቴ! ለዚህ ለዚህማ እኔ መቸ መካሪ አጣሁ ። ነገረ ሥራህም አላማ
ረኝ" ብለው ፍጥነታቸውን ጨመሩ ።

የአፈሣ ስሜት ቀዘቀዘች ። አፉ የተወተፈ እግሩ የታሰረ መሰለው ።
ጥቂት ርምጃዎች ሔዶ ቆመ ። ዕቃም የወደቃቸው አልመሰላቸው ። ይሳ
ካል ብሎ ያመጣው መዘዝና የሚያስከትለው ጣጣ እንደ አዳል ግመል
እየተንተተ ተርታውን ሲመጣና ፡ ምንዳዬም ቢሆን ይኸን ሁሉ
ነገር ካወቀ ከቶ ምንም ቢደረግ እንደማይለቀው ወለል ብሎ ታየው ።
እዚያው ቆሞ ሲያወጣና ሲያወርድ የተለያዩ ሐሳቦች ድቅን አሉበት።
ሲፈራ ሲቸር አንዱን ሐሳብ ጨምድዶ ትንቅንቅ ገጠመ ። በምንዳዬ
ቤት ላይ ጥርሱን ነከሰ ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

ሸዋርካብሽ ፥ በጓሮ በር ሹልክ ብላ ገብታ ዐውራ ጣቷ አዲስ ቁስል ላይ ዐመድ ነስንሳ ፥ ደም መጥጦ ያልተላከከውን እፍ እያለች ስታራግፍ ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ገቡ ። ዐውራ ጣቷን በምድጃው ጥላ ከልላ ቆም አለችና ፥

"እቴሜቴ!"አለች እሳቸውን ሳይሆን ጥላቸውን እያየች ።

"ምነው፣ ደሞ ምን ቀረሽ?" አሏት በግልምጫ ።

"ቲፈልጉሽ ነበር" አለች በሰባራ ድምፅ ።

"ማ?"አሉ ፥ በማን እንደሚፈለጉ እየታወቃቸው ።

"እሳቸው ናቸው" አለች 'ስማቸውን ቄስ ይጥራው' እያለች በልቧ ።

"አሁን ነው ቆዩ?" ብለው ወጡ ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፥ ካዳራሹ ወጥተው በስተጓሮ እግቢው መኻል ቆም አሉና ፥ ጐራ ወደ ከለለው ሚካኤልና ፥ አሻቅበው ወደሚያዩት ሣር—አምባ ጊዮርጊስ አዩ ። ችግራቸውን ለማንኛው እንደሚነግሩ ሐሳባቸው ዋለለ ። ትዝ ሲላቸው ለካ ሚካኤል የቀኛዝማች ምስጢረኛ ኖሯል ። እየፈሩ ፊታቸውን አዞሩና ወደ ራሳቸው ሰማዕት ወደ ጎርጊስ መለስ አሉ ። "እስኪ ምኗ ካዲያን ነኝ እስተዛሬ ያለሱ አለሁሽ ያለኝ ማን አለ? እንዲያውም እሱ ሰው ነበር አሉ ። የሰው ችግር ይገባዋል ። የኔ ጎዮርጊስ አንተው ታእልኛለህ" አሉት በመዋለላቸው እየተጸጸቱ ። ማርያምንማ በሴትነቷ" ምን አቅም ይኖራታል ፥ እሷም ቢሆን ገና ለምና ነው" በሚል ግምት ፥ ሥላሴዎችን "እነሱም ቢሆኑ ያው ለወንዶች ታያደሉም አይቀሩ ። ሽማግሌው ሁሉ እሚያዳላው ለወንዶች ነው ። በያ ላይ ደሞ ሦስት ናቸው ። ሁሉንም ከመለመን አንዱ ጎርጊስ ይሻላል" በሚል እምነት ብዙም አይማጠኗቸው ።

"አይይ! !" አሉ እንባቸው እየተንቆረዘዘ ። "እስኪ የኔ በደል ምንድነው፣ እስኪ አንተ ፍረድ! አንተው ፍረደኝ ፥ ምን አባቷ እንዳታረግ ብለው ፥ በላዬ ላይ ሴት ያዙ ፥ የለፋሁበትንና የደከምኩበትን እየወሰዱ ሲሰጡ ፥ ላንተው ነግሬ ዝም አልኩ ። ይባስ ብለው እኔን እንደ

ቀብር ዐፈር እያድፋፉና ችላ—ችላ እያሉ ያዳሜን ጋለሞታ ይዤ ታል
ሔድኩ አሉ ። ላንተው ነግሬ ዝም አልኩ ። ምን አባቷ እንዳታረገኝ
ብለው የገዛ ሎሌዩን ነገር አመላላሻቸው አርገው በገዛ ቤቴ ያንን
በግቡኝ ጀመር ። ተነገ—ዛሬ ልብ ያበጃሉ ፣ እትልእ ሥርፋ ሊውሉ
ነውና ይተዋሉ ብል ቲብስባቸው ጊዜ ፣ አንጀቴ ድብን ብሎ ይኸው
አይገቡ ጣጣ ገባሁ ። አንተ እማታኸው ምን ነገር አለ" ብለው ግዙፍ
የጨለማ ክብር የመሰለውን የሣር—አምባ ጊዮርጊስ ተራራ እንጋጠው
እያዩ አለቀሱና ፣ "ኧረ ተው! እውነቱን ፍረድ! ኧረ ተው አሳየኝ!
አሁን ተዚያ ተዘንዶ የኚህ ታይብስ ቀርቶ ነው፣ ችላ ያልከኝ"ብለው
ከዚያ ቀደም ከተሳሉት ስለት የበለጠ ተስለው ወደ እልፍኝ አመሩ።

በየብስጭታቸው ጊዜ ሁሉ የተሳሉትን ስለት በልቦናቸው ይዘው
ማስታወስ ስለማይችሉ ፣ ተኝተው በቅዠታቸው የተለያዩ እራዊትና
እንስሳት ካዩና ካሯሯጧቸው ፣ "ደሞ የማንኛው ስለት ተረስቶ ይሆን?"
በማለት በየአምባው ያሉትን ታቦቶች በሐሳብ ያስሳሉ ። ጥርጣሬአ
ቸው ወዳጋደለበት ታቦት ፣ ወይ ከዕጣኑ ፣ ወይ ከስንዴው ይልካሉ ።
ከማንኛውም ጉዳይ ይልቅ በወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ላይ የተሳሉት ስለት
ከሁሉም ይበልጣል ። የጣውንታቸውን ጉዳይ ረጋ ብለው ባስታወሱ
ቁጥር በጣም ላጭር ቅጽበት እንኳ ቢሆን የወላጅ እናታቸው ሥራ
ትዝ ይላቸዋል ።

ብዙ ጊዜ ወላጅ እናታቸውንና ጣውንታቸውን በተመሳሳይ ዐይን
ስለሚመለከቱ ፣ የገዛ እናታቸውንም በጥላቻ ትዝታና ስሜት ያስታውሷቸ
ዋል ። የወይዘሮ እልፍ ይከንዱ አባት በወረርሽኝ በሽታ የሞቱት እሳቸው
ገና የስምንት ዓመት ልጅ ሳሉ ነበር ። እናታቸው ጸጉራቸውን ተላጭ
ተው ፣ ማቅ አገልድመውና ፣ መሬት ላይ የበግ ለምድ አንጥፈው
እየተኙ ከሁለት ዓመት በላይ ተኮራምተው አዘኑ ። የባልና ሚስቱን
መዋደድ የሚያውቁ የባልየው ዘመዶች 'ከዚህ በላይስ ይበቃታል'
ከሚሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ ። በመጨረሻም 'ተንግዲህስ ወዲያ ደግ
አደለም ፣ አጥንቱም አይወቅስሽ ፣ ነፍሱም አይከስሽ' ብለው ሐዘ
ናቸውን እንዲተዉ ገፋፏቸው ። የገዛ ዘመዶቻቸውም ፣ "ምንድነው
እቴ ፣ አሁንስ በዛ! ማ ጎኝ ይለኛል ብለሽ ነው? ተነሥቶ አያይልሽ
ነገር ፣ ሰው ሒዶ እንዲህ ያለች ውለተኛ ናት አይለው ነገር — — —"
ብለው ስለ ወቃቀሷቸውና ስለ ተቆጧቸው ፣ በሐዘን ተጨብጦ የነበር
ልባቸው ላልቶ ፣ የተጎሳቆለ ገላቸው እየሞላ ሔደ ። ብዙ ወንዶች በተ
ለያዩ አጋጣሚዎች ለትዳር ጠየቋቸው ። የወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ
እናት ግን ፣ 'ከሟቹ ባሌ የማይስተካከል ከሆነ እንዲች ብዬ አላገ
ባም' ብለው የመጡትን ሁሉ በሰበብ አስባቡ መለሱ ። ጠይቆ
የተመለሰው ወንድ ሁሉ ፣ 'ይቺ ሴትዮ ምንድነው ብልሃቷ!? ቆብ



ታጠልቅ ከጀላት እንዴ?' እስከ ማለት ደረሰ ። 'እኔ ልጂት ከማ
ንም ሎግኒ ጋር አልነፋጠጥም ። ቢያስቀዝንም ጮማ' ብለው እጅ—እግ
ራቸውን ሰብስበው እንደ ተቀመጡ ፣ ዝናቸውን የሰሙ አንድ የሳፍራ
ባላባት ደም— ግባታቸውንና ቁመናቸውን አይተው ስለ ወደዷቸው ፣
እምቢ የማይባል ዘመድ ባማጭነት ልከው ፣ በልጆቻቸው እናት
ላይ የወይዘሮ እልፍ ይከንዱን እናት በቅምጥነት አስቀመጧቸው ።
ባዘዙ ቁጥር እህል በያይነቱ ፣ ዓውደ—ዓመት በመጣ ቁጥር ሙክቱ ፣
ነጭ ከመያዣ እያቀረቡ በክብካቤ አኖሯቸው ። ሴትዮዋም ቢሆን በሙ
ያቸውና ባልጋ ላይ ችሎታቸው ተጠቅመው ፣ ሰውየውን እንደ ኩቲ
ጠርተው እንደ ላም አለቧቸው ። በመጨረሻም ከቆዩ ትዳራቸው አፈ
ናቅለውና አጣልተው ጠቀለሏቸው ። ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ያንን ሁሉ
የእናታቸውን ድርጊት አንድ ባንድ ያስታውሳሉ ። ሰውዬውን ለመጠቅ
ለል ሲሉ ያደረጉትን ጥረት ፣ የሠሩና ያሠሩትን ተንኮል ፣ የደረሱበትን
ጠንቋይና የገቡበትን ደብተራ ፣ 'እህ' ያሉትን የወሬ አመላላሽ ብዛት
ያውቃሉ ። ይህ ከሆነ አያሌ ዓመታት ቢያልፍም ትዝታው ግን
አልጠፋም ። የገዛ እናታቸውን ድርጊት እያሰቡም ጣውንታቸውን ፈርተ
ዋል ።

በቀኛዝማች የሚፈጸምባቸውን በደል ሁሉ ከእንጀራ አባታቸ
ቸው ከኃዲነት ጋር በማነጻጸር ፣ "አይ ልጅነት ፣ እኔ ደህና ሰው ይመ
ስሉኝ ነበር ። ለካስ ጉዳቸው ሁሉ አልገባኝም ኖሯል ። ዘልዛላ የሰው
ዘልዛላ! ያ መሳይ ቁመናቸው ቅሌት ብቻ ኖሯል" በማለት በወይ
ዘሮ ደጅ ይጥኑ ምክንያት በተናደዱ ቁጥር ከእንጀራ አባታቸው
ሚስት ጋር በዛሬው ሐሳባቸው በማበር ወላጅ እናታቸውን ያወግ
ዛሉ ። ዐልፎ ዐልፎም ፣ 'የሷ ጡር ቀኑን ጠብቆ በኔ ላይ ደረሰ' በሚል
እምነት እናታቸውን ይራገማሉ ። በዚህም ምክንያት ከእንጀራ አባ
ታቸው ሚስት ዕጣ ለመዳን ሲሉ ፣ በጣውንታቸው በኩል ያለውን
ነገር ሁሉ በእልህና በበቀል ተያያዙት ። ወደ እልፍኝ የገቡትም
ከዚህ ትዝታ ቁንጣሪና ከተረበሸ አእምሮ ጋር ነበር ።

## ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

ሣር አምባ የዋለ ሰው ወደ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ቤት ጐራ ብሎ የሰማውን ሁሉ ነግሯቸው ሳለ ፣ ልብ ብሎ እንዳላዳመጠና በምን ግዴ እንደሰማ ሰው ፤

"ማን ነው የሞተው?" አሉ እንደገና ከድንጋጤአቸው መለስ ብለው።

"የየት አገር ሰው እንደሁ አልታወኸም መሰል"አላቸው ሰውዬው።

"ይኽ የኛስ ተጐድቶ ይሆን" አሉ ረጋ ብለው ።

"ታይጐዳም አይቀር ።"

"እሚያሠጋው ይሆን እንዴ!" አሉ ትኩር ብለው እያዩ ።

"የጌታን ነገር ማን ያኽዋል — እሱ እንዳለ ነው" አለ ወደላይ እያየ ።

"ቀኛማችስ ?"

"ምነው ነግሬሁ ፣ እሳቸው ምንም አልሆኑ ፤ ያው እሱ እፊት— እፊት ቲል ተጐዳዪ ፣ የሱ መኖር ነው የበጃቸው ፣ አለያማ የዛሬዋ ጥይት የሳቸው ነበረች ።"

"እሳቸውም እሚወዱት ለዚህ ነው፤ እንኳን ጠላትን ደስ ያላ ለው ። ሺ—አውል ከሚሞት ሺ—ይሙት ይባል የለ !" ብለው ብድግ ሲሉ ሰውዬውም ተሰናብቶ ወጣ ። እሳቸውም የጎረቤት ሰው እስከ ትለው ወደ ሣር አምባ ገሠገሡ ። የመንደሮቹ መቀራረብ ጠቀማቸው። እንደ ደረሱም የቤቱ አቀማመጥና የአደጋው መጠን በቅድሚያ እን ዲገቡ ወደሚያስገድዳቸው ወደ ምንዳዬ ቤት ገቡ ። የነበሩትን ጥቂት ሰዎች መስቀል አሳልመው ፣ ስለ ደረሰው አደጋ እንደገና ጠይቀው ተረዱ ። በተደጋጋሚ ከንፈራቸውን እየመጠጡ ተቆርቋሪነታቸውን ከገ ለጹ በኋላ ፣ አደጋም ሆነ ሞት በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚመጡ ፣ ሰውም በጠላቱ ላይ ድል የሚቀዳጀው በሱው ፈቃድ መሆኑን ባጭሩ አብራርተውና አጽናንተው ወደ ቀኛዝዝማች እልፍኝ አመሩ ።

እንኳን አተረፈሁ ከሚሉ ከሁለት ሽማግሌዎች በቀር ሌላ ሰው አልነበረም ። እዚህም ከቀኛዝማች በመጀመር መስቀል አሳልመው ፣

ከፍ ባለ አዛኝነትና የሃይማኖታዊ አባት ስሜት ቁጭታቸውን ገልጸው ፣ አምላክ የወዳጆቹን ጽናት ለማወቅ ዐልፎ ዐልፎ በዚህ ሁኔታ እንደሚፈትን መጠቃቀስ እንደ ጀመሩ ፣ ሁለቱ ሽማግሌዎች ፣ "በዚሁ ያሳልፈው ፣ የዛሬን ጥላ ከለላ ሁኖኋል ፣ ለወደፊትም ከከፉ ነገር ይከልልሁ ፣ እሱንም የውሻ ቁስል ያርግለት" ብለው ሔዱ ።

ቀኛዝማች ፣ ያን ብዙ ምስጢር አለበት የሚሉትን አገልግል ወደ ጎን ብለው ፣ ከዕለቱ ሁኔታዎች መካከል ገና የሚያጣሩትን ቸል እያሉና ፣ አልፎ አልፎ አንዳንድ ድርጊቶችን እየዘለሉ ፣ "ይኸ ነገር የታሰበው ለኔ ነበር" የሚለውን የግል ጥርጣሬአቸውን እያጎሉ ፣ የምንዳዬን ጉብዝና እንደ ራሳቸው ጀብዱ እያስማመሩ አወሩላቸው ። ቀኛዝማችን እጅግም መቃወም የማይሆንላቸው ቄስም ፣ ጉራና ጥርጣሬውን ፣ እውነትና ውሸቱን ሁሉ ፣ ትክክለኛ ነገር እንደሰማ ሰው ራሳቸውን በአዎንታ እየነቀነቁ አዳመጡ ።

ቄሱ በዚያ በጨለማ ገስግሰው በመምጣታቸው በቀኛዝማች በኩል ምን ያህል እንደሚያስወድዳቸውና እንደ ታላቅ ውለታም እንደሚታይላቸው ልባቸው ያውቃል ። ቀኛዝማችም ያን ዕለት መጥቶ የጠየቃቸውንና ምንዳዬ ቤት እየደረሰ የሔደውን ሰው ልብ ብለው እያዩ ፣ ሌሎቹንም ማን እንደ መጣና ማን እንደቀረ ተመልክቱ ብለዋል ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስን ተማፅነውና 'አደራህን' ብለው ወደ እልፍኝ ሲገቡ ዐይኖቻቸው ባለቤታቸው ላይ ተሰኩ ። በጭንቀት ማዕበል የተናወፀው አእምሯቸው ያይናቸውን ንቃት ቢቀንሰውም ፣ እዚያው ከቀኛዝማች አጠገብ ቄሱንም አዩዋቸው ። ሁሉም ነገር አስጠላቸው ። በተለይም ከቀኛዝማች እግር አጠገብ ያለውን አገልግል ሲመለከቱ ፣ ሲሰርቅና ሲዋሽ እንደ ተደረሰበት ሰው ዐይንና ቅስማቸው ተሰብሮ ደነገጡ ። 'እንኳንም የመጣሽልኝ ! እረ በምን አበሳዬ ነው እንዲህ መንገላታቴ ! እነማን ሲቀባበሉኝ እንደዋሉ አንድ ባንድ እናገር የለ?!' የሚል መሰላቸው ። የጭንቀት ሃዕር አነቃቸው ።

"ደህና አመሸሽ ወይ? ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ" አሉ ቄሱ በርጋታ።

"እዝጊሐር ምስጌን ፣ እንዴት አመሹ አባቴ? ምነዬ መጡ ?" አሉ ወደሳቸው እያመሩ ።

"ጥኢት ቆየት ብያለሁ ፣ ምንዳዬ ጋ ገባሁና 'እንኳን እግዚአብሔር አተረፈህ' ብዬ ፣ ዋናው ሥጋቴ ደግሞ እዚሁ በመሆኑ መጣሁ ። —— በጎ ሰነበሽ ወይ?" ብለው ከጀጠባባቸው ደረት ኪስ በቀይ ግምጃ እራፊ የተሸፈነች ፣ ቡናማ ላብ — ጠገብ የንጨት መስቀል አውጥተው ሲያሳልሟቸው ፣ እንደ ወትሮው 'ይፍቱኝ' እንኳ አላሉም።



ቀደም ብለው ከልፍኝ ውጪ ሁለመናቸውን ለዚያው ለጊዮርጊስ በማስረከባቸው ፣ በቄሱ መስቀልና አማላጅነት የሚተላለፍ መልዕክት አልነበራቸውም ።

"ምነው ታዲያ ተመሸ ፣ ነገም እኮ ትደርሱ ነበር" አሉ ከፊል ልባቸው 'እንኳን መጡ' እያለ ።

"እንዴት ብሎ ሊነጋልኝ? አሳቡም አያሳድረኝ ፣ ቲጨነቁ ተማደርስ ይኸ ይሻላል ። እናንተ እንኳ አትቀየሙኝም ። እሱ ግን ፣ አንደዬ ከተቀየመ ሆዱ በቀላል አይፈታም ። ላንድ አፍታ መንገድ ብዬ ከሚያዝንብኝ እንዲህ መምጣቱ ይሻለኛል ። ቀስ ብዬ መስቀል ሳሳልመው እንኳ ደስ ብሎት አየኝ" አሉ ደስ እያላቸው ።

"እሱስ እውነኩን ፣ ፣ ደግ አርገኋል" ብለው ፊንጠር ብለው ተቀመጡ ።

"—— ምን ነበር የጀመርነው ወሬ ፣ አልጨረሱልኝም እኮ?" አሉ ቀኛዝማች ።

"—— አዎ ፣ አልጨረስኩልዎም ፣ እንዴት አመሸሽ ልበላት ብዬ ነው ልጄን ።"

"ውይ! ዐፈር በበላሁት ! —— አይ የኔ ነገር! አቋረጥኳችሁ ?"

"እረ ጠላትሽ ዐፈር ይብላ ! ምን በወጣሽ ! እንዳይጠወልግ ነው እንይደርቅ ?" አሉ ቄሱ ። የወሬው መቀጠል በጠንቀኛው ዕቃ ምክንያት የሚጀመረውን ንትርክ የሚያዘገየው በመሆኑና ፣ በተጨማሪም በመካከሉ ራት ቀርቦ ሌላ አዳዲስ ጨዋታ ስለሚቀጥሉ ፣ እንዲያው በባዶ ሜዳ በመጠኑ ደስ አላቸው ። ገደብ የለሽ ምኞታቸው ፣ ከዚህ ዐልፎ ፣ ራት ሲበላና የተንተተ ወግ ሲወጋ በጣም ይመሽና ፣ ስላገልግሉ ሳይነሣ ያድራል ። በማግሥቱም የምንዳዬና የሚቹ ነገር ስለሚኖር በዚህም በዚያም በመዘግየት ፣ በችላ—ችላ መረሳቱ አይቀርም በማለት ፣ ልባቸው እንደገና ረጋ ፣ አእምሯቸው ባጉል ተስፋ ተንፈስ አለ ። ወዲያው 'የተቋረጠው ወሬ ስለምን ይሆን'በማለት ቢሠጉም ፣ ከጥቂት ድምጫ በኋላ ግን ፣ ዱሮ ደርሶ ስለነበር ተመሳሳይ አደጋ መሆኑን ስለተረዱ ቀለል አላቸው ። ያም ሆነ ይህ እሳቸውንም እንደ አፈሳ ወስድ—መለስ ያደርጋቸው ጀመር ።

ሌላ አዲስ ወሬ ከመጀመሩ በፊት ፣

"ጥሯት ብዬ ልኬብሽ ነበር ፣ አልነገሩሽም ኖሯል እንዴ ?" አሉ ቀኛዝማች ፣ በርጋታ ከያዛቸው የሐሳብ ሰመመን ነቁና ።

“ቢማሽልን ብለን ፤ እምንዳዬ ቤት ቡና ተፈላና ፤ ያቺ እቴዋ ስንዴይቱና ጋሼ አፍራሳ ወሬ ጀመሩልን ፤ አቋርጣብን ሔደች ይሉኛል ብዬ ሳልወድ የግዴን ቆየሁ ፤ እሱ ደሞ ወሬ ተጀመረ ፤ ክፉ አመል አለበት አውርቶ አያበራም ።”

“በሉ እንግዲህ እህል ውሃ በሉንና እንተኛበት — በጣም መሸ” አሉ ቀኛዝማች ። ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ወደ አዳራሽ ሔደው እረጋሽና ሽዋርካብሽ ራት እንዲያቀርቡ አዝዘው ተመለሱ ። ፍርሃትና ሥጋት ባጣደፈው ስሜት ጭምር ተፍ—ተፍ ብለው እጅ አስታጥበው ራት አቀረቡና ፤ ሲጠሩ ቶሎ‘አቤት! እመት!’ ለማለት አንዷ አዳራሹ፤ ሌላዋ እልፍኙ በር አጠገብ ለጠፍ ብለው ቆሙ ።

ቀኛዝማች ፤ ከዕለቱ ሁኔታ ሌላ የተለያዩ ሐሳቦች ሲያወጡና—ሲያወርዱ ፤ ሴትዮዋ ከራት በኋላ ወይም በማግሥቱ ጧት የሚሰሙትን ያገልግል መዘዝ እያሰላሰሉ ፤ ቄሱ በራሳቸው የሐሳብ ጎዳና ሲንጎዳጎዱ ፤ እጅግም ተከታታይ ወሬ ሳይወራ ራት ተበልቶና ‘በብሐት ለአብ’ ተብሎ መዓዱ ከፍ አለ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፤ ለቄሱ አዳራሽ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ተነጥፎላቸው ተኙ ።

ቀኛዝማችና ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ብቻ እልፍኝ ውስጥ እንደቀሩ ፤

“ይኸ አገልግል የማን ነው?” አሉ ቀኛዝማች ረጋ ባለ ሁኔታ አገልግሉን እንሥተው ። የሴትዮዋ ነፍስ ተሸብራ ልባቸው ተንዱዱች።

“የቱ?” አሉ ዐይናቸው ፈጦ እያየ ።

“ይኸን ነዋ! — ምነው ? አይታይሽም እንዴ?” አሉ በማንገቻው እያሽከረከሩ ።

“እእ!—የኛ ነው ። ምን ያረግልሁ እዚህ አመጣሁት” አሉ አፋቸው እንዳመጣ ።

“በደንብ አየሽው?—እንዳትሳሳቺ ብዬ ነው ።”

“ኡኡ! የገዛ ንብረቴን እንዴት አጣዋለሁ ?!”

“አምሳያ እንዳይሆን ብዬ ነዋ! እንኳን የዕቃ የሰው መልክ ያሳስታል ።”

“እስቲ ወዲህ በሉት !?” ብለው አገላብጠው አዩት ።



አገልግሉን ሲያገላብጡ እሳቸውን ደግሞ ድንጋጤና ሥጋት አገላበጣቸው ።

‘የኛ እማይደል በያቸው’ አለ አንዱ ደፋር ሐሳብ ፤

‘ቁርጥ የኛን አገልግል በይ’አለ ሌላው ቀላማጅ ሐሳብ ፤

‘ለሰውዬው እንደሁ እነ ሽዋርካብሽ አረጋግጠው ነግረዋቸዋል ፤ ይልቅዬ የኛ ነው ባልሽው ጥኚ’ አለ ሌላው አብሯቸው ያመሸ ሐሳብ ። ሴትዮዋ ከሐሳቦች ጋር ሲራኮቱ ፤

“ምነው ዝም አልሽ?—የኛ አይደለም እንዴ?”አሉ ቀኛዝማች።

“የኛማ—የኛ ነው ።”

“የኛ መሆኑን ብቻ ካረጋገጥሽ ይበቃል ። ለሌላው ግድ የለም” ብለው አገልግሉን እንደገና ለመቀበል እጃቸውን ዘረጉ ።

“ምን ያረግልሁ አስመጣሁት?” አሉ የነገርና የብልሃት አቅጣጫ ለመቀየር ።

“እኔማ ምን ያረግልኛል ፤ ከየት እንዳስመጣሁት ግን እነግርሻለሁ ። ‘እኔ ለሰው ሠርግ ሳንቀላፋ ያስረገዘኝ ጠፋ’ አለች አሉ ሴትዮዋ ። እኔ ከሰው እኩል እሆን ብዬ ጣጣ—መከራዬን እያለሁ ፤ እዚህ ደሞ ቤቴ ሥር—ሥሩን ይማሳል ። በሬ ካራጁ ይውላል አሉ ። በይ እዚሁ ደህና ቦታ ስቀይውና ጣጣውን ሲጨርስ እንደሆነ ይሆናል” ብለው ወደ መኝታቸው ሔዱ ። ሴትዮዋም አገልግሉን ወደ ድንኩ አልጋ ግርጌ ገፋ አድርገው ፤ አካላቸው እየተብረከረከ ወደ መኝታቸው አመሩ ።

ቀኛዝማች ጋደም እንዳሉ ነገሩን ለመጀመር ፤ ሴትዮዋ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ ሁሉ በአሉታ ለመመለስ አቆበቆቡ ። ከትራስጌአቸው በላይ የሚበራው ፋኖስ ፤ መስተዋቱ ቆሽሾ ደብዘዝ ያለ ብርሃን ይሰጣል ።

“ቅድም እኮ ነገሩን ብቅ አርጌ ችላ ያልኩት በቅድሚያ ላጣራ ብዬ ነው”

“የቱን ነገር?”

“አገልግሉን ነዋ! ተምነዬ ረሳሽው?” አሉ በገረሜታ ድምፀት ።

“ደሞ ምን ቁም ነገር አለው ብዬ እሱን ላስታውስ?!” አሉ ለማምታታት ።

"እእ! ኧረ እንዲህ ቀላል ነገርም አደል! —መዘዙ ሳያማዝዝም አይቀር!" አሉ ቆጣ ብለው ።

"የምን መዘዝ ልጄ? ባገልግል የሚመጣ መዘዝ!?" አሉና ደረቅ የስላቅ ሣቅ ሣቁ ።

"መዘዙንማ እያደር ታገኚዋለሽ! የዘንድሮ አገልግል እግር—አውጥቶ ዱር ለዱር እየሔደ ፥ እየጢሻው ውስጥ መገኘት ይዟል ። ያውም ሰው እየገደለ ———"

"አበስ ገበርኩ ጌታዬ! ምነው ባማን አሳድረን ብንልበት! ዛሬስ ደሞ ደጃም ቤቱም ነው እንዴ? ሰው በእንዲህ ያለው ቀን ተመስገን ብሎ ይተኛሊ — — —"

"የደጃም የቤቱም ያው ነው ፥ ሁሉስ ያንቺ ጉድ ሳይሆን ይቀራል ፥ አገልግልሽ ዱር ለዱር እየተገኘ ———" ብለው የፌዝ ሣቅ ሣቁ ።

"ኧረ ንሱ አባቴ ! እንግዲህ ደሞ ጀመረሁ ፥ ደሞ የምን አገልግል ነው ዱር — ለዱር እሚገኝብኝ ?"

"ምነው ነገሩን ሁሉ እያየሽውና እያወቅሽው ባታደኸሚኝ?" አሉ ቆጣ ብለው ።

"ጎርጊስ አባቴ! ደሞ ምንድን ነው ያየሁትና ያወኩት?"

"የምንዳዬን መቁሰልና የሰውዬውን መሞት ነዋ ?" አሉ በቀልድ መልክ ።

"እኔ ታዲያ ምንድነኝ — የምን ቤት ነኝ ?" አሉ ኮስተር ብለው ።

"አሁን ገና ጥሩ ጠየቅሽ ! ያን ያየሽውን አገልግል የኛ ነው ካልሽ ፥ ሌላ ሌላውን ደግሞ ቀስ በቀስ እንተማመናለን ።"

"የዛሬውስ የጉድ ነው ! ተነሥቼ ልሒድልሁ እንዴ ? በሌላ ቢያእትሁ ደሞ በዚህ መጣሁብኝ ።"

"እኔማ ምን እመጣብሻለሁ—— — የጊዮርጊስን መገበሪያ የበላ ያስለፈልፈዋል አሉ — —"

"ምንድነው ብላትሁ አንቱ ሰውዬ? እንግዲህ ደሞ ቀኗ ደረሰች መሰል ! ያላወኩ አይምሰልሁ ።"

"እሂሂ ! ምኑን ከምን አገናኘሽው በይ ! ? እኔ በላይነህ ካስፈለገኝ ዐሥር ዐሥራምስቷን ብነዳት ማባቱ ይከለክለኝ መሰለሽ ?



ይኸን ወግ ብለሽ አታውጊ ። ይልቅ ባገልግሉ ለማን ቋጥረሽበት ነበር ?" አሉ በስጨትጨት ባለ ሁኔታ ።

"ይኸው ነው የቀረሁ ?! 'ያብዬን እከክ ለምዬ' አሉ ። ብዬ ብዬ በስተርጅና ቅሌት ተራ ገባሁ ? አይ አንተ ጎርጊስ ! የለህማ ! የለህም! ወይ መቆየት ፥ ደሞ ብዬ ብዬ አገልግል አቀባይ ሆንኩና ዐረፍኩት ?! እኔ ደሞ ምን አረግሽው ሊሉኝ ነው ብያለሁ ? ለካስ ተደግሶልኝ ኖሯል ! ምንም ብትሉ ምን ፥ እኔ እንደሁ ሰበቡ ገብቶኛል ፥ 'ገር ልጅ እናቷ አትወዳትም' አሉ"

"ይኸ ሌላ ፥ ያ ሌላ ፥ አላሉ ሽማኔ ። አሁን ነገር ማዟዟሩን ተይና ፥ ፍሬ —ፍሬ ነገሩን እንነጋገር ። አንቺስ አልቋጠርኩበትም አልሽ — እሺ ይሁን በጄ ፥ ለሰውስ አላዋሽም ?" ብለው ቀና አሉ ።

"እኔ ለማንም አላዋስኩ" አሉ የሐሳባቸው ቋት ጠቦ ።

"እንዴት ያለ ነገር መጣ እባካችሁ ? አገልግል እንደ ሰው እግር አውጥቶ ይሔድ ጀመር እንዴ ?"

"እኔ ምን አቅልኋለሁ !?"

"ኋላ ምን ልበል ? ካላዋሽ ፥ ቋጥረሽ ካልሰጠሽ አገልግሉን ገንዳ ውሃ ምን ወሰደው ?"

"ማ ተወስዶ ነበር አለሁ?"

"ማ ይለኛል ? እኔው ራሴ አንጠልጥዬ ሳመጣው !"

"ማ? አንቱ ?"

"አዎ ! እኔው ራሴ ?"

"ምንዳዬ እቆሰለበት ሥርፋ ተገኘ ልትሉኝ ይሆን?"

"ጤናም አልያዛት እንዴ ይቺ ሴትዮ !? እንዴት ብዬ ልናገር — አዎ! እዚያው !"

"ምነው ብተዉኝ አንቱ ሰውዬ ! እልህ ቲይዝሁ ጊዜ በዚህ መጣሁብኝ ? ይኸስ ያንዳይ ነው ! ሰው ቢሰማስ ምን ይል ?" ብለው ትራስጌአቸው ሽጎጥ ያረጉትን ነጠላ አውጥተው ለበሱና ፊታቸውን ወደ ግድግዳው አዙረው ተቀመጡ ።

"እኔስ የገረመኝ ይኸው አደል ? እኔን ሆነሽ አንቺ እዚያ ብታገኚው ኖሮ ራስሽን ይዘሽ ነበር ኡኡ እምትዪው ።ይኸ እንዲህ በቅላ ቅላ እሚተው አይደለም" ብለው ጋደም አሉ ።

ቤትዬዋ በሥጋትና በፍርሃት እንደ ተጨነቁ ፥ ቀኛዝማች ፥ በኔ ላይ የተቃጣና ፥ እኔን ስላጡ በሎሌዬ ላይ የተፈጸመ ነው በሚል ግምት ነገሩ እየከነከናቸው ለመበቀል ሲያወጡና ሲያወርዱ አያሌ ደቂቃዎች አለፉ ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፥ በተንዛዛው ጥያቄና ንትርክ ፥ እንዲሁም ሰውዬው ቁርጠኛ መልስ ሳያገኙ ጋደም ባሉበት ወቅት ባጋጠማቸው ፋታ በመጠቀም የሁኔታውን አዝማሚያ አጢነው ስለ ተግንዘቡ ፥ ከዚህ አደገኛ ጣጣ ለማምለጥና ራሳቸውን እንደ ምንም ነጻ ለማውጣት ፥ ነገሩን ባንዱ ላይ ደፍድፈው ለመሸምጠጥ ቆርጠው ተነሡ ። ነገሩን እዚያው በዚያው ማጠላለፍና ከተቻለም ማድበስበስ ስለ ፈለጉ ፥ በሐሳብ መባዘኑን ትተው ፥ የማምለጫ ብልሃታቸውን ከቤታቸው በታች አጠመዱ ። አእምሯቸው ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀም ፥ ሦስት — አራትዬ አጨበጨቡና ፥ "ተዉት ፥ ተዉት ፥ ተዉት ፥ ተዉት! ኧረግ! ኧረግ! ኧረግ!" አሉ በቁጭት ድምፅ ።

"ምነው ? ምን ሆንሽ?" አሉ ቀኛዝማች ከሐሳባቸው ባነው ።

"አሁን ገና ነገሩ ገባኝ ። ለካ ነገሩ እንዲህ ወዲህ ኖሯልና !"

"እንዴት ወዴት በይ?! — ምን ነገር ትዝ አለሽ ? እስኪ ጉዱን ንገሪኝ?"

"አንቱ ለመሆኑ ምን የሰማሁት ነገር አለ?" አሉ ከሩቁ ለመጀመር ።

"ነገር ቢደጋገም ምን ያረጋል ? የተገኘበትን ቦታ ነግሬሻለሁ ፥ አረጋሽና ሸዋርካብሽም የኛ ነው ብለዋል ። ሸዋርካብሽማ ለአፈሣ ወስዳ መስጠቷንም አምና ተናግራለች ።"

"ዐፈር ስሆን?! በምቶዱት ታቦት በሚኻል ይዠኋለሁ ፥ ለማን ሰጠሁት አለች 'ይቺ አነካኪ የሴት—እር !"

"ለዚያ ለጥላ — ቢስ ዘመድሽ ነዋ! ጠላት ከሩቅ አይመጣ ! ከዚሁ ከጉያሽ ሥር ነው እሚወጣው ።"

"አሁንማ ገባኝ እኮ ! እዚሁ አጠገቤ ተቀምጦ የገዛ ቀብሬን ቲምስልኝ ኖሯላ!"

"እንዴት?"

"እኔ ነኝ ሞኟ! እቴዋ እያለ በማጅራቴ ቲያርደኝ ኖሯላ?! እኔ ደሞ አንገቱን እየሰበረ ሲቅለሰለስ ደህና ሰው መስሎኛል ! እባብ ፥ የሰው እባብ !"



"እንዴ! ሥር የሰደደ ነገር አለበት እንዴ ? ምን አረገሽ?"

"ደሞ ምን ያላረገኝ! ኧረግ !ኧረግ! ኧረግ! በቁሜ ቲቀብረኝ ምን ይባላል ? በሉ እንግዲህ 'እህ' ብለሁ ስሙኝ ።"

"አሁን እሱ ምን አረገ ልትዪ ይሆን? በሌለበት አትደፍድፊበት" አሉ ካንገቴ በላይ ።

"አንቱ ደሞ ክፉ ዐመል አለብሁ ፥ የልብሁን ታደርሱ ትናገሩና ፥ ሸተት ማለት ታበዛለሁ ።"

"አሁንስ እውነሽን ነው ፥ እኔማ ምን አሻኝ ፥ ሥግነቱ ላንቺ —"

"ከሱ ሥግነትስ የለየለት ባዳ ይሻላል ። ይልቅዬ ጉዱን ልንገርሁ ስሙኝ ፥ እንዲህ ላይ ፥ ላውን ቲታይ ቆዳው ሞኝ ይመስላል ። ዋዛ ፥ አረንዛ ሆድ! አይምሰልሁ ፥ እኔም ያቀረብኩትና አንቱም ስትወጡና ስትገቡ ዐሥሩን ታቦት እየጠራሁ ያስቸገርኩሁ ቦረቦር መስሎኝ ነበር ። ክፉ ጊንጥ ነው ። በዚያ ላይ ምቀኝነቱ አይጣል ! ከውሃ አቅም እንኳ ምነው የእነከሌ ቤት ውሃ ይጥማል ብሎ ይመቀኛል ። እኔማ መቼስ ምን ልበል እያልኩ ዝም ብዬ እሰማለሁ ። አንዱን ትቼ አንዱን ሆነዪ ፥ አንድ ቀን ምን አረግ እንደሁ እንጃ ፥ እሱው ቤት ሔጄ ስናወጋ ፥ 'ይቺ የምንዳዬ ጎጆ ትልሑን ቤት ግርማ ሞገስ አሳጣችው ፥ ያያት ሰው ሁሉ ፥ ይቺ ቤት ማማሯ እያለ ያወራል' ብሎ የማይሆን የማይሆን ነገር ቲያወራኝ ጊዜ ታዝቤ ዝም አልኩ ። አንድ ቀን ለታ ደሞ ቅራሪ ቢጤ ጠጥቷል መሰል ፥ 'እኝህ ቀኛማይ ያን የመሰለ ለም መሬት ፥ ነገ ጥሎ ለሚሔድ ለማንም ባዳ ከሚሰጡ ፥ ምናለ ለኔ ቢጤ ደሃ ዘመዳቸው ቢሰጡኝና ደህና እየተመራረእን ብንጠአኤምበት ። አረረም መረረም የኋላ—ኋላኮ ቀሪዎቹ እኛ ነን' አለኝ ።"

"እኔ እኮ አውራ—ጣቴን አልጠባም ፥ እሚሆነኝን ሰው መች አጣዋለሁ ። ካሥር አፈሣ አንድ ምንዳዬ ይበልጣል! የሱ ቢጤ ቢግተለተል ምን ያረጋል ። ደሞ ምን አርገኝ ብሎ እሱ ላይ ተንጠለጠለ? ዋ ይቺን ነገር የሰማበት እንደሁ ——"

"እኮ ቆይ ልጨርስልሁ ፥ መይ ጨረስኩልሁና? አብሶማ እቤቱ ከሔድኩለት ይሠራውን ያሳጣዋል ። የምንዳዬን ጉልማ እንደ ሸማው ጠእሎ ቢነጥቀው እንዴት ደስ ባለው! ኧረ—ምኑ ቅጡ የሱ ነገር?!" አሉ በሚያጋንን ድምፅ ።

"አይ ያንቺ ነገር! እኔ ይኸን—ይኸን መች አጣሁት! ይኸን ውሃ ወቀጣውን ተይውና ፥ ያገልግሉን ብቻ ንገሪኝ ። አሁን ጉዱ ሁሉ ያለው አገልግሉ ላይ ——"

"አንቱ ደሞ! ላመጣልሁ አደል ፣ ገና አሁን እኮ ነው ነገሩ ዝክር
ያለኝ —— ልቤ ስንት ቦታ ረገጠ ?!" አሉ ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ።

"ዳር—ዳሩን ስታንዣብቢ ምን ልበል — — ?"

"ያፈሳን ሚስት አገር ታሎት የለ እንዴ?"

"አሳምሬ ፣ ለምን አላኸውም ፣ መተር—ሆዴ አይደለም እንዴ?"

"ነው ። ዞን—አምባና መተር—ሆዴ አፍና አፍንጫ ናቸው ። እሷ
ታዲያ የዋዛ ሴት አትምሰልሁ ፣ የምንዳዬን ዘመዶችና ባላጋራዎቹን
ልቅም አርጋ ታቃቸዋለች ። እሱም የሆዱን እንጃዬ ፣ ያገሬ ልጅ እያለ ፣
መተር—ሆዴ ስቴጂ ፣ አገሬን አሽቆልቁለሽ እዪልኝ ይላታል" አሉ
ሥር—ሥሩን ትብተባቸው እየላላ ።

"ምነው እቴ! ይኸን አማይመስል ወሬሽን ብተይኝ !? እኔ እንደሁ
ነገርሽ ገብቶኛል —— ምን አለፋሽ ? ተይው!" አሉ እየነደዳቸው ።

"አይ ፍርጃ !አታስወሩ! — አንቱ የት ታቃለሁ! አንቱ እምታሎት
ላይ—ላውን — —"

"እንዲያው ባፈለገሽ ሁኔታ እዪው ፣ ባላጋሮቹ ጃራን ተሻግረው
ይኸን ነገር አያረጉም ።"

"በሉ ተዉት ወንድሜ! እኔም ቂል ሆኜ ነው ካንቱ ጋ መሟ
ገቴ ። እኔ ለምኔ ፣ ነገ ጧት እውነቱን ትሰሙት የለ ! አሁን የኛ አገር
ሰው ነው ሆዱ እሚገኘው? እኔም እረዳሃለሁ ፣ ቀስ ብለህ በድብእ ደመ
ኛህን ዲብ አርገው ካሉት ይተዋል? አይተውም ።"

"እስቲ በይ ቀጥይ ልስማሽ ?—መቼም የሰው ነገር አይታወእ ፣ ዛሬ
ቢያምልጠኝ ነገ አያመልጠኝ ፣ ይቺን ነገር እኔ አለሁላችሁ ብሎ
ውሏት ከሆነ ——"

"አሁን ቢናደዱት ምን ያረጋል? ነገርን እያጣሩ ነው — ይልቅዬ
ልንገርሁ ፤ ታዲያ ይኸ የኔ ጉድ — — —"

"ማ?" አሉ ሳይታወቃቸው ።

"አፈማ" ብለው ቀጠሉና ፣ "ለሱ ያለለትን ላያጣው የሰው አዱኛ
እያየ ሲያክ ያድራል ። ታዲያ ዛሬ ጀምበሯ ዘእዘቅ እንዳለች ይመጣና
'ሚስቴ ወደ ሐጃ—ፊጅ ሔዳ ቆየችብኝ ። እኔ ደሞ ወደ ኮለሴ እሚሔድ
ሰው አግኝቼ ፣ ቆላ አዝመራ ጥበቃ ለሚያድረው ልጅ ራት መላክ
ፈልጌ ነበር' ሲለኝ ጊዜ ሸዋርካብሽን ቋጥሬለት አልኳት ። የሰው መሔ
ጃው አይታወእ ፣ ከምንዳዬ ባላጋሮች ጋር ውስጥ—ውስጡን መክሮ



አለያም ሰው ገዝቶ ሊያስገድለው ተኋሁኖስ እንደሁ ማን አወኤ?
አገልግሉንስ ወስዶ ሰጥቶ እንደሁ ማ ተከትሎ አየው? የሰው ደም
አይለቅ! እሱማ በየትኛው አሞቱ ፣—አጀባ ሆዬ! ምን ሱሪ አለውና
ይቺ ነገር ከዚህ ብታልፍ ጠጉር ተምላሴ!"

"እ! እንዲህ ኖሯል ነገሩ!? 'ሚስቱን ገደለና አማቱ ቤት ተደበቀ'
አሉ!" አሉና በንዴት ቡግ ብለው ተነሡ ።

"ኧረ ንሱ ሰዎች! አሁን ታዲያ ምን ልኮኑ ነው? ምን ታረጉ
ከጀለሁ!"

"እማረገውንማ እኔ ዐቃለሁ! አስጠፈንገዋለኋ! አይዞህ ባይ እን
ዳለውስ ማን ያውቃል! አሁን ማ ይሙት እሱ ብቻውን ይቺን ሥራ
ሊሠራት! ወግ ነው! የምንዳዬ መቅደሙን አትዪ ፣ እኔንም ያስገደ
ለኝ ያክል ቁጠሪው ። ዛሬ እኮ አብሬ ያለመኖሬ ነዪ ሙቻለሁ"
ብለው ጋቢ ለብሰው ወረዱና ሱሪያቸውን ታጠቁ ። ሴትዮዋም ቀሚ
ሳቸውን አጥልቀው እፊታቸው ቆሙ ።

"ኧረ በምቶዱት ታቦት ይዤኋለሁ ወንድሜ! ኧረ አገር ጉድ
ይላል ! ኧረ የሰው መሳቂያ መሆን ነው? ምነው ይኸን ያክል? አይነጋ
ልሁም እንዴ? ወዴት በሮ እንዳይጠፋ ነው ? ነገ እንደ ስሎግ ሰተት
ብሎ ሲመጣልሁ ያደርስኋል ። አሁንማ ነገር ማበላሸት ነው ። ነገር
ሲያውጣጡና ሲያጣሩ ቀስ ብሎ ነው ። ከገነገነና ከሰማማ ምናቅላች
ኋለሁ ብሎ ይሸመጥጣል ። እሱ ራሱ ከመጣም እሰየው ! አለያም እዚቹ
ጠርቶ ቀስ ብሎ ማስለፍለፍ ነው ። እኔ በብላት ቢጠየቅ ይሻላል ፣
ነው እምልሁ" ብለው የሚመልሱትን ለመስማት ዝም አሉ ። ሁለ
ቱም ከየራሳቸው ሐሳብ ጋር እየመከሩ አጠር ላለ ጊዜ ፊት ለፊት
ተቀመጡ ። ሰውዬው የጉዳዩን ሁኔታ ረጋ ብለው ለማሰላሰል ተመል
ሰው ጋደም ሲሉ ፣ ሴትዮዋም ከተል አሉ ።

"የሚገርም እኮ ነው" አሉ ውስጥ—ውስጡን በጀርባቸው
ተኝተው ጣራ—ጣራውን እያዩ ። "እስቲ የሰው አገር ሰው አደል ፣
ባይልለትና መዘዘኛ ሰው ቢገጥመው ነውዪ ፣ ላንድ ራሱና ለቤተሰቡ
ያባቱ ርስት ይበቃው ነበር ። አሁን ይኸ ነገር እውነት ሆኖ እሱ
ገብቶበት ከተገኘና ምንዳዬ ካወቀ መተላለቃቸው ነው ። እኔ ሒድ ብዬ
ባላዘው ኖሮ ይኸ ሁሉ መከራ አይደርስበትም ነበር ። እሱ ባልሰማና
እኔ ብቻ አሳሩን ባስጨለኩት ——" አሉ በልባቸው ። ይህንኑ እያ
ሰላሰሉ እንቀላፉ ።

ሴትዮዋም ነገሩ ተድበስብሶ የሚቀርበትን ብልሃት እህህ እን
ዳሉና የሚያመልጡበትን የሸር ምጥ እንዳማጡ ወፍ ተንጫጫ ።

በማለዳ የሚሠራ ሥራ ያለባቸው በማስመሰል ቀስ ብለው ተነሥተው አፈሣን ፍለጋ ወደ ቤቱ ገሠገሡ ። የአጥሩ በር በወልጋዳ ተዋጋ ተዘግ ታለች ። ሊከፍቱ ቢሞክሩ ተዋጋዋ ተቸክላ አስቸገረቻቸው ። ወደ ውስጥና ወደ ውጭ እየገፉና እየሳቡ አንገላቷት ። ሥጋት ባፈለቀው ጉልበት መከራዋን ያየችው በር የተዋጋዋ ጫፍ ነድሏት ወደ ውጭ ብቅ ስላለ ፣ ጫፏን በሁለት እጃቸው ቁልቁል ተጭነውና ስበው ከመሬት አላቀቁና በሪቱን በዝግታ ከፍተው ገቡ ።

ቁና ቁና እየተነፈሱ ዋናውን በር በጥፊ መታ—መታ አደረጉት ።

"ማነህ" አለች አስካደች ።

"እኔ ነኝ" አሉዋት አፋቸውን በሩ ላይ ለግተው በቀስታ ።

"እኔ ማ? "አለች ድምፅ ለመለየት ጆሮዋን አቁማ ።

"እኔ ነኝ አልኩሽ አንቺ ደሞ! አሁን አጣሽኝና ነው ?"

በወጉ ባይነጋም ፈጓል ። በሩን ከፍታ "ውይ! እቴዋ ኑረኋል እንዴ? ምነው ሳይነጋ መምጣትሁ? ደህናም አደለሁ እንዴ?"

"ደህና ነኝ ፣ በደህና አደራችሁ ወይ? እስቲ አፈሣን ቶሎ ቀስ ቅሽልኝ ። ቶሎ በይ ጉሽ ! ድምጤን ቲሰማ ምነው አለመነሳቱ ? — በምን ታደለው ? አሳብ የለው ።"

"አይ እቴዋ! እዚህ ያለ መስሎሁ ነው እንዴ? እሱ እዚህ የት አለልሁ?"

"ወዴት ኬደ? እቤትም አላደረ እንዴ?"

"እሱ እቴ! ሰው ሁሉ እደይ ሬሣ እየጠበቀ እኔ እቤቴ ተኝቼ ባድር ሰው ምን ይለኛል ብሎ ፣ ብለው ብሠራው እምቢ ብሎኝ እያው እናንተ ደይ ነው ።"

"ያንቺ ባል አዙሮ እሚያየው መቼ ይሆን ? አበስ ገበርኩ ! ማ ኅሽ ይለኛል ብሎ ነው ለማንም ሽፍታ እብርድ ላይ ቲጠበስ ማደሩ ? እኔስ ምን ይሻለኛል ! ታንድ ቀን አንድ ቀንም ልብ አይገዛ!? ደህና መወዳጃውን ይዟላ ?! እሳቸው እኔን ሊገል የመጣ ሽፍታ ፣ እኔን ቢያጣ ሎሌዬን አቀሰለ እያሉ ይበሳጫሉ ። እሱ ደሞ ሬሣ ይጠብ ቃል ።አበጀህ ማለቱ ነው ? ይሰሙበትና ያቺን በስንት ልመና ያሰጠ ሁትን መሬት ይመነጭኡታል ። በይ ነይ ለበስ አርጊና ፣ ሮጥ ብለሽ ጥሪልኝ ። ቶሎ ና ብላሃለች በይው ! እዚቹ ተቀምጬ እጠብእሻለሁ ። በይ ቶሎ በይ — ጉሽ!" አሏትና በሩን ደገፍ አሉ ። ነጠላዋን ለብሳ



ወደ ውጪ ስትወጣ ፣ "ያንተ ያለህ! ኧረ ፈጠን — ፈጠን በይ! በዚህ አካሔድሽማ — —" ሲሉ ፈጠን አለች ።

ከበሩ ገለል ብለው ተቀመጡ ። በድንገተኛ ሁኔታ ዓላማው ሁሉ ፈሩን ስቶ ሕሊናው ግራ—እንደ ተጋባ ሰው ውስጣቸው ባዶ ሆነ ። ሁሉም ነገር ከንቱ መሰላቸው ። አፈሣ በጣም የዘገዩ ስለ መሰላቸው መንፈሳቸው ተሸበረ ።

"ይኸነዬ ያቺ ክርፋፋ ሚስቱ ስትንቀረፈፍ ነውዪ ፣ ቢሰማስ ቶሎ ይመጣ ነበር ። 'አንቺ ብለሽኝ ነውዪ ፣ እኔ ይኸን ያክል ምን በድሎኛል ?'. ብሎ የሚያውቃትን ሁላ ቢዘከዝካትስ እንዴት አባቴ እሆነዋለሁ ?" እያሉ ሲሠጉ አስካደች ብቻዋን ብቅ በማለቷ ክው አሉ ።

"እህ? የለም እንዴ? ምናለሽ?" አሏት ገና ከመድረሷ ።

"የለም! ከነጋ ወዴት እንደሔደ እንጃዪ ፣ እዚያው ነበር አሉ ።"

"ወዴት ሔደ አሉሽ ? አልጠየቅሻቸውም እንዴ?"

"ጠይቄአቸውማ ፣ 'እየሁ ነበር አሁን' ብለው ተሳሳኡብኝ"

"ምን ያለሽው ነሽ እቴ !—— ይኸነዬ በሌላ ይሆናል የተሳሳ ኡት ።"

"አፈሣ የት ኬደ ብዬ ብጠይቅ ፣ 'ሬሣ አስደንብሮት ሔደልሽ' ብሎ አንዱ ቀለደብኝ ።"

"አንዳች ያስደንብረው እቴ! ዝም አልሽው ታዲያ?! እስተዶቃ ማሰሪያው አትነግሪውም ኖሯል?" ብለው ወደ ቤታቸው ገሠገሡ ።

* * *

ቀኛዝማች አልተነሡም ። ያልታሰበ አንዳች በሽታ አጋድሞላቸው ቢውል ደስታውን አይችሉትም ። ከገዛ ቤታቸውም ይሸሹ ይመስል፣ ውሻ እንዳየች ቀበሮ ፈትለክ አሉ ። ሌላ ምርጫ ስላልነበራቸው ሰተት ብለው ወደ ሬሣ ጠባቂዎቹ በመሔድ ፣ "እንዴት አደራችሁ እዚህ እውርጭ ላይ ተጨብጣችሁ አደራችሁ አደል?" አሉ ድንገት ።

"እሱ ቲያመጣው ምን ይደረግ" አለ አንዱ ፈጠን ብሎ ።

"ሌላው ቢቀር ለሰማይ ቤት ይሆነናል! ሌላማ የትኛው ዘመዱ" አለ ሌላው ።

"እኔ እኮ ጥኢት መስላችሁኝ ነበር ፣ ለካ ብዙ ናችሁና — ያ አፈሣ እዚህ ነው አዳሬ ብሎኝ ነበር ፣ ወዴት ኬዶ ይሆን ? አላያችሁትም?" አሉ እየሣቁ ።

"እየሁ እኛው ጋ ነበር አሁን —— በዚህ ወደታይ ወረድ አለ መሰል" አለ አንዱ እየጠቆመ ።

"ምን ያለው ነው ወንድሜ ?! — እስቲ አደራህን ብየው ጥፍት ይበልብኝ" አሉ የተጋደመውን ቃሬዛ ማየት እየፈሩ ።

"ምናሻሁ ታዲያ ፣ እኔ በያው ነው ምንገዴ ፣ ታገኘሁት እነግርልኋለሁ" ብሎ አንድ ጐረምሳ ቁምጣ ሱሪውን እያራገፈ ቁልቁል ተንደረደረ ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ረጋ ብለው በዚያው አቅጣጫ ሲጓዙ ፣ ስንኳንስ አእምሮው ተሸብሮ ሐሳብ የገባው ሰው ሊመስሉ ቀርቶ ነገር የሚያሰላስሉ አይመስሉም ነበር ። ጥቂት ወረድ ብለው መንገድ እንደ ጠፋው ሰው ገላጣ ቦታ ላይ ፈዘው እንደ ቆሙ ፣ አንድ ሰላላ ድምፅ ከበስተጀርባቸው ፣ "እቴዋ!" ሲላቸው የናቱን ድምፅ እንደሰማ ሕፃን ተደሰቱ ።

"የት ኖረሃል ልጄ?" አሉት በጭምትርትር ፈገግታ ።

"እያው እደጅሽ ነው ያደርኩት ——"

"እሱንማ ሰምቼልሃለሁ! አሁን አልኩሂ ?"

"እንዲህ ወደታይ ወረድ ብዬ ነበር ። ብስጭቱ አላስቆም ፣ አላስ ቀምጥ አለኝ እቴዋ! ንዴቱ አንጀቴን ላስ አደረገው ——"

"ዋ—'ቴ! አሁን እንደንቧይ ቢፈርጡት ምን ያረጋል? ከኔና ካንተስ የሞተ ሰው ይሻላል!"

"ምነው እቴዋ? ምነው? እኛ ምናችን ተነካ ? እሚሆን መስሎን ——" ሲል ፣

"እሱን አታንሣ ። መበርታት አሁን ነው ። እንዲሁ ትንዘረኽረህ ጉዳችን መንተክተኩ ነው ። አንተ መቼም አሳበ—ቢስ ነህ —— ሰው እንዴት ቆሞ እጁን ይሰጣል?"

"ምነው ?ምን መጣ? ደህናም አደለሽ እንዴ?"

"ኧረ እንዲያው ሞተህ ባረፍከው አንተስ! ደሞ ደህናም አደለሽ ወይ ትለኛለህ?! አንተን ይገፎ ነው ደህና እምሆነው ? የዚያን ያገልግል ነገር ማታ በጭለማ መጥቼ አልነገርኩህም እንዴ?! እንዲቹ ቁጭ ብዬ ነጋልኝ —— "



"በምን ምክኛት? —— አትክጃቸውም እንዴ?"

"ኧረ—ወዲያልኝ አንተስ! ምን ብዬ ነው እምከዳቸው? እታእቸውምና ነው? አሁንማ ብለው—ብለው ፣ ያገልግሉ ጉዳይ ከሱ ራስ አይወርድም እያሉ —— "

"ከማ?"

"ካንተ ነዋ !" አሉት አፉቸውን ሞልተው ።

"ነው' ንዴ !? ኧረ—ንሱ! — እንተያያታለና! ዐርፈው ቢከበሩ ይሻላቸዋል ።"

"ኧረ ተው እንዳፍ አይቀናም! ይኸ አፍህ ዘረጥ—ዘረጥ አይበል! እማትወጣውን ዛፍ አትጠንቁል ። እኔ የሰሙትንም እንጃ ፣ ነገሩን ደር ሼበታለሁ ቲሉ ነው ያመሹት ——"

"እኔ ቢያነጉበ ምን አሻኝ! —— እኔ የሳቸውን አገልግል አቅላቸዋለሁ እንዴ?"

"ማ ነገሩን አሳክቶ እንደ ነገራቸው ምን ዐውቄ ፣—— ዐሥረዬ እየተነሡ ይኸ ዘመድሽ ፣ እንዳሉ ነጋላቸውዬ ——"

"እንዴት አሳሬን አሳዬኝ ይኸ ዝምድና ወንድሜ !— አሁንማ ማ ችሏቸው ፣ ተሾሙ መሰል ፈረደብን ፣ እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ! ለመሆኑ ማ ነገረኝ ይላሉ?"

"ያቺ ቀላማጅ ምን ያልቀላመደችው አለ ? ሌላም ሰው ጢይኽዋል መሰል ማባቱ ሔዶ ሲሸረከት እንዳመሸ እንጃ ፣ እነዚያ ባላጋሮቹ ምንዳዬን ተዚህ ቢያበሩልኝ ፣ አለያም ቢገሉት ፣ ቀኛማይ ለሱ የሰጡትን ማሳ እቴዋ ለኔ ታስጠኝ ነበር ፣ እሱ ነው እንቅፋት የሆነብኝ እያለ ሲያወራ ሰምተነዋል ብለው ነግረዋቸዋል መሰል ።"

"እስቲ ሙት በይኝ! ደሞ ማ ይሆን እንዲህ አርጎ ስሜን ያጠፋው?"

"የት አባቴ ዐውቄ ! እኔስ አንጀቴ እርር ያለው በምን መሰለህ ?"

"ደሞ ወደኔ ዞሩ ?! እኔ መቼ ጉዴን አወኩ ?! አንቺ ታዲያ ምን አልሽ እቴዋ ?"

"ቀድሞ ነገር ማ አናግሮኝ? እሳቸው ለራሳቸው ነገር —ነገር ብሏቸዋል ። 'አንቺ ምን ታቂያለሽ' ብለው አፌን አስያዙኝ ።"

"እስቲ ምን እንደሚያረጉኝ አያለሁ ፣ አሁን ስተት ብዬ እሔድ የለ !"

"ጎርጊስ አባቴ! ምን ታረግ?"

"እነግራቸዋለኋ! ያለ ስሜ ስም — — —"

"ምን ብለህ?"

"ኧረ ቆይ ዝም በይ፣ እኔ ዐቃለሁ!"

"ጤናም አልያዘህ እንዴ! ወዮ ጉድ !"

"ያንቱን አገልግል አይቻልኋለሁ ወይ ብየ ነዋ!"

"አይ አዙሮ አለማየት! ሸዋርካብሽን ጠርተው ያፋጥጡሃላ !"

"ቁብ ያለኝ መስሎሻል፣ የት — ምድር ነው የሰጠሽኝ ብዬ፣ አፏን አሲዛታለኋ!"

"እይ ያንተ ነገር! አልሸሹም ዘወር አሉ ። እኔስ ብሆን አሳሬን አይቼ የለ ? ሰጪው ብያት ሰጥታዋለች ብያቸዋለሁ" አሉ ሲፈሩ —ሲቸሩ ።

"አንቺስ ብትሆኚ ትሰጭኝ አትሰጭኝ የት አየሽ ?"

"እኔ እቴ ! አላየሁም እውነክን ነው ። ሰጥችኝ ብትለኝ ነወዴ !"

"ታዲያ ምንድነው እምትዪው ?"

"እኔማ እምለው፣ ያም — አለ ያም አለ፣ አገልግሉ እንደሁ ገንዳ — ውሃ መገኘቱ አልቀረ፣ አንተ ካድክና ሸዋርካብሽን አይለ ቋት፣ እሷ ደሞ ከኔ ጀርባ አትወርድ ።"

"ያልቸገረሽን እኮ ነው እቴዋ! እኔ ማንስ ወስደው ማ ምን ቸገረኝ! ሥራ አጥተሻል ።"

"ተው አጉል ታስገኝኛለህ አንተ ሰው! እዬ! 'ፈሷን ፈስታ ቂጧን ጨበጠች' አሉ እቴዋ ዘርፌ፣ ይኸማ አጉል ነው ። እንዲያ ውም ነጋ —ጠባ ጠምደሽዋል ይሉኛል፣ ይቺን ታህልማ ታገኙ ልታ ስገድይው ነበር ብለው ይከመሩብኛል ።"

"ድብን ይበላ! ለምን ዐሥረዬ እየተነሣ አይከነችርላቸውም!"

"አይይይይ! ምነው ይኸን የሎፍ —ሎፍ ወግህን ብተወኝ! —ቀን እያዩ ነው መቀናጣት ። በረድ እስቲልላቸው ከየህ ግድም ገለል ብትል ይሻላል ። አሳስሬው እሔድና አዲሳባ ምንትስ እሚሉት ቦታ አስቀርበዋለሁ ብለው ጨርሰዋል ። ምን አረገኝ ብለሁ ታሳስሩ ታለሁ ብላቸው፣ አገልግሉን ተቀብሎ ለማባቱ እንደ ሰጠው ቲጠየቅ ትርክርኩ ይወጣል እያሉ ሲዝቱ ነው ያደሩት ።"



ክፉኛ ደንግጦ ልቡ ተሽረከረከ ።

"እያረጉም አይባልም እኮ — —ለዚያውስ እሳቸው ምን አጠፉ" አለ በተማታ አስተሳሰብ ።

"እሱንማ ምነው ነግሬህ ! ያለ ሸዋርካብሽ ማጃ የዶለኝ የለ፣ ምን ያረጋል" አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

"አሁን ምን አለፋሽ፣ የመጣው ይመጣሊ እኔ እንደሁ ወይ ንእንቅ፣ እንኳን አገልግል የገዛ በእሷቸው ተሰንክላ ብትገኝ ምን ቸገረኝ ? — —አትልፊ እቴዋ ! የመጣው ይምጣ — —"

"ኧረ በናት ባባትህ ውቃቢ ይዝሃለሁ፣ የኔ ኢሳር ገና ነው መስ ለኝ — —ምነው ሙቼ ባረፍኩት፣ አንተም ተዋርደህ፣ እኔም ያገር መሣቂያና መሣለቂያ ከምሆን — — —" ብለው ንግግራቸውን ሳይጨ ርሱ እንባቸው ግጥም አለ ። ሐሳቡ ተማታበት ።

"እኮ እንዴት ላርግ እቴዋ?" አለ በግርታ ።

"እንኳንና ከክፉ ነገር ከደህና ነገርስ ቢሆን ሁኔታው እስቲ ለይ ገለል ማለት ጥሩ ነው ! እኔስ እንዲህ ክንፌን ጥዬ ስርጥ መምጣቴ ለማን ብዬ መሰለህ፣ ቢጨንቀኝ አይደል?"

"አይጣል እኮ ነው እናንተ ሆዬ!" አለ ሐሳቡ እየዋለለ ። ዝም አሉት ።

"እንዲህ ቤት ንብረቴ ተዝረህርሆ፣ በዛሬ ጊዜ ማ ታምኖ አደራ ይባላል — —"

"ኧረ እንዴት አባቴ ልሁነው፣ አንዳንደዜ በሆነ — ባልሆነው ትሠጋለህ ልበል ? እንዲች ብለህ አታስብ፣ እኔ የት ኬጇ?"

"አንቺ አዲሳባ ልኬጅም አዶል እንዴ እቴዋ፣ የት ሆነሽ?"

"አይይይ! ኧረ እንዲያው ምን ያሉህ ነህ — —እሳቸው ጧት እግራቸው ወጣ እንዳለ አንተ ማታ እቤትህ ገብተህ፣ ታድራለህ፣ እስተዚያው ደሞ እኔ አለሁ"አሉ በኩራት ።

"አሁን እኮ ያም አለ ያም አለ ! እኔ ከምንዳዬ ጋ ደም መቃ ባቴ ነው ።"

"በየት በኩል ልጄ?" አሉ ነገሩ ገብቷቸው ሳለ ።

"አሁን አጣሽውና ነው፣ አንተ ለገደልከው ሰውዬ ባገልግል እንጀራ ቲያቀበል የነበረው አፈሣ ነው ብለው ይሉታል፣ ይቺን እን ደሚሉት ዐቃለሁ፣ ያውም. . ."

"ማ ይነግረዋል ?"

"ቀኛማይ ቢሆኑስ ፣ ተዚህ የበለጠ ስንትና ስንት ነገር ያወጋሉ — — እነቸርነትስ ምን ሥራ ይዘዋል ።"

"ግድ የለህም እኔ ነገር ማብረጃ መላ አላጣም ። ይኸም ነገር እሱ ጆሮ አይደርስ ፣ ቸርነትንም ቢሆን ከሰው አትቁጠረው ። የቁም ስቅሉን ታሳየው እንኳን ወሬ ሊያወራ የገዛ ምላሱን ይውጣታል" ብለው ነገር አቀዘቀዙ ።

"ስንበትበት ብሎ መስማቱ አይቀር ፣ ከነገሩት እንኗኗርም ብዬ ነው ። አቢጀህ — አበጀህ በዝቶበታል ። ሸዋርካብሽስ ብትሆን ይኸን ለማውራት — — —"

"ስለሷ ግድ የለህም ። እኔ አቅበታለሁ ። ተንግዲህ ስለሷ አታስብ — — ይልቅዬ ረፈደ ።"

እሱ ልቡ እንደ ዋለለ ፣ እሳቸው "በሒድ ጥፋ' እንደጸኑ ወደ አፈሣ ቤት ገሠገሡ ። ወደ ጓሮ ዞረው አፈሣ ስለሚሔድበት አካባቢ ተነጋግረው ተግባቡ ። እስካደችንም ጠርተው አፈሣ ከቀኛዝማች ጋር በነገረ—ሠሪ ከፉኛ መጣላቱን ጨማምረው ነገሯት ። እሳቸው አዲስ አበባ እስኪ ሒዱ ድረስ ለጊዜው ከፊታቸው ዘወር እንዲል መመካከ ራቸውንም ገለጹላት ። ክው አለች ።

ሴትዮዋ ለሱ ያላቸውን አሳቢነትና መውደድ ፣ እንዲሁም በባ ለቤቷ ላይ ተንኮል ያስባሉ ብላ ባለመጠርጠር ነገሩን ሰምታ አዘነች ። ቀኛዝማችን ግን በጣም ጠላቻቸው ። "አሁን በያ ሰሞን'እንዴት ታረ ጉኝ ፣ ያለናንተ ማን አለኝ' እያሉ እንከኮ ሊሉን ሲቃጣቸው ክረ ሙና ፣ ያቺ ሁሉ ተምነዬው ተረስታ ነገር ነገር አላቸው ? አይይይ! እስኪ አንተ የላይኛው ፍረድ!" ብላ አሳቀለች ። ተጣሉ የተባሉበትን ምክንያት በግልጽ ባለማወቋ ግን ከነከናት ። ሆኖም በወቅቱ በነበረው ጥድፊያ የተነሣ ጉዳዩን በዝርዝር መጠየቅ አልቻለችም ። እነሱም ቢሆን ፊት አልሰጧት ።

አፈሣ ጥቂት ጥይቶች ያለበትን ዝናሩን ታጥቆና ረዝም ምንሽ ሩን ይዞ እንደ ዘበት ከቤቱ ሲወጣ ባለቤቱ እንባዋን እያባበሰች ፣ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ውስጥ—ውስጡን እየተፍነከነኩ ከግቢው ሲወጡ ፣ "የሌላ እንዳይመስልብን አንቺ እየሁ ቅሪ ፣ እኔም ቢሆን እግረ—መን ገዴን ነው ብዬ ነው — — — ደሞ የምን ማለቃቀስ ነው ፣ የምን እዩ ልኝ ስሙልኝ ነው ፣ በይ ዝም በዪና ግቢ"አሉዋት ።

ሰው በማይበዛበት መንገድ ጥቂት አብረው እንደሔዱ ፣



"ለማባቱ ብዬ ነው ቤቴን ጥዬ መሔዴ? ሁሉም ቀዳውን ሊያ ደነድንና እንደልቡ ሊዘባነን እኔ በምንተዳዩ ደም ተቃብቼ ችግር ይበግብገኛ" ብሎ በልቡ ተነጫነጨ ።

"እቴዋ!" አላቸው ፣ እፊት—እፊታቸው በዝግታ እየተራመደ ።

"አቤት!" አሉት ፣ ምን ሊጠይቀኝ ይሆን በሚል ሥጋት ።

"ኧረ እንዲያው ለማባቱ ብለን ነው እንዲህ መሆናችን?"

"ለኔና ላንተ ብለን ነዋ! ለሌላማ ለማን ብለን — — ወራቱ ነው ያጋደለብን — — —"

"ምን እንዳንሆን? ምን እንዳያረጉን ፣ እንዲያው እኮ ነው ፍራቻሽ?" አለ ቆም ብሎ ።

"የሚያረጉትንማ ምነው ነግሬህ — — አልፈው ተርፈው አሳስረ ዋለሁ ብለው ቲዝቱ ።"

"እንዲያው ባገሩ መንግሥትም የለ ማለት ነው? ባልሠራሁት ሥራ የትኛው ዳኛ ታስር ይለኛል ?"

"እዬ ሞኛ! አሁን እኮ እሳቸውም የስንትና ስንት ዳኛ ያክል ሆነዋል ። አካሔዳቸውስ የት መስለህ ፣ እዚያው አዲሳባ እንጉሡ ዘንዳ እኮ ነው ። እ! ላሰኛቸው ዳኛ ቢነግሩ ማ ከልካይ አለባቸው ? ናዳን ቆሞ ከመጠበእ ዘወር ማለት አይሻልም ትላለህ?" አሉ ወዲሁን ገደል የፊት ለፊቱን አውላላ ሜዳ እያስመሰሉ ።

"ይልቅዬስ ቤቴን ጥዬ ስሔድ ነው የሠራው ሥራ ቢኖር ነው እያሉ ስሜን ለማጥፋትና ደም ለማቃባት የሚመቻቸው ፣ ተዚህ ሁሉ ምን ሳረግ አይተሁኛል ብዬ ልጋተራቸውና የመጣው ይምጣ ። ጨክኜ ተደፈርኩ ምንም አልሆን ፣ ፈርተሽ አስፈራሽኝ — — እኔማ እየቆየሁ—እየቆየሁ ታሰላስለው — — —"

"ያንተ ያለህ! ምነው ልጄ ገና ታሁኑ አሞትህ ፈሰሰ? ይኸን ጨበጥ — ለቀቅህን ተወኝ! የምን አድሮ—ቃሪያ መሆን ነው እቴ? እንዲህ ጥንክር ሰው ተሆንክማ ያነዬ እትበረታውም ኖሯል? አሁን ቢያኩ ቢቧጥጡት ምን ያረጋል ? አቅምን እያዩ ነው መጀነን — — — የትናንት አዳሬን ብታይ እንዲህ አትልም ነበር! ነፍሰ ሥጋዬ ሲበጠ ቅና ሰማዩ ተደፍቶብኝ — — — ተው ማንጠልጠያ የሌለው ቅል አታርገኝ ። ልብህ አንድ ይሁን ። ሁለታችንም ሆድ ለሆድ ተዋው ቀናል ፣ ያቺን ጋለሞታቸውን አዲሳባ ሰደው እኔ እንድቀርና ምንዳዬን ይዘው ለመንዘላዘል ነው ፣ የሌላ መሰለህ!? እንዳሰብኩት ባይሳካም

አይቆጨኝም — — አንጀቴ ርሷል ፥ እንዲህ ቆስሎ መጋደሙስ ምን ይውጣው — — በል እኮ ልቤ ቆመ ።”

“ — — እንዲያው ላንቺ ስል ለጥኢት ቀን ገለል ልበልልሺ ደስስ አላለኝም — — መቼም ላንቺ ስል እንደዩ ቀን ጎሎብኛል — — የቤቱንም ነገር ታኢዋለሽ — — —”

“አሁን እኔ ነኝ ስላንተ ቤት እደራ እምባለዋ? ካንተ ሳልሻል ቀረሁና ነው — — — በል በርታ —በርታ በል ፥ ቀኑ ነው ሸርተት ያለ ብን — — የዛሬን እጋሼ አጥላባቸው ቤት እደርና ፥ ነገ ረፈድፈድ ቲልልህ ተሻግረህ እደር” ብለው ሳያስበው አገላብጠው ሳሙት ።

እፈሣ ሲያሽው—ሲጎሽው በሆዱ ነገር እየጉነጉነ እና ቅር እንዳ ለው ተለያዩ ። ሴትዮዋ መለስ ብለው እንኳ ሳያዩት ወደ ቤታቸው ገሠገሡ ። እሱ ግን ወደ ካብ ሥላሴ በሚወስደው መንገድ ጥቂት እን ደተጓዘ ፥ ፊቱን ወዳገሩ አዙሮ አንድ ዲብ ላይ ዐረፍ አለ ።



# ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

“ይኸ ሰው እስላም ይሆን አማራ?” አሉ ተረተኛው ሽማግሌ ።

“ማ ጠየቀው ብለሁ ነው!?” ብሎ አንዱ ሣቀ ።

“ይኸን ቀልዳችሁን ተዉ ፥ በሞተ ሰው አይቀለድም — —ጡር ነው” አሉ በቁጣ ።

“ለምን አንገቱን አናየውም ፥ ማተብ እንዳለውና እንደሌለው ያስ ታውአል ።”

“እውነትን ነው” አለ አንዱ ተቀብሎ ።

“ማተቡ ተበጥሳ እንደሆነስ?” አለ ሌላው በቀልድ ።

“እንግዲህ መምሬ ደሳለኝና ሸሕ ሢራጅ መጥተው ዕጣ ይጣጣ ሉና አንድ ይበሉታ! ታልሆነ በሽሆቹ ውጂብና በሚኻል በተስኪ ያን መኻከል እንቀብረዋለን ፤ ያው ዞሮ ዞሮ አፈር ነው ፥ ምን ልዩነት አለው ?”

“ተዉ ጉበዝ — ተዉ ቀን በጣለው ሰው እንዲህ አይባልም ፥ ካገሩ አይወጣና ችግር አያገኘው የለም ። እኛ ባላወእነው እንፈርዳ ለን ፥ ጌታ ባወእው ይቀጣል ፥ ሰውና እንጨት ተሰባሪ ነው ፥ አሁን ከመኻላችን ማንኛችን እንደሚእድም ያለሡ ማን ያአል ። እስኪ ማና ችን ነን እንዴት እንደምንሞት የምናእው ፥ ግፍ አትናገሩ” ብለው ሽማግሌው ፊታቸውን ከሰከሱ ።

“በሉ ገልጠን እንየው” አለ አንዱ በመኻል ።

“ግለጠዋ!” አሉ ሁለት — ሦስቱ ።

ሬሣውን ገልጦ ሲያይ ሁሉም አሰፈሰፉ ። አንገቱ አብጦ ፊቱ ተድበል ብሏል ። ደረት ፥ አንገትና ፊቱ ላይ ረግቶ የደረቀው ደም የአዋዜ ልቅልቅ ይመስላል ። የሁሉም ዓይን ሬሣው አንገት ላይ ተተከለ ።

“እስኪ ስንጥር ቢጤ ፈልጉና ስጡኝ” አለ ሰውዬው እፍና — እፍንጫውን በግራ እጁ አፍኖ ።

“ለምንህ?” አለ ከሚመለከቱት አንዱ ።

“ማተብ እንዳለው ጫር — ጫር አርጌ ልይበት” ከማለቱ አንዱ አቀበለው ። የረጋውን ደም በስንጥሩ እየጫረ ማተቡን ፈለገ ።

“በደንብ ነሃ — ነሃ አርገው ፣ ምነው ፈራኸው?” አለ አንዱ ደፋር መሳይ ።

“ይቻት ክሩ! በደም ተለውሳ ነውዴ — ይቻት!” ብሎ ሁለት ሦስተዬ በስንጥሩ ወደ ላይ አነሣና ፣ “አማራ ነው! በሉ እንግዲህ ለቀ ኛማይ እንንገራቸው” አለ ቀና ብሎ ።

“ምን እንዲያደርጉልን ፣ እንዲያማምሱን ነው?” አለ ሌላው እየሣቀ ።

“ልንቀብረው ነው ብለን ነውዴ !” አለ ሁሉንም እያየ ።

“መሬት ለክተው እንዲያሰጡን ነው ወይስ ለቄሶቹ እንዲነግሩ ልን — ይልቅ አታሥቁብን ።”

“ለማንቻውስ ቢሆን ፣ አገሩ ሳይታወእና ሰው አይቶ ሳይለየው ፣ ማ ቅበሩ አላችሁ ቢሉንስ? በሰው ነገር ማ ጣጣ ይገባል? ቄሶቹም እሚሰሙት እሳቸውን ነው” አሉ ሽማግሌው ።

“እውነታቸውን ነው ፣ ማ ቅበሩ አላችሁና ቀበራችሁ ብንባልስ” አለ አንዱ ።

“እንደ ዐውሬ ጠባቂ ብርድ ሲፈደፍደን አደርን — —አሁን ደሞ ምን ባረግን እንንገላታ?”

ሌላው ካፉ ልፎ “ሬሣውኮ የነሱ ነው ፣ እኛ ዐይናችን እያየና ጆሯችን እየሰማ እንዴት ዐውሬ ይበላዋል ብለን አደርኚ ፣ ምንዳዩ በገደለው እናንተን ምን ዶላችሁ ቢሉንስ ?” በማለቱ ተሣቀ ።

“እናንተ መማሻውን አምጡ ፣ እኔ ለቀኛማች እነግራቸዋለሁ ፣ ብላት አያጡም” አሉ ሽማግሌው ።

“ደግ ብለኋል ፣ ያደርነው አንሶ ስንንቃቃ እንዋል እንዴ?” አለ አንዱ ችኩል መሳይ ።

አንዳንዶቹ ዶማ ለማምጣት ወደየቤታቸው ሲሔዱ ፣ ሽማግሌው ወደ ቀኛዝማች እልፍኝ አመሩ ። ባዳራሾቹ መኻል አልፈው እልፍኙ አጠገብ እንደ ደረሱ ከወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ጋር ተገናኙ ።

“ምነው? የደህናሁን ነው?” አሉ ሴትዮዋ — እኚህ ደሞ ‘ምን ሊሉ ይሆን’ በማለት ።



“ደህናስ ደህና ነኝ ፣ ቀኛማይን ፈልጌ ነው ፣ ቅድም አፈሣን ስት ጠይኢ እነግርሻለሁ ስል ቶሎ ሔድሽብኝ — —አገኘሽው አደል— —”

“በሉ ግቡ! — ግቡ! አሁን የእድሙን ምን አነሣሣሁ” ብለው ገለል አሉላቸው ።

“አላገኘሽው እንደሁ ብዬ ነው” አሉና ገቡ ። ሽማግሌው እጅ ነሥተው ከቀኛዝማች ፊት እንደቆሙ ሰላምታ ተለዋውጠው ፣

“ምነው ? ደህናም አይደለሁ እንዴ ?” አሏቸው ባክብሮት ።

“እኔስ ደህና ነኝ ፣ እየሀ እደይ ያደረው ሬሣ” — —ብለው እን ደጀመሩ ፣

“የቱ ሬሣ?”

“እየሀ እደጅሁ ያለውን ሬሣ ነዋ !”

“እኔ ታዲያ ምን ላርግ?”

“ልጆቹ እየትኻራችን ልንሔድ ነው ፣ በጧቱ ቢቀበርስ ቶሎ ጊዜ—”

“ህ! ታዲያ በላይነህ ታፈሰ ግቢ መቃብር አለ ያለው ማን ነው?”

“ኧረ ማንም አላለ ቀኛማይ ! አንቱ ሳትሰሙ ብለን ነውዴ —”

“እኔ ቀድሞውንስ መች አምጡልኝ አልኩና ፣ ሲያንዘፋዝፉ ያመጡት እነሱ ———”

“እነሱም አምጡ ብለውን ነው አላሉ አሁን ምናልባት እኔ ታልሰማ ማ አዘዛችሁ እንዳይሉ ———”

“ለኔ ብለው ተሆነ ፣ ሚጨራ ገበያ ያስጡት ፣ — —እንዴት የጠ ቀመኝን ሰው አመጡልኝ !”

“ይሁን ፣ ለዚሁ ነበር አመጣጤ ። እኛማ ለቄሶቹም ትነግሩልና ለሁ ብለን ነበር ።”

“መይ ሥራ አጣሁና ፣ ቢሻቸው ይፍቀዱ ቢሻቸው ይከልክሉ ፣ ሰውዬው አማራ መሆኑ ከታወቀ ቤተስኪያን መቀበሩ አይቀር ፣ ዐፈር አይከለከልም ፣ ዐፈር ያባታችን ያዳም ነው” አሉ ሽማግሌ ውን ትኩር ብለው እያዩ ።

“ለምን አልነገራችሁኝም ብለሁ እንዳትቆጡ ብለን ነው” ብለው ሽማግሌው መሰስ አሉ ። “ዐውሬ የሰውዐውሬ! ደግነቱ ሁላችንም

እላይ ቤት እኩል መሆናችን ፣ እንኳንና የሰው ፣ ያህያ ሬሣም እንበያ መኻል አይጣል — —ቲሾሙ ጊዜ ባሰባቸው ልበል፣ ሒደው የመጡለትማ እንኳንና ሬሣ ደሃም ባይኔ አታሳዩኝ ሳይሉ አይቀሩ ። ክፉ —የሰው ክፉ — ስባት ላብ !" እያሉ ተመለሱ ።

"እ —ሀ ፣ ምን አሉ?" አሉ ሁለት ሦስቱ ።

"ሲያቀብጠኝ ሔጄ—ተዋርጄ ልምጣ!" አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ።

"ተቆጡ እንዴ?"አለ አንዱ ።

"እኔ ያሉትን ቢሉ ምን አሻኝ! ቀደው አያለብሱኝ ፣ ቆርሰው አያጕርሱኝ ፣ ሥራቸው በጣም ያሳዝናል" አሉ ሬሣውን አሽቆልቁ ለው እያዩ ።

"ተናገሩሁ እንዴ?" አለ አንዱ በቁጭት ።

"በምን ምክኛት ይናገሩኛል!? — — እኔ ቸግሮኝ አለቁኝ ልል አልሔድኩ ።"

"እንዴት ይሁን አሉ?"

"እንዲህ አሉ ቢሉት ምን ያረጋል?"

"እኛስ ቢሆን ለነብሳችን ብለን ነውዴ — — — ማ የግድ ያዘን። ቄሶቹም ቢሆኑ ባፋቸው ነውዬ ለነፍሳቸው አላደሩም ፤ ይኸነዬ ከበ ርቲ ሞቶ ቢሆን እንደ ቀፎ ቆራጭ ጭሳቸውን እያምቧለሉና ምና ምኔአቸውን እያንሿሹ ከራስጌ—ከግርጌ ይሉ ነበር ፣ ላለው አፋሽ— አጎንባሹ ብዙ ነው ። ደህና ገላገሉን ፣ በጧት ቀብረን ወደየ ምላዳችን እንሔዳለን" ብሎ እንደ ጨረሰ መማሻ ሊያመጡ የሔዱት በየተራ ብቅ ብቅ አሉ ። አንዲት ሴትዮ ሬሣው ላይ ሸማ ጣል አደረጉ ። አንዳንድ የመንደሩ ሴቶች ቀስ—በቀስ እየመጡ ፣ ድምፃቸው ሳይሰማ አለቀሱ።

* * *

ቃሬዛው ሊነሣ ሲል ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ አጥራቸው በር ላይ ቆመው በነጠላቸው ጫፍ እንባቸውን እያባበሱ ስቅስቅ ብለው አለ ቀሱ ። እሚሟቱና አወዳደቁ ሁሉ ክፉኛ ቆጠቆጣቸው ። የሚወዱትም የሚጠሉትም ጠፉቸውና ፣ "አይ ሰው መሆን! አሁን የኛ ነገር ምን መላ አለው!!"አሉና እንባቸውን አንዠቀዠቁት ። የነበራቸውንም ቃል ኪዳን አስታወሱ ። ተስፋና ምኞታቸው በመለምለም ፋንታ ሲደርቅ እየታያቸው ቢናደዱም ፣ ምስጢራቸውን የሚያውቀው ሰው አንዳችም ትንፍሽ ሳይል በመሞቱ እፎይ አሉ ።



## ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

አፈሣን እንደ ቀብር ዐፈር አድፋፍተው ከሸኙና የጠሉት ሬሣ ከደጃቸው ከተወሰደ በኋላ ፣ ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ልባቸው ዲዲታ ውን ቢቀንስም ፣ አእምሯቸው ከመሸበርና አካላቸው ከመርበትበት አላ ረፈም ። ከመሞት ፣ እያገገሙ መኖርን ይመርጣሉ ። ዋሽተውም ቢሆን የሚያማክሩት ፣ ለመጠቃቀም ሲል ተጠግቶና ምስጢራቸውን ጠብቆ ከቀኛዝማች ጋር የሚያስማማ ሰው ፣ ቢያስቡ ፣ ቢያሰላስሉ አጡ ።

"ወይኔ ልጂት!" አሉና አጥር ዘሎ ከሚወጣ ውርደት እቤታ ቸው ውስጥ መንበርከክን መረጡ ። ሁሉንም እርግፍ አድርገው ወደ ራሳቸው ተመለሱ ። ሌላው ቀርቶ በጭንቅና በጥቃታቸው ሰዓት ከዐይነ —ሕሊናቸው የማይጠፋው ጊዮርጊስ እንኳ ትዝ አላላቸውም ። ከቤት ንብረታቸው ይልቅ ስለ ስማቸው አሰቡ ። በተለይም ጣውንታቸውን ሲያስቡ ይብስባቸው ጀመር ። 'እኔን እታገል እጥል ብላ የገዛ ጉድ ጓዷን ማሰች ፣ የገዛ ሸሯ ተደረባባት' እያሉ የሚሳለቁባቸው መሰላ ቸው ። 'አንቺ እኔንም ከማስገደል አትመለሺ ፣ አሁንም ቢሆን ያረግ ሺው ያክል ነው ፣ እኔ ተንግዲህ ወዲያ ምንሽም ምንሽም አይሻኝ ፣ እጅሽ ባንጠለጠለና ጀርባሽ ባዘለ ያፈቀደሽን ይዘሽ ሒጂልኝ' እያሉ ቀኛዝማችም ሲያሰናብቷቸው ታያቸው ። ምኞታቸው እሳት እንደ ለቀቁበት የሣር ክምር ይሆንባቸውና እርር ድብን ይላሉ ።

ዕቃ እንደጣለ ሰው አጥር— ላጥር ሲዞሩ ቆዩና ፣ መምሬ ተክለጊ ዮርጊስ ወደ ምንዳዬ ቤት እንደ ገቡላቸው "ተንግዲህ በነገሬ ማንም አይገባበት ፣ ተፈርቶ የት ሊደረስ ነው ፣ እስታሁንም በቁሜ የገደለኝ ፍራቴ ነው ፣ የገዛ ነገሬንማ እንደ ሚሆን እንደሚሆን ማረግ ታቃተኝ የሰው መሳቂያ መሆኔ ነው" ብለው በቀጥታ ወደ እልፍኝ ገቡ ።

"የት ሔደሽ ነበር ? ቤተክርስቲያን ደርሰሽ መጣሽ እንዴ?" አሉ ቀኛዝማች በርጋታ ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል እንደ ሰሙ እፎይታ ተሰማቸው ።

"እዎ" አሉ ያላሰቡትን ምክንያት በማግኘታቸው ደስ እያላቸው ። ሁለቱም ዝም አሉ ። ሴትዮዋ አፈሣን ከሸኙ በኋላ ያውጠነጠኗትን አዲስ መላ ለመናገር ተዘጋጅተው ሳለ ፣

"ያንን ሬሣ ወሰዱት—እስካሁን አለ?" አሉ ሰውዬው ድንገት ።

"እኛ በጧት ቀብረን ወደ የጉዳያችን እንሒድ ሲሉ ነበር ። ሰበበኛ የሆነ ሰውዬ ፣ ስንቱን አንካካው ፣ እኔማ የዚያን አገልግል ጉዳይ እስታ ውቅ ድረስ አሳቡ ሊገለኝ — — —"

አሁን ምን ያወቅሽው ነገር አለ?" አሉ ትኩር ብለው እያዩ ።

"አሁንማ ነገሩን ደረስኩበት ፣ 'ከቂል ዘመድ ደህና በሬ ይሻ ላል' አሉ አብዬ መሸሻ ። አንዳንድ ሰው ኮ ቲመሀሩትና ተው ሲሉትም ይመለሳል ፣ የዚህ የኔ ዘመድ ግን አይጣል ነው ። እንዲያው ብቻ ጥሎ አይጥሌ ደህና ባለሙያ ሚስት ሰጥቶታል — — —"

"እኮ ምንድነው ነገሩ? እሱ ነው እንዴ አገልግሉን ወስዶ የሰ ጠው?" አሉ በችኮላ ።

"እሱ ከየቱ! ደሞ ይኸን ያክል የት ዐውቆበት?—የት ያእበትና፣ እሱ ለራሱ እበት — — —"

"አሁን ታዲያ ምንድነው እምትዪው? እኔ ደሞ ፍንጭ ያገኘሽ መስሎኝ—"

"አንቱ ደሞ ብርቱ ዐመል አለብሁ ፣ ቃለ ነገርሁ አታስወሩም ፣ እኔ አሁን የሰማሁትን ሰምቼ ነው ልነግርሁ የመጣሁት — —"

"ምን ሰማሽ?—እንዲያው ነገሩን ዐውቄው የቀረው በቀረ!"

"ልነግርሁ አደል ፣ በተስኪያን ስሜ ትመለስ ፣ እያ ሃች መምሬ አድማሱ ቤት አጠገብ ያፈሣን ሚስት አገኛታለሁ ። ያለወትሮዋ ክንብ ንብ ብላ እየተቻኮለች እፊት እፊቴ ስትሒድ ፣ እሷ ትሆን ሌላ እያልኩ ልጣራ ሳመነታ ፣ ድንገት ዘወር ስትል ዐይን—ላይን ተጋጨን ። እግዚ ሐር ያክብራት ቆም ብላ ጠበቀችኝና ከመንገዱ ሸረር ስትልልኝ ስታ ለእስ አየኋት ። 'ምን ሆነሻል ብዬ ብጠይእት ዝም ብላ ታለእስ ጀመር። እኔም 'ምን ሆነሻል? ደህናም አደለሽ' ብዬ ወጥሬ ስለ ያዝኳት አንድ ባንድ ነገረችኛ!"

"ምኑን?" አሉ ለመስማት ጓጉተው ።

"ሌላማ ምን ፣ ስለዚያው ስለ ጉደኛ አገልግል ነዋ!"

"እስቲ ሙት በይኝ?!"

"እንግዲህ እህ ብለሁ አድምጡ ፣ መቼም ያንቱ ነገር — —"

"ወዮ ጉድ! ግድየለሽም ቀጥይ ።"

"ይኸ የኔ ዘልዛላ ፣ ሚስቱ ውላ ሳታድርና ደርሳ መመለሷ ላይቀር



ዘገየችብኝ ይልና እኔ ጋ ብቅ ብሎ ቆላ መውረዴ ነውና አንዷት እን ጀራ ባገልግል አስቋጥሪልኝ ብሎኝ ይመለሳል ። እኔ ደሞ ለሸዋርካብሽ ነግሬለት ወደ መንደር ገባሁ ። አንቱም እኮ እየሁ ተኝተሁ ነበር ። አቀብዬኝ ብሷታል መሰል ከዚህ ተሸክማ እያ ሃይ ድረስ ትወስድለ ታለይ ፣ እሱም አገልግሉን ተቀብሎ ቲሔድ ፣ የሱ ቢጤ ወደ ቆላ የሚ ወርድ ሰው ያገኝና ፣ አንተ እምትሔድ ተሆነማ ለምን ሁላችንም እን ደህማለን ፣ ይቺን አገልግል እኔ ማሳ አጠገብ ዐውሬ ለሚጠብቁት ልጆች ሰጥልኝ ፣ እኔ በሌሊት እመጣለሁ ብሏችኋል ብለህ ንገራቸው ይልና አገልግሉን ይሰጠዋል ። ያም እሺ ብሎ ቅብል ። እንግዲህ ተዚያ በኋላ ያጋጠመውን እናእም ፣ ማታ ከብትም እረኛም ከገባ በኋላ ነው አለች ፣ ላይን ያዝ ቲያደርግ ፣ እኛ እዚህ ጉድ! ጉድ ትንልና ትንጫ ጫ ያ አገልግል ይዞለት ወደ ቆላ የወረደ ልጅ አፈሣ ቤት ይመጣና 'አንድ እማላኽው ባለጠመንጃ ሰውዬ እመንገድ ጠብእ የኔንም ያንተ ንም አገልግል ቀምቶኝ ሔደ ይለዋል ።"

"የተገኘው አንድ አገልግል ፣ ሁለተኛው የት ሔደ?" አሉ ቀኛዝማች አቋርጠው ።

"እሱ ላይ እኔ እንጃ ፣ ይልእ ያወራችኝን ልንገርሁ" አሉ ደን ገጥ ብለው ። 'የሰው አገልግል ነው ፣ ባይሆን እሚበቃህን በልተህ መል ስልኝ ብለው ፣ ሊመታኝ ቲያፈጥብኝ ጊዜ ጥየለት ሸሸሁ' ብሎ አለው ። አፈሣም 'ያቺ እቴዋ ምን ትለኝ ይሆን ፣ ያን መሳይ አገልግል አስወሰድኩ ባት' እያለ ሲናደድ ያመሻል ። በመኻሉ አንቱን እንኳን አተረፈሁ ልበል ይልና ወዲህ ቲመጣ ፣ ሸዋርካብሽን እደይ ተቀምጣ ስታለቃቅስ ያገኛ ታል ። እሱም አፉ እያርፍ ፣ ምን ሆንሽ ይልና ይጠይቃታል ። ይቺ የኔ ቅልብልብ 'ይኸ ሁሉ ጣጣ ላንተ ባቀበልኩህ አገልግል የተነሣ ነው ብላ ሹክ ትለዋለች ። እሱ እንግዲህ ቀድሞውንም አገልግሉን ተነጠ እሁ ተብሎ ተነግሮታልና ሰውነቱ ይጠረጥራል ። አጅሬ የሞኝ ብልጥ አደል! ወዲህ መምጣቱን ይተውና አብረውሁ ተነበሩት መካከል ማን ቻቸውን እንደሆን እንጃ ፣ ሰውዬው እሞተበት ሥርፋ አገልግል ተገኝ ወይ ብሎ መጠየእ ። ከነምልክቱ ነግረውታል መሰል ፣ እንግዲህማ ማ ያምነኛል ፣ ከሽፍታ ጋ ተስማምቶ ምንዳዬን ሊያስገድል ነበር ብለው ይጣሉኛል ። የሆነው እስቲሆን ከፊታቸው ገለል ልበል ብሎ ገና ወፍ ታይንጫጫ ከቤቱ ወጥቶ ሔደ' ብላ መንታ —መንታውን እያነባች ነገረችኝ ። መቼም እሱ ይቅር ይበለኝ ፣ በዚህ በመሬት የተነሣ እኔም ጠርጥሬው ነበር" ብለው ከዚህም ፣ ከዚያም አማተው ያቀነባበሩትን ውሸት ኮስተር ብለው ነገሯቸው ።

ቀኛዝማች ወደ ማመኑ ቢያመዝኑም ፣ እእምሯቸው ከጥርጣሬ አል ተላቀቀም ።

"እውነቱም ውሸቱም እያደር ይለያል ፤ የሱ እጅ ከሌለበት ምን አሸሸው ታዲያ ?"

"ወዮ ጉድ! ለጊዜውስ ቢሆን ነገሩ እስቲጣራና ንጥሕናው እስቲታ ወቅ እንዳልጣላ ብሎ ነዋ! አሁን አንቱ እንደ ትላንትናው ንዴትሁና እኳኋንሁ ብታገኙት ትለቁታለሁ እንዴ? ያ ነገር ማለት ይኸ ነው ። ምንዳዬስ ቢሆን ነገሩ ታይጣራ ቢሰማ ፣ ቁስሌ ይሻርልኝስ ይላል? ያው ተያይዞ ገደል መሆኑ እማዶል ? እኔም ዘመዶቹን ገሎብኝ ዝም አልል ፣ መተላለእችን ነበር" ብለው ያቀረቡት ሐሳብ ራሳቸውን ስላሰ ደስታቸው ተንፈስ አሉ ።

"እስኪ ይሁን ? እኔ ግን እውነት ፣ እውነት አልመሰለኝም ። ባልና ሚስቱ እንዲህ ብለን እናስወራ ብለው ተማክረው እንደሆነስ በምን ዐወቅሽ ?"

"አያረጉትም ፣ ምንም ቢያስቡ ይኸን ያክል አያስቡም ፣ አንቱስ ብትሆኑ አታኡትምና ነው? ማ ይሙት እነሱ ናቸው እንዲህ አቀና ብረው እሚያስወሩት" አሉ በድፍረት ።

"ሞኝ ማለትስ አንቺ ነሽ ፣ ሰው የቸገረው ለት ተዚህ የባሰ ተንኮል ይሠራል ፣ ይኸማ ቀላል ነው ፣ እንዲህ ብለን እናስወራ ብሎ መመሳጠር ነው ። አሁን ያ አገልግሉን ያስቀማው የታል ቢባሉ ፣ እውነትና ሐሰቱ ይለይ ነበር" አሉ ኮስተር ብለው ።

"ኧረ እኛ ምን አገባን ፣ እዚያው እንደ ፍጥርጥራቸው እስበሳቸው ይኊተቱ ፣ እኔ ብቻ እምለምንሁ ነገሩ ታይጣራና እውነት ውሸቱ ታይ ለይ ፣ አፈሣ ተዚህ ተቤት የወሰደው አገልግል እሚቹ ሰውዬ ዘንዳ ተገኘ የሚል ወሬ ምንዳዬ እንዳይሰማና እንዳይጋደሉብኝ በምታም ኑት በወዳጅሁ በሚኻል ይዠኋለሁ" ብለው ቀኛዝማች ሳያስቡትና ታደርገዋለች ብለው ሳይጠረጥሩ ፣ ቤትየዋም ቀደም ብለው አደርገዋ ለሁ ብለው ሳያቅዱ ፣ ድንገት በመጣ ግፊት ሰውዬው እግር ላይ ጥም ጥም አሉ ።

ቀኛዝማች ደነገጡ ። ርኅራኄ ተሰማቸው ። "ኧረ በፈጠረሽ አም ላክ ይገዴሻለሁ ተነሽ?" ብለው ወዲያው አነሷቸውና ፣ "ምን መጣ ይህን ያክል ፣ እኔ እኔን የሚተናኮል ጠላት መጥቶ እንደሁ በማለት ተናደድኩና ተበሳጨሁዪ ፣ ይኸ ሌላ ሌላውማ የተለመደ ነው ። አፈሣ ሽፍታ በገንዘብ ገዝቶ ሊያስገድለው ነበር ቢባልስ ፣ ምን ይኮ ናል? ያው ላንቺ ስል ነገሩን ሽፋፍኜና አድበስብሼ ዝም ነው ። አሁ ንም ቢሆን እንኳን 'በሚካኤል ይዠሃለሁ' ብለሽኝና በልጆቻችንም ብትዪኝ ቃል አይወጣኝም ። እንግዲያው አሁን የምር አይደል



እምንጫወተው ፣ እኔማ አገልግሉን ወስዶ ነበር ካለችኝ በኋላ ብዙ ክፉ ክፉ ነገር አስቤ ነበር ። ሽፍታም ከሆነ ጠመንጃውን ሊገፍ ይሆ ናል" ብለው ዝም አሉ ።

የቤትዮዋ እንዲያ መጨነቅ የገዛ ዘመዳቸውን ለማዳንና ነገር ለማብረድ ስለ መሰላቸው ፣ ቀኛዝማች ልባቸውም ፊታቸውም ላላ ።

"በይ እንግዲህ ያም አለ ፣ ያም አለ ፣ አፈሣ አገልግል አድርስ ልኝ ብሎ የላከው ልጅ አገልግል ስለ ተነጠቀ ፣ አፈሣ ጠፋ ቢባል ማንም አያምንም ። ተንግዲህ የሚበጀው ነገር የተገኘው አገልግል በምኑም ፣ በምኑም አምሳያ ሆኖ ነውዪ የኛ አይደለም ተብሎ ቢወራ ልሽ በያት ። ሌላ ሌላው ቀላል ነው ። መቼም አንደዬ ሐሰት ተናጋሪ አድርገሽኛል ፣ አፈሣ የጠፋው ከቀኛዝማች ጋር ተጣልቶ ነው ተብሎ ይወራና ነገሩ ውሎ ይደር ። እንዲህ ከሆነ ምንዳዬ እንኳ የስሚ — ስሚ ቢሰማ ተገኘ በተባለው አገልግል አይጠረጥርም ። እኔ ግን ፣ ነገሩ በኔና ባንቺ ይቅር እንጂ ለዘዶአቸው ያስወሩት ነው የመሰለኝ ። አፈሣ ከዚያ ከሚቹ ሰውዬ ጋር ምንም ግንኙነት ባይኖረው ኖሮማ አይሸ ሽም ነበር ። ሽንጡን ገትሮ ነበር የለሁበትም የሚለን ። እኔ እንዲያው ያንቺን መርገብገብና መጨነቅ አይቼ ፣ ለኔ የመጣ ጠላትና ምቀኛ ያለመሆኑን ካወኩ በኋላ ተወት አረኩት ። በምንዳዬ ላይ የተፈጸመው ግፍም ቀላል ነገር አይምሰልሽ ። እስቲ ይኸ ድሃ ምን አረገው ፣ በምን ደረሰበት ፣ ከበቅሎ እኩል ሮጦ መከራውን አይቶ ባደረ ፣ ሰጠሁም ነማሁም እኔ ነኝ ፣ አሁን እሱን አስገደለና የሱን ማሳ አልሰጠው ፣ እንኳን እግዚአብሔር አተረፈው ። ቢሞት ኖሮ እገባበት ገብቼ አለቀ ውም ነበር ። እኔ እንደሚመስለኝ ጉዳዩ ይኸው ነው" አሉ ቀኛዝማች በሙሉ እርግጠኝነት ።

ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ የኔ ጉድ እስካልተጋለጠ ድረስ የፈለጉ ትን ቢሉና በዚያም አለ በዚህ ነገሬ ከተድሞነሞነልኝ ምን ቸገረኝ በሚል ብልሃት ፣ ነውም አይደለም ሳይሉ ሰምተው ዝም አሉ ። በልባ ሩን መጣፍ አሙን—አሙን ሲሉ ይውላሉ ፣ አንዳይ መጥቶ ሹክ ብሏ ቸው ይሆናል" በማለት ተገርመዋል ።

"ይኸስ ይሁን በጄ ፣ ምን ይደረጋል ፣ እንኳን ብቻ ፍጡነ—ረድ ኤት ሰወረው ፣ ይዋል ይደር እንጂ ሁሉም የጁን አያጣም ። አንቺም ለዘመድሽ ማድላትሽና መርገብገብሽ ያለ ነው ። ምንም ቢያረግ ሥጋሽ ነው ። ይኸ የሰው አገር ድሃስ እንዲህ ደሙ እንደውሃ ፈስሶ፣

ዛሬ ይሙት ፣ ነገ ይሙት ሳይለይለት ምን ታረጊለታሽ ! ተማክረው ምን ያሉት አይገማም አሉ" አሉ ቀኛዝማች በኩራ ስሜት ።

"እኔማ ምን አለኝና ምን ላርግለት፤ በምን አሳብቤ?" አሉ ሳይታወቃቸው ።

"እንዴት የለሽም፤ ለሰበብም ከሆነ ደሙ ፈስሷል።"

"ለሱ እሚሆን ምን አለኝ፤ እስቲ አንቱ ንገሩኝ?" አሉ ችግሩ የተቃለለ እየመሰላቸው ።

"ምነው ያ ዘመድ ያመጣልሽ ያልተቀጠቀጠ ወጠጤሽስ ?"

"ብልጥ ልጅ አስቀድሞ ያለቅሳል አሉ —— በሉ እንዳልኩ ።"

"እሂሂ! ትልቅ ነገር ሆነና ነው?! አዙሮ ማየት ነዉዪ ——"

"እኮ ምን ወጣኝ? —— ይሁን እኮ ነው ያልኩሁ ።"

"እኛን ብሎ በመጣና እኛን ብሎ በተጠጋ ———" ሳይጨርሱ፣

"የምን ነገር መደጋገም ነው ። ተንግዲህ ውሾን ያነሣ ውሾ ነው ያሉት ቢጤ ነው ። ከኔና ካንቱ እንዳያልፍ —— ባንቱ ያምራል ፣ አንቱ ወስደሁ ስጡት" አሉ የሰውዬውን ልብ ለማማለልና ውዴታቸውን ለማሳየት ።

"የለም! የለም! ያንቺን አንቺ አድርሺ ፣ —— እኔ ደሞ የኔን"

"ደሞ ሌላ?"

"አንቺኮ ዘመድሽ ስለ በደለው ፣ ማንም ሳያውቅ መካስሽ ነው ፣ ማገገሚያውን ። መቼም ወሬ መያዣ የለውም ። ጨማምረው ቢነግሩትም እፍ ማስያዣ ይሆናል —— ቀላል እኮ ነው ፣ አንቺ በናትነቴ ሰጠሁህ ትይዋለሽ ፣ የኔን ደሞ ዋል አደር ብለን እንሰጠዋለን ። እ! —— ይኸው ነው" ብለዋቸው ወደ ምንዳዬ ጐጆ አመሩ ።



## ምዕራፍ ሐያ

አውቶቡሱ በሁለት ትይዩ ጐራዎች ላይ እንደ ጆሮ ተለጥፋ በሸለቆ ውስጥ የተቆረቆረችውን የካራቆሬን ከተማ ዐልፎ ጠመዝማዛውን ቁልቁለት እንደ ወረደ ፣ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ እጐናቸው የተቀመጠውን መንገደኛ፣

"ወንድሜ፤ የሣር አምባ ሰው መስልኸኝ ——" አሉት በለዘብታ ።

"እዎድ ነኝ" አለ ፈጠን ብሎ ።

"ሰው ልጠይእህ አስቤ ፣ ታሁን—አሁን እያልኩ ሳመነታ ——"

"ማንን?"

"ቀኛማይ በላይነህ ታፈሰን ታእቸው የለ?!" አሉ እንደሚያውቃቸው እያወቁ ።

"ሣርአምባ ተወልጄ እሳቸውንማ ታላወኩ?——"

ቀስ በቀስ ወሬ ቀጠሉ ። ሌላው ቀርቶ የቀኛዝማችንና የሳቸውን ግንኙነት ጠቀስ አድርጎ በማስደሰት ፣ እሱ ወደ ማጀቴ ሲገሠግሥ እግረ—መንገዱን ያየውንና የሰማውን ሁሉ ነገራቸው ። ከፋኛ ደነገጡ ።

"የኔ መድካኔ—ዓለም የት ሔዶ? ነግሬዋለኋ! አደራህን ብየዋለሁኋ! እኚህ ሰውዬ አንድ ነገር ቢሆኑ ኖሮ ፣ አዳሜ ይቺ ገደ—ቢስ እያለ መግቢያ መውጪያ ያሳጣኝ ነበር ። የእሱም ቢሆን ነገ ተነገ ወዲያ ይሽርለታል ፣ ዋናው ነገር አለመሞቱ ብቻ" አሉ በልባቸው ።

አውቶቡሱ ደብረ—ሲና ከተማ እንደ ደረሰ ከተንገሮቹ በከፊል ለቁርስ አይሉት ለምሳ በየተራ ሲወርዱ ወ/ሮ ድጅ—ይጥኑ ላቀችን በእጅ ምልክት "አንቺ እዚያው ቆዪ" አሏት ።

አብሯቸው ከሚጓዘው የሣር አምባ ሰውዬ ጋር ከመንገድ በታች ምግብ ቤት ገብተው እየተቆነኑ ጥቂት ከበሉ በኋላ ፣ "በል አንተ ቅልጥፍጥፍ አርገህ ብላ ፣ እንዴት ያለ ማለፊያ ወጥ መሰለህ ፣ እኔ መኪና ላይ ስወጣ ብዬ ብዬም አይለኝ" ብለው ተዉለት ። ቤትዮዋ የምግቡን ዋጋ ተሽቀዳድመው ከፈሉ ። ባላገሩ ሰውየም ደስ